# ድርቅና ጠኔ በኢትዮጵያ

| | |
|---|---|
| **የዲሬክተሮች ቦርድ** | አቤዬ ፎርድ<br>ሊቀ መንበር<br>ያዕቆብ ሀይለማርያም<br>ፈንታሁን ጥሩነህ<br>አህመድ ኑር |
| **ዋና አዘጋጅ** | ፈንታሁን ጥሩነህ |
| **የአዘጋጅ ቦርድ** | ኤልሳቤጥ ተስፋዬ<br>ገብርኤል ዳንኤል |
| **የስርጭት ሀላፊ** | አህመድ ኑር |
| **የአማካሪ ቦርድ** | ክፍአለ ገብረ ጊዮርጊስ (ዶ/ር)<br>(ሜሪላንድ፣ ሰሜን አሜሪካ)<br>ኢንዱ ቦናና<br>(ጣልያን)<br>ፍቅሬ ቶሎሳ (ዶ/ር)<br>(ምዕራብ ጀርመን)<br>ሐረጓ ጌጡ (ዶ/ር)<br>(ቶሮንቶ፣ ካናዳ) |


ጽሑፎችን በዚህ አድራሻ መላክ ይቻላል።


SEM INNA WORQ

P. O. BOX 43003

WASHINGTON. D. C. 20010

U. S. A.



ISSN: 0891-9119

Sem Inna Work Corporation is a non-profit tax-exempt organization. Washington, D. C., U.S.A.

# ስ ም ና  ወ ር ቅ

፪ኛ ዓመት ቁ ፩/፪ የካቲት ፲፱፻፹፩
ልዩ የጥናት እትም

## ማ ው ጫ

ርዕሰ አንቀጽ 1

ረሀብና ተስቦ በኢትዮጵያ 7
ከፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ

ረሀብ ድርቅና መንስኤዎቻቸው 38
ከአቶ ገብርኤል ዳንኤል

የኢትዮጵያ ረሀብና የምዕራባውያን ጋዜጠኞች አስተያየት 73
ቀርቾ ፈይሣና ጓደኞቹ

ሰላም በኤርትራ 113
ከዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም

ደ ብ ዳ ቤ ዎ ች 128

ማስታወሻዎች 133

# ርዕሰ አንቀጽ

## ድርቅና ጠኔ ከምርምር አንጻር ሲታይ

ስለድርቅና ስለጠኔ በምርምር ደረጃ በምንነጋገርበት ጊዜ ከተራ ገለጻ ማዶ ዘልቀን ጠለቅ ወዳለ ትንተና እንገባለን። በተራ አነጋገር የድርቅና የጠኔ እንዲሁም አብረው ተከትለው የሚሄዱት ችግሮች ሁሉ መንስኤና እንዴት፣ ለምንና ለማን የሚሉትን ጥያቄዎች የሚመልሱ አይደሉም። በጽሑፍ ደረጃ አያሌ ድርሰቶች በምርምር ላይ ያልተመሠረቱ፤ ጥልቅ ጥናት ያልተደረገባቸው ሐሳቦችን አዝለው ይወጣሉ። በዚህ ደረጃ የሚሰነዘሩ መንስኤዎችም ሆኑ መፍትሄዎች በሃገር ደረጃ ሊወሰዱ ለሚገባቸው እርምጃዎች እምብዛም የሚያገለግሉ አይሆኑም። አገልግሎት ላይ ቢውሉም አገልግሎታቸው መሠረታዊ መፍትሄ በማበርከት ደረጃ ሊታይ አይችልም ማለት ይቻላል። በሌላ በኩል ደግሞ ምርምርና ጥናት የተደረገባቸው ድርሰቶች ስለድርቅና ስለጠኔ እንዲሁም አብረው ስለሚሄዱት እክሎች ሁሉ መሠረታዊ የሆነ ግንዛቤና ዕውቀት እንዲኖረን ከመርዳታቸውም ሌላ መፍትሄም ለመዘየድ አመቺ ሁኔታን ያዘጋጃሉ። በተጨማሪም ጠቃሚ የሆነ የዕውቀትና የምርምር ዘዴ ክምችት እንዲኖር ይረዳሉ።

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ የምድር መድረቅ ብቻ ሳይሆን የሐሳብና የአስተሳሰብ ድርቅ ሰፍኖ ይገኛል። አስቸኳይ እርምጃዎችና መፍትሄዎች በሚያስፈልጉባቸው አንዳንድ

አቢይ የሃገሪቱ ጥያቄዎች ላይ አርኪና አጥቃሚ መፍትሄዎች አይቀርቡም። ለዚህ እክል አንዱና ዋነኛው በቍንጽልና በጊዜያዊ ግንፍል ሀሳቦች ላይ የተመሠረቱ መፍትሄዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ስለሚደረግ ሊሆን ይችላል። ለእክሉች የሚቀርቡ ሐሳቦች በጥናት ላይ የተመሠረቱ የምርምር ውጤቶች ይሁኑ ቢባልም ሕዝቡ ያልተሳተፈባቸው ጥናቶች ብቻቸውን የሚያመጡት ውጤት እልባት ሊያስገኝ የሚችል አይሆንም። በሕዝቡ ተሳትፎ ያልተመሠረተ ጥናት የማድረጉ እርምጃ ሕዝቡን ለሚዘየዱ መፍትሄዎች እንግዳ ከማድረጉም በላይ ለመፍትሄዎች ተጨባጭ አስተዋጽዖ እንዳያደርጉ የሚገረግር እክል ነው። በምሁሮቻችንና በሕዝቡ መካከል ያለው የግንኙነት ዓይነት መታወቅ አለበት። በምሁሮቻችንና በመንግሥት መካከል ያለው ግንኙነት ምን እቅድ ይዞ እንደሚሄድና ምን መሆን እንደሚገባው ራሱን የቻለ ጥናት ያስፈልገዋል። ባሁኑ ጊዜ ግን ምሁሩ ጥናት ቢያቀርብ በጠረጴዛ ክልል ብቻ የተወሰነ ከመሆን አይዘልም። መፍትሄ በመዘየድ ረገድም ጥንት ይሠራባቸው ከነበሩ አሠራሮች ማዶ የማቅረብ ሆነ የፈጠራ ችሎታ የማሳደግ ዝንባሌ እምብዛም አይታይም። ድርቅም ድርቅ ይባል እንጅ ከጥንት ይዘቱ እየተለየ በዚያው ልክም ልዩ መፍትሄ እየጠየቀ መሄዱ የማይቀር ነው። ጊዜያዊ ተጨማሪ ምክንያቶች በየታሪካችን እጽቅ ስለሚከሰቱ ድርቅን በድርቅነቱ ብቻ ተመልክቶ የጥንት መፍትሄዎችን ብቻ ለማቅረብ መቃጣት ራሱን የቻለ ድክመትን ያስከትላል። ስለዚህ አዳዲስ ዘዴዎችን (መፍትሄዎችን፤ አስተዳደርን፤ አቀራረብን፤ አስመልክቶ) ለማቅረብ የችግሩን እድገት ታሪክና ሕዝቡ የሚያቀርባቸውን መቋቋሚያ ዘዴዎች መከታተል ያስፈልጋል።

በዚህ እትም የቀረቡልን ጽሑፎች ከተለያየ አቀራረብ

እንጻር ተቀነባብረው የመጡ ጥናቶች ሲሆኑ ለወደፊት ስለዚሁ ርዕስ ለሚደረጉ ጥናቶች ዓይነተኛ መነሻ እንደሚሆኑ የማያጠራጥር ነው። እነዚህ ጽሑፎች በአንድ ርዕስ ላይ ያተኩሩ እንጂ ደራሲዎቹ ከተለያየ አቅጣጫ የራሳቸውን (የግላቸውን) ሀሳብና ድምዳሜ ነው ያቀረቡልን። የሀሳቦች ልዩነት ሆነ መቃረን ቢኖርም የሚያስፈራ ሳይሆን በብሩህ ልቦና ተመልክቶ መገምገም ተገቢ ይመስለናል።

ፕሮፌሰር ጌታቸው ሀይሌ በተለይ የጥንቱን የድርቅ የረሀብና የተስቦ ታሪክ ከነማስረጃው አቅርበውልናል። ይህ ኢትዮጵያን በተደጋጋሚ የሚያጠቃው እክል በታሪክ ውስጥ ብዙ ዓይነት ጠባይ ይዞ መከሰቱን ጽሑፋቸው ያመለክታል። የተለያዩ መንግሥታትም የሞከሩትን የተለያየ መፍትሄ አብራርተው ገልጸውልናል። ከዚህ ታሪክ የምንማራቸው አያሌ ጠቃሚ ቁም ነገሮች መኖራቸውን ጠቁመን ለአንባቢያን እንተወው። በቅርቡ የድርቅና የጠኔ ታሪክ በኩል መንስኤዎቹን አስመልክተው አቶ ገብርኤል ዳንኤል ሰፋ ያለ ማብራሪያ አቅርበዋል። ይህ ክስተት ኢትዮጵያን ብቻ የሚያጠቃ ሳይሆን የአፍሪካን ሰሜናዊና ሰሜን ምስራቅ ክፍል ወደምድረበዳነት እየለወጠ በመሄድ ላይ መሆኑን እንረዳለን። «የምድረ–በዳነት ወረርሺኝ» ልንለው ይቻላል።

«ኢትዮጵያ» የሚለው ስያሜ ወደቅጽልነት ወይም የረሀብ መግለጫ ወደመሆን እንዴት ተሸጋገረ። «የዳቦ ቅርጫት» ትባላለች እየተባለች የምትጠበቅ ሀገር የረሀብ ምሳሌና የረሀብ ተምሳሊት ወደመሆን የተሸጋገረችበት ምክንያት አለ። በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተንነነ ያለው ፖለቲካዊ ውስብስብ የኢትዮጵያውያንን በድርቅ መመታትና በጠኔ መሰደድ ምክንያት

በማድረግ በሥልጣን ላይ ባለው መንግሥት ሳቢያ በሶሻሊዝም ርዕዮተ–ዓለም ላይ፤ በኢትዮጵያ የጥንት ታሪካዊ ዝና ላይ፤ በሀገሪቱ ሕዝብ ነፃነት ወዳድነት ላይ፤ እንዲሁም በአፍሪካ ውስጥ ሀገሪቱ ባላት ተምሳሌአዊ ቦታ፤ .....ወዘተ ምዕራባውያን ጋዜጠኞችና የየጋዜጣው ርዕዮተ–ዓለም ታሪክን የመናድ ዘመቻ በማካሄድ ላይ መሆናቸውን እነቀርቸ በሰፊው መዝግበው አቅርበዋል። ይህ ዓይነት ዘመቻ እንዲቆም የኢትዮጵያውያን ግንዛቤና ትግል የሚያስፈልግ ይመስላል። ግንዛቤው በቅድሚያ ከገዛራስ ጋር የሚደረግ ትግልን ሲጠይቅ ሌላው ትግል ደግሞ ታሪክን የማስከበሩና ትክክለኛ ቦታውን ማስያዝ ይሆናል ማለት ነው።

የሀገሪቱ የውስጥ ፖለቲካዊ ውዝግብ በብዙ የፖለቲካ ደራሲዎች በቸልታ የሚታለፍ ጉዳይ እየሆነ መጥቶአል። የፖለቲካ ቁርቁስ የሕዝብ እልቂት የሚገታበትን መፍትሄ ለመሻት መሆን ሲገባው የሕዝብን ችግርና እልቂት እያባባሰ በመሄድ ላይ ነው። ፖለቲካ በእልህ እሽክርሪት ውስጥ ከገባ የእልህ ፖለቲካ እንጂ ፖለቲካ ሊባል አይችልም። በዚህ የፖለቲካ መተላለክ ሳቢያ አንዱ ከሌላው ወገን የሚገድለውን ሰው ብዛት ከማስላት ሌላ አይታየውም፤ ሌላውን ወገን አዳከምኩ ለማለት የእልቂት ዘመቻወችን መዘየድ እያስከተለ ይመጣል እንጂ። ይህ ከመሬት መድረቅ እክል ጋር ሲደመር የሕዝብን እልቂትና መሰደድ፤ የረሃብንና የጠኔን በተከታታይ መከሰት ያመጣል። በኢትዮጵያ ውስጥ የጠኔና የረሀብ መባባስ እንዲሁም የእድገት መሰናክል ሁሉ በፖለቲካው ሁኔታ በተለይ በብሔርችና በብሔረሰቦች ጥያቄ ላይ ያረፈ መፍትሄ አለመገኘት ምክንያት መሆኑን እንገነዘባለን። በኤርትራ በኩል ያለው በተደጋጋሚ የሚከሰት

እልቂት አገሪቱን በጠቅላላ ከዳር እስከዳር በማድማት ላይ ይገኛል። ይህን ጥያቄ በሚመለከት ዶክተር ያዕቆብ ሀይለ ማርያም አስፋፍተው በመተንተን ለፖለቲካው ውዝግብ መፍትሄ ለሕዝቦችም ሰላም የሚገኝበትን መንገድ የሚከፍት ጽሑፍ አቅርበዋል።

በዚህ አጋጣሚ ምርምርና ጥናትን አስመልክቶ እነቆርቆ በቡድን ተደራጅተው ያሳዩትን አርአያነት ማንስት ትምህርታዊ ነው ብለን እናስባለን። መልካም አርአያነቱ በአሁኑ ጊዜ ተበታትኖ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ አያሌ በመሆኑና ከአብዮቱ እንቅስቃሴ ወዲህ እንዲሁም በተለያዩ ጦርነቶች ሳቢያ መፈራረቅ፤ አለመተማመን እና አንዱ ለሌላው ባይታወር የመሆን ዝንባሌ እየገፋበት ስለቀጠለ ይህን አሉታዊ ሂደት በመቋቋም ያላቸውን ልዩነት በማጥበብ የጥናት ቡድን መፍጠር በመቻላቸው ነው። ሀገራችን ያለችበት ዝቅተኛ ስፍራ ጥቃቅን ልዩነቶችን ቦታ የማይሰጥ መሆኑን መረዳት ባሁኑ ጊዜ እጅግ አስፈላጊ ይመስለናል። የነቆርቆ የጥናት ቡድን ትምህርታዊ የሆነ አርአያነት አለው የምንለው የምርምር ጽሑፎች ለማውጣት ውሳኔ በማድረጋቸው ነው። ለሃገራቸው ሕዝብ በገቡት ቃል መሠረት የመጀመሪያ ውጤታቸው የሆነውን ጥ ናታዊ ጽሑፍ በዚህ መጽሔት ሳቢያ አቅርበውልናል።

* * * *

## የአዘጋጅዎች ማሳሰቢያ፤

ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ እና እንዲመቸ ኢትዮጵያን በሚመለከቱ አንገብጋቢ ጥያቄዎች በአንዱ ላይ ልዩ ጥናት እንዲደረግ ጥሪት እናደርጋለን። እነዚህ ጥናቶች በልዩ የጥናት እትም ለአንባቢዎች ይቀርባሉ። ይህ እትም የመጀመሪያ ውጤታችን መሆኑ ነው። እስካሁን ከተለያዩ አንባቢዎች የቀረቡልን ሀሳቦች በኢትዮጵያ ጊዜያዊ የፖለቲካ ሁኔታ ላይ ጥናት እንዲደረግ እና ሀሳብ እንዲንሸራሸር የሚጠይቁ ናቸው። ስለዚህ የሚቀጥለው ልዩ የጥናት እትም የሚያተኩረው በዚሁ ጥያቄ ላይ ይሆናል። የኢትዮጵያ ጊዜያዊ የፖለቲካ ሁኔታ ላይ የጥናትና የምርምር ጽሑፍ ማቅረብ የምትሹ ግለሰቦች፤ ቡድኖችና ድርጅቶች የጥናቶቻችሁን አርእስት ከአሁኑ እንድታስታውቁን ይሁን።

---

### ስለደራሲዎች አጭር ሀተታ

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፤
ፕሮፌሰር ጌታቸው በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት አገልግለዋል። ኢትዮጵያን በሚመለከት አያሌ የምርምር ጽሁፎች ን አበርክተዋል። የምርምር ስራዎቻቸውን ተመልክቶ የከፍተኛ ሽልማት ተተባይ የማክአርተር ፋውንዴሽን አድርጎዋቸዋል። በሚቀጥለው እትማችን የህይወት ታሪካቸውን ባጭሩ ስለምናወጣ ብዙ ከመተረክ እንቆጠባለን።

ዶክተር ያእቆብ ሃይለ ማሪያም፤
ዶክተር ያእቆብ በኖርፎልክ ስቴት ዩኒቨርሲቲ አረዳት ፕሮፌሰር ናቸው። የህግና የንግድ ስራ ትምህርት የገበዩ ሲሆን በነዚሁ የስራ መስኮች በመምህርነት በመስራት ላይ ይገኛሉ።

አቶ ገብርኤል ዳንኤል፤
አቶ ገብርኤል በመድሃኒት ቀመማ ትምህርት የሰለጠኑ ሲሆን በዚሁ መስክ የማስትሬት ዲግሪ አላቸው። በአሁኑ ጊዜ በአፍሪኬር ድርጅት ዉስጥ በሙያቸው በስራ ተሰማርተው ይገኛሉ።

እንቆሪቸ ፈይሳ፤
ስለእኑ ቆሪቸ ማንነት ቡድኑ ራሱ የጻፈውን ይመልከቱ።

# ረኀብና ተስቦ በኢትዮጵያ

ከፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ*

ለፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም

## መቅድም

በኢትዮጵያ ላይ የሚወርደውን የዝናም መጠንና የሀገሪቷን የአየር ብልጽግና ያየ ሰው ኢትዮጵያን ጥጋብ እንጂ ረኀብ ያስቸግራታል ብሎ መገመት ያዳግተዋል። ዘፋ (ሚከው ደኑ) እየተመነጠረ ሲሄድ ሰማያትም ንፉጎች ሆኑ። ዝርዝሩን የአየሩን ጠባይና የዓፈሩን ዓይነት ለሚያጠኑ ልተወውና ረኀብና ተስቦ በኢትዮጵያ በታሪክ በኩል የቱን ያህል እንደነበሩ ለማሳየት አንዳንድ ማስታወሻዎችን ከታሪክ ገጾች ልጥቀስ። ማስታወሻዎቹ አንዳንድ መጻሕፍት ስመለከት እንዳጋጣሚ ያገኘኋቸው ስለሆኑ ጥናቱ መነሻና ውጥን እንጂ የተሟላ አይደለም። የሰምና ወርቅ አዘጋጆች ደጋግመው ባይጠይቁኝ ደፍሬም ለአንባቢዎች አላቀርበውም ነበር።

በኢትዮጵያ የረኀብ ምክንያት ሆነው ካገኘኋቸው ውስጥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ይገኙበቸዋል።

(1) የዝናም አልፎ አልፎ መቅረት አንዳንዴም መብዛት።
(2) የአንበጣ በየጊዜው መምጣት።
(3) ሰብሉን በረደ፣ ተምችና አመዳይ መምታት።
(4) ተላላፊ በሽታዎች በሰውና በከብት ላይ በየጊዜው መነሣት።
(5) የአስተዳደር በደል።
(6) የእርስ በርስ ጦርነት።
(7) ረኀቡን መቋቋሚያ ዘዴዎች አለማግኘት።
(8) የመሬቱ ዐፈር በዝናም መታጠብ።

የበዓለት መብዛትም በገበሬው ላይ ችግር ሳይፈጥር አልቀረም። ምንም እንኳን በነሱ ምክንያት መሬቱ ባያድርም ጊዜ ለመሸማት ገበሬዎች ሁል ጊዜ ሲጣደፉ ይታያል።

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በማንኛውም ጊዜ ረኀብተኛ ነው ማለት ከባድ

እንጋገር ይሆናል። ግን ልብ ብለን ብንመለከትው ኢትዮጵያ ገበሬው ከነቤተሰቡ ወተት ጠምቶት፣ ሥጋ አምሮት የሚኖርበት አገር ናት። ሥጋ የበሉ እንደመሰላቸው በጥቂት ቋንጦች እንጀር ተቀምጠው እነሱን እነሱን እያዩ የሽሮ ወጥ ራት የመብላት ዘዴ ያላቸው ወገኖች አሉ ሲባል ቀልድ ይመስለኝ ነበረ። ሁላችንም ወደምናውቀው እንመለስና ከቀኑ በማንኛውም ሰዓት እንግዳ ቢመጣ መጀመሪያ እህል ውሀ ይቀርብለታል፤ ይህ መስተንግዶ እንግዳው ረኀብተኛ መሆኑን መመስከር ይመስለኛል። ሐሳቤን የሚደግፉልኝ የሚመስሉኝ ተጨማሪ ነገሮች እነሣለሁ፦

ንጉሦች በየአውራጃውም ወኪሎቻቸው ለሹማምንትና ለጦር መኳንንት ለሕዝብም ተመርጦ ግብር ያገቡ እንደነበረ ሰምተናል፤ ያየንም የተካፈልንም እንኖራለን። የተካፈሉ ሰዎች ከግብሩ ገበታ ለመድረስ ስለአለው «ተጋድሎ» ሲነግሩን ረኀብ የጸናበት ብቻ የሚታገሠው ይመስላል፤ ያለው ግፊያ፤ ጉሽምትና ዱላ ተደጋግሞ በልሰማው ተረት ይመስለኝ ነበር። እንዳንዶቹ እንግዶች ከግብሩ ገበታ ላይ ሥጋ በጉያቸው ይዘው ይሄዱ ነበር።

መምህራን ሊያደርጉን አስበው ነበር መሰለኝ በ1943 ዓ/ም የትምህርት ጓደኞቼና እኔ ከየቦታው ከመጡ ተማሪዎች ጋራ የክረምት ትምህርት እንድንማር ተደረገ። ትምህርቱ ሲፈጸም የመምህራን ማሠልጠኛ ዲሬክተር የነበሩት ሰው (ካናዳዊ ነበሩ መሰለኝ) የትምህርት መደምደሚያ በዓል አደረጉልንና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ዘፈኖች እያሰያዙን ሰናሸበሽብ አምሽተን አደራሽ እንድንዘዋወር ተጋበዝን። ሻይና የሚቆረጣጠሙ ነገሮች ወደተዘጋጀበት አዳራሽ እንድንዘዋወር ተጋበዝን። ከዳራሹ ብቅ ስንል በየጠረጴዛው ላይ መግለሲትና ማባ በመሰሉ ዓይን በማይሞሉ ዕቃዎች ቆሎና ብስኩቶች አየን። እስፈላጊነታቸው እንደመክሰስ ለማምሸሸ እንጂ ረኀብ ለመግቻ መሆኑን እላወቅንምና ቀድሞ የደረሰ ከፈሰላቸው ወደኋላ ለቀረው ምንም ያህል እንደማይተርፍ ወዲያው ተረዳን። ድርውንም ስር የሰደደ ጨዋነት ስለሌለ ያሉትን መምህራን (ያችን በልዩ ዓይን እናያት የነበረች ቆንጆ ህንዳዊት ሳትቀር) ሳናፍር በጠረጴዛዎቹ ላይ ተራ ኩትንባቸው። በዚያን ጊዜ የቆጨኝ ወደኪሳችን ከገባነው ይልቅ እቃዎቹ እየተደፉ ከመሬት የፈሰሰው ቆሎ መብለጡ ነው። እንግዲህ ይህ የሆነው የዛሬ ሠላሳ ስምንት ዓመት ነው።

የዛሬ ሐያ አንድ ዓመት ግድም ደግሞ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ባለ ሥልጣኖች አዲሱን ሕንፃ ለማስመረቅ ወደጉለሌ እንድ አውለሳ ሜዳ ፈልገው ሰፋ ያለ ግብዣ አደረጉ። የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ሁሉም የተጠሩ

ይመስለኛል። በዚያ ላይ እንደኔ ያሉ የውጭ እንግዶች ነበሩ። ሥርዓቱ ምግብ ያዘለው ከድንኳን ውስጥ ያለው ረጅሙ ገበታ ሲከፈት በሰህን የምንፈልገውን ያህል እያነሣን ለተረኛ ገለል ማለት ነበር። እንደታሰበው አልሆነም፤ ከላይኛው ታሪክ የገለጽኩት መራኮት መልኩን ሳይለውጥ መጣ። ልዩነቱ እዚህኛው ላይ ጓደኞቼና እኔ ሌሎችም እንዳደች ከትግሉ አለመካፈላችን ነው።

ወደሸርሽር ሄዶ አገልግል ሲከፈት በአካባቢው ያለው እረኛ ሁሉ ከበቁጭ የሚለውና ፍርፋሪ ሲጣልለት እጅ ነሥቶ ጎረስ ጎረስ የሚያደርገው በቤቱ በሰዲቃ በወግ በማረግ ከሚቀርብለት ይልቅ የሰው እጅ አይቶ የሚያገኘውን ትራፊ መርጦ ነው ብየ አላምንም። እኔም አንድ ጊዜ እነሱን ነበርኩና በቅርብ አውቀዋለሁ። ባጭሩ የሒያ አራት ሰዓት ራብተኞች ባንሆንም የእህል ስቀቀን ያልወጣልን ሕዝብ ባንሆን እንቀርም።

ይኸንኛውን ማስረጃ ደግሞ በቅርብ ጊዜ ነው የሰማሁት። ለቅሶኛ ከቀብር ሲመለስ እንባ አድርቅ ንፍሮ እንደሚቀርብ ሁላችንም እናውቃለን። በእንደዚህ ያለ አንድ አጋጣሚ ግማሹ ለቅሶኛ አስከሬኑን አጅቦ ወደ ቀብር ሲሄድ ግማሹ ከልቅሶው ቤት ቀርቶ ነበር። ወደ ቀብር የሄዱት ሲመለሱ ከልቅሶ ቤት የቀሩት እንባ አድርቁን ዉርሰውት ኖሮ ተሰቀው ወደየቤታቸው ተበታተኑ።

ከላይ የረኀብ ምክንያቶች ያልኳቸው ሁሉም ማብራሪያ አይፈልጉም። ኢትዮጵያ ከእንበጣ መፈልፈያ አገሮች አንዷ መሆኗ የታወቀ ነው። በአምስተኛው ቍጥር የአስተዳደር በደል ያልኩት የመሬት ይዞታንና ግብርን ይመለከታል። ይህንንም ከዚህ በሰፊው መተቸት የተበላን ማሞስኪት ይሆናል። የሀገራችን የመሬት ይዞታ በብዙ አውራጃዎች የተዛባ እንደነበርና ገበሬው ለሚከፍለው ዓሥራትና ግብር ተመጣጣኝ ጥቅም እንዳላገኘበት በሰፊው በየበታው ተተችቷል። ብቻ ዉርሰን እንዳናልፈው ልዑል ራስ እምሩ ስለዚህ ጉዳይ ገና ባልታተመው ማስታወሻቸው የጻፉትን እንዳለ ልጠቅሰው እወዳለሁ። ጊዜውም 1923 ዓ/ም ከዘውድ በዓል በኋላ ነው።

> በዚያ ወራት የሹም ሽሩ ስራ ሁሉ ካለቀ በኋላ አንድ ቀን ወደሚኒስትሮች ክፍል የምክር ቤት ስለተጠራሁ ሄጄ። እንደኔውም ሚኒስትሮች ያልሆኑ ሌሎች ጥቂት መኳንንቶች ነበሩ ከሚኒትሮች ጋር ወደ እስራምስቱ እንሆን ነበር ወደተዘጋጀው ስፍራ ገብተን እንደተቀመጥን፦ ጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደ መስቀል የተጠራንበትንና የተሰበሰብንበትን ጉዳይ በዝርዝር አመለከቱን፤

ነገሩም በጉራጌና በከንባታ ወገን ያለው አገር ባላባቶች ባንድነት ሆነው እቤቱታ ላስታወቁት ጉዳይ ነበር፦ ቃሉም የገባሩ ግብር ጥንት ትኒሽ ነበር እንደ መሬቱ መጠን ለመልከኛውና ለሽለቃው የሚከፈለው በየጊዜው የሚለዋወጠው የሸለቃው ሁሉ ግን እንዳንድ ነገር እየጨመረ ግብሩን ሁሉ እሳድጎብን አሁን ብዙው ገባር መገበር አቅቶት መሬቱን እየተወ ተሰደደ። የዚህንም የተሰደደውን ገባር ግብር እኛን ባላባቶችን የገድ ገብሩ ብለው ያዙን። የተሰደደው ገባር እየመኪንንቱ የወሰሰማና የጉልት መሬት ነው የገባው። ይኸውም የወሳሰማና የጉልት መሬት የወሰሰማና የጉልት መሬት ነው የገባው። ይኸውም የወሳሰማና የጉልት መሬት የመንግሥት ግብር ብዙ ስለሌለበት እየተስማማ እየሄደ እርቦ እራሽ ሆነ። ለሄደውና ለሚሄደው ሁሉ የሰንቱን ገባር ጠፍ መሬት ገብረን እንዘልቀዋለን። የሄደውንም ገባር ከሄደበት ተከታትለን እያመጣን በግድ ለመመለስ እንችልም ባለጉልቱም ይከለክለናል። ስለዚህ እጥብቀን ተቸግረናልና ጠፉን መሬት ቢፈልጉ ገባሩ ጥሎት የሄደውን እናስረክባለን በሄደው ገብሩ ተብለን እንዳንያዝ። ደግሞም አሁን ያለውም ጨርሶ እንዳይጠፋ በየጊዜው የሽለቃና መልከኛ ያሳደገውና የጨመረው ግብር እንዲፋቅልን እናመለከታለን ብለው በየጊዜው የተጨመረውንም ግብር በዝርዝሩ አጽፈው የሰጡትን ደጋግመው እንበው ይኸን እንድታሰቡበትና እንድትመከሩበት ስለዚሁም የወሰናችሁትን እንዲውቀው ብለዋል ጃንሆይ [ቀ.ኃ.ሥ.] ብለው አመለከቱን። ነገሩን ሰምተን ጥቂት ዝምታ ከሆነ በኋላ እንዳንዶች መኪንንቶች መናገር ጀመሩ። እነሱም የበላተኛውን ወገን የመልከኛና የሺእለቃውን እበል ለመንከት የተጨመረውንም ግብር ዝቅ ለማድረግ እጅግ ፈርተው መልከኛው ደግሞ እበላችንን ከለከላችሁ ብሎ ይነሳብናል የሚያስቸግር ነገር ነው እያሉ ተናገሩ፤ ደግሞ ጥቂቶችም መሬቱን እየለቀቁ የሚሄደውን ገባር ያው መልከኛው እየፈለገ እ[የ]ተከታተለ እየያዘ ይመልሰውና ያስገብርው በያንዳንዱ አገርስ እንደዚሁ ያለ ደምብ አለ የለጥይ። በንደዚሁ ያለው ባላባት መያዙ ይቅር። አሉ። እኔም በተራዬ ሁሉንም ከዳመጥኩ በኋላ ነገሬን ስጀምር ሁሉም ዝም ብለው አዳመጡኝ። የተናገርኩትም በሐረርጌ ወገን ያለው ገባር አስተዳደሩ ከዚህ ከተነገረው ልዩነት ስለሌለው መጀመሪያ የዚያን እኪሆን ነበር። በሐረርጌ ገባር መሬቱን ጥሎ ቢሄድ መልከኛው እራሱ መሬቱን ቢያርሰው ወይም ሌላም እራሽ አጋዝቶም ቢሆን የሚገኘውን (ይበላል) ይወስዳል እንጂ ገባር አልችልም ከለ እንኪን ተሰደና እዚያውም አገር ለገር አስታውቶ ለቶ ቢቀመጥ የሚነከው የለም። የተወሰነውም ዓመት ሳይደርስ እንኪን ወደ መሬቱ ለመመለስ ፈልጎ በፈቃዱ ቢመለስ ገብቶ አለችግር መያዝ ይችላል።

ስለዚህ ሰው የሚገብረው ለኑሮውና ለትዳሩ ሲል መሬት ይዞ ቤት ሰርቶ ሚስት አግብቶ ልጅ ወልዶ ተቀመጠበት እንጂ። የማይችለውን ዕዳ ሊከፍልበት አይ[ደ]ለም።

ደግሞስ ይኸንኑ መሬቱን ዕዳውን አልችልም ብሎ ደህይቶ ቢሰደድ የግድ እየተፈለገ የሚያዘው ምን ባደረገ ነው። እስኪ እራሳችን እናስበው ሰው የሚወደውን ቤቱን እየርበታለሁ ያለውን እርስቱን። እንዲኖር የሚረዳውና የሚደገፈው ዳኛ በማጣት። ይኸው በየጊዜው የተጠመረበትንና ያደገበትን ጽር አቅርበልን እናያለን። ይኸን ያለ መንግሥት ፈቃድ የተጠመረውን ለመቀነስና ለማሻሻል መከራ መስሎ ይታያችኋል። በሳተኛውን በመፍራት ከዚህ ለማዳን የማይቻል ሲመስላችሁ። ድኃውን ከተሰደደበት አብርር መያዝና የግድ ግብር ማለት ትልቅ የግፍ ግፍ ነው። ብየ ከተናገርኩ በሰተኋላ። ቀጥዬ ይልቅስ እኔ እሳቤን ላመልክታችሁ የምሸው እውነተኛው ነገር። ለመንግሥቱም ሆነ ለባላገሩ። ታላቅ እንቅፋት ሆነን ለማሻሻል ያስቸገርንው እኛና እኛን የመሰለው ሹማምንት ሁሉ ነን። ምክንያቱም ከመንግሥት ደሞዝ እንቀበላለን። አገርም እየገዛን የገባሩን ግብር እንወስዳለን። ደግሞም በዚሁ ላይ ብዙ ሰፋፊ መሬት እርስት እያልን እየያዝን መቶውን ጋሻ ባምስት ሸማ። አምሳውን ጋሻ በሶስት ጉንደ ማር እየሆነ ብዙውን ሰፋፊ መሬት ሁሉ ያለ ግብር ይዘን። እያወክን ባንድ ወገን በዚህ አኳሆን የመሬቱ ግብር ሁሉ እየጎደለ። በሌላ ወገን ደግሞ። በገባሩ ላይ በመጨመሩ ሊኖር አቃተው።

በሌላው መፍረድ እንድንችል እስቲ መጀመሪያ በራሳችን እንፍረድ ሌላው ነገር እንኳን ለጊዜው ቢቆይ። እርስት ብለን ያለደንበኛው ግብር የያዝነውን መሬት። እንደድኃው ገባር ልክ በየእንዳንዱ ጋሻ ግብሩን ተካክለን እንገብር። ይኸንኑም ብናደርግ ከባላገሩ ላይ የከበደውን ታላቅ የግብር ሸክም መቀነስና ማቅለል ይቻላል። ገባሩም ግብሩ ከቀለለ[ለ]ት በመሬቱ መኖር ይችላል። ደግሞ በየጊዜው በየሻለቃው ምክንያት እንዲጨመር መንግሥቱ የሚጠበቅበትን ደምብ ከስራለት መሬቱን ለቆ የሚሄድ ገባር ምንም ያህል አይገኝም። ግብሩም በሚሄድበት ሥፍራ ሁሉ ተመሳሳይ ስለሆነ። ይኸ የቀረበልን ነገር ትልቅ ነው። ዳር አገር በተባለው አገር ሁሉ። ባላገሩ አቅም እያነሰው ነው እንጂ በዚህ በቀረበው አቤቱታ አይነት። ወሬውን እንደምንሰማው ያልደኸየና ያልተቸገረ አገር አይገኝም። ይኸውም በብርታት ቶሎ የሚድንበት ነገር ካልተሰራ። ይኸ አሁን የተፈራው በሳተኛ አገሩን ፈጽሞ ከደኸየ በኋላ የሚበላው ሲያጣ እንደገና መንግሥቱን እያስቸገረ የከፋ ነገር ሳይሆን አይቀርም። አሁን እንኳን የተመቻቸው ሹማምንቶች አገር ሲሰሙኑ ይኸ ያልተበላ አገር ነውና ስጡን ይላሉ ይባላል። ብዬ ነገሬን እንደጨረስኩ።

እዚያም ከነበሩት አንዳንድ ትልልቆች መኳንንቶች እፃ የአደሚን እርስት ሁሉ ልትነቅል የማይሆነውን ነገር እያሉ አንድ ጊዜ ነገራቸውን አወረዱብኝ።

ከልጅ አግሮቹ ወገን ግን እንዳንደቹ ምንም ቢያንሱ የኔኑ አይነት አሳብ የመሰለውን ተናገሩ። በዚሁ ስንጨቃጨቅ ያንለት ሰዓቱ

ደርሰ ተለያየን። ሁለተኛም በዚሁ ነገር የተነጋገርንበትና የተፈጸመ እኔ የማውቀው የለም። እንደመሰለኝም ለእቤት ባዮቹ መልስ ያህል ምንአልባት ጥቂት ነገር ያደረጉላቸው ይኖር ይሆናል።

ዛሬ የምናየው የእርስ በርስ ጦርነት የኢትዮጵያ አዲስ ታሪክ አይደለም። ኢትዮጵያ በረጅሙ ታሪኳ ሁሉ ያለ እንዳች እርስ በርስ ጦርነት አንድ መቶ ዓመት ኖራ እንደሆን ያንን ዘመን ለማወቅ እንፈልጋለን። አልፎ አልፎ «በዚህ ዓመት ንጉሡ ከመደናው አልወጣም» ከሚለው በቀር ታሪክ ነገሥቱ የሚነግረን በየዓመቱ ንጉሡ እለዚያም የጦር አበጋዞቹ የዘመቱትን ዘመቻና ያገኙትን ወይም ያጡትን ድል ነው። በጦርነት ጊዜ ገበሬው ሳይቀር ወታደር ይሆናል፤ ያልዘመተ በዐዋጁ መሠረት ርስቱ ይነቀላል። ዘመቻውም በእርሻ ወራት ከሆነ መሬቱ ጦሙን ያድርበትና እሱም ከዘመቻ በሰላም ከተመለሰ እንደመሬቱ ጦም አደሪ ይሆናል።

በዛሬው ዘመን ለዘማች ሠራዊት አስፈላጊውን ስንቅ የሚያቀርብለት የስንቅ አቅራቢ ክፍል አለው። በኢትዮጵያ ታሪክ ግን እስከ ሀያኛው መቶ ዓመት ድረስ ወታደሩ ስንቁን የሚያገኘው ከሰላማዊ ሕዝብ እየዘረፈ ነበር። በዚህ ሁኔታ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ወታደር ከአንድ ጠቅላይ ግዛት ወደሌላው በአገሩ ሲጓዝ ለምሳ ባረፈበት በታ ሁሉ ያለውን ሕዝብ ያደኽያል፣ ያስርባል። ከሁሉም የሚያሳዝነው ገበሬው ለዘር የከተተው ጥራጥሬና ማረሻ በሬዎቹ ሳይቀሩ ይበሉበታል። እንዲህ ያለ ፍርጃ የመጣበት ገበሬ ከቤተ ሰቡ ጋራ በረኀብ እቃስቶ ከመሞት ወይም ክብሩንና ኩራቱን ዋጥ አድርጎ ወደሌላ አውራጃ በለማኝነት ከመሰደድ በቀር ብዙ ሌላ ምርጫ አይኖረውም። ለምሳሌ በ1888 ዓ/ም በዓድዋ ጦርነት ጊዜ የኢትዮጵያው ጦር የኢጣሊያ ወራሪዎችን ለመውጋት ዓድዋ እንደደረሰ አልተዋጋም። የኢትዮጵያ ወታደሮች ሲቀርቡላቸው ተደብቀው ለማጨድ ጣሊያኖች ዓዲግራት ላይ ከዘጋጁት እርድ ውስጥ ገብተው ይጠባበቁ ነበር። አጼ ምኒልክ ይኸንን የጠላት ዘዴ አስቀድመው ስለወቁ ከምሽጉ ካልወጣ ውጊያ አልጀምርም ብለው ከአንድ መቶ ሺ በላይ የሚሆን ወታደር ይዘው ሦስት ወር ያህል ተቀመጡ። በዚህም ምክንያት እንኳን የተጫነው ስንቅ በዓድዋ አካባቢ ያለው እህል ስላለቀ ወታደሩ ጠላት መጠባበቁን ትቶ እስከ ሽሬ ድረስ እየሄደ ይዘርፍ ነበር። ጀኔራል ባራቲሪም የጣልያንን ጦር ከምሽግ አውጥቶ የኢትዮጵያን ጦር ለመምታት ሌሊቱን ወደ ዓድዋ ሲገሠግሥና ሲደናበር ያደረው የኢትዮጵያ

ሠራዊት ተርቦ እህል ፍለጋ ሄዷል የሚል ወሬ ደርሶት ነው። እውነትም ብዙ ወታደር ከጦርነቱ አልተሰተፈም። ጦርነቱ ሲያልቅ የትግሬ መሬት በሰውና በጭነት ከብት ተልቦ ስለነበር አፄ ምኒልክ ለትግሬው ገዢ ለልዑል ራስ መንገሻ እህል ከሰሜን ድረስ እንዲጫንላቸው አዘውላቸው ነበር። ራስ መንገሸና ሠራዊታቸው እህል ተጭኖላቸው ይሆናል፤ ሕዝቡስ?

ከላይ እንደጠቀስኩት ይኸንን ለምሳሌ አነሣሁት እንጂ እርስ በርስ የሚደረገው ጦርነትም የሚያስከትለው ረኀብ ይኸንኑ ዓይነት ነው። እንዲያውም ይበልጥ ይሆናል። በእርስ በርስ ጦርነት ጊዜ ተሸናፊው ወገን እንደዘሬው ሥርዓት ነጭ ጨርቅ በማውለብለብ ጦርነቱን አያቆመውም። ተሸናፊ ሲሸሽ፤ አሸናፊ ሲያባርር ሴቶች ሕፃናት ከብት ጉተራ ካለበት ይደርሳሉ። በዚያን ጊዜ «ጀግናው አሸናፊ» የተሸናፊውን ቤቱንና ጉተራውን አገሩን ሁሉ በእሳት ያቃጥልና ከብትና ባርያ ዘረፋና ምርኮ ይጀምራል። ታሪክ ጸሐፊውም የጦርነቱን ምዕራፍ «ወማኅረኩ ብእሲቶ ወውሉዶ ወእንስሳሁ ወቀተሉ ብዙኃ» በሚል ቃል ይደመድማል። በቅርቡ ጊዜም የጐጃሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በአፄ ዮሐንስ ላይ ማመፃቸው እንደተሰማ አፄ ዮሐንስ ወደ ጐጃም ዘምተው ነበረ። ሁኔታውን ከብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ <u>«የኢትዮጵያ ታሪክ»</u> እጠቅሳለሁ።

> ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም የአፄ ዮሐንስን መምጣት በሰሙ ጊዜ መተራ ወደሚባለው አምባ ወጥተው ተቀመጡ። አፄ ዮሐንስም የመተራን አምባ በመድፍ ለማፍረስ ቢሞክሩ በዚያ ዘመን የነበረው መድፍ እንደዛሬው ዘመን መድፍ በሩቅ ሄዶ ሥራ አይሠራም ነበርና አምባውን ለማፍረስ የማይችሉ ሆኑ። በዚህም ነገር እጅግ ስለተናደዱ አገሩን ኀጃምን ያጠፉት ጀመር። በሊላው ሰፍራ ይቅርና [የአገሬው ሕዝብ] ከመከራው የሚድን እየመሰለው ገንዘቡን እየያዘ በየቤተ ክርስቲያኑ እየተማጠነ ቢገባ [የአፄ ዮሐንስ] ወታደር በኃይል እየገባ ገንዘቡን እየቀማ እምቢ ያለውንም እየገደለው ይወጣ ነበር።

አፄ ዮሐንስ ሃይማኖተኛ ስለነበሩ ከደብዳቤዎቻቸው ባንዱ ውስጥ ስለዚህ ስለዘመቻው ሲጽፉ «በእኔም በድኃውም [በሕዝቡ ማለታቸው ነው] ኃጢያት እንደሆነ አይታወቅም አገሩን ሰጠፋው ከረምሁ» ብለዋል። በዚያን ጊዜ እንዴት አልቃሽ የገጠመችላቸው አንድ በታ ተጽፎ ማንበቤ ትዝ ይለኛል።

በላይኛው ጌታ በባልንጀራዎ
በቅዱስ ሚካኤል በጋሻ ጃግሬዎ
በጽላተ ሙሴ በነጭ አበዛዎ
ጎጃምን ይግሩት ፈረም እንልዎ

የዘመቻ ተስፋው ዘረፋ ስለሆነ ወታደሩ ተው ቢሉትም በቀላሉ እሺ አይልም። ቅል ባገኝ ወታደርገንና የኔ ብጤ ደሀውን እንርሰ። ሁለቱም ወገኖች ዘረፋ ብናገኝ እያሉ ያለእዘዝ ያለእለቃ የሚዘምቱ ናቸው።

ሁኔታውን አተኩሮ ያየ ሰው አልፎ አልፎ የዝናም እጥረት ከኢትዮጵያ ጋር አብሮ የኖረ ነው ለማለት ይቃጣል። በእንግሊዝኛ ሉሲ በአማርኛ ድንቅነሽ (እሷን ቢጠይቋት ግን የራሷን ቋንቋ ስም ትመርጥ ይሆናል) የተባለችው የጥንት ሴት በተገኘችበት አካባቢ የብዙ ሰው ዐፅም የተገኘበት ምክንያት ወይ የመቃብር ቦታ ወይም ሰው በአንድነት በረኀብም ሆነ በተስቦ ያለቀበት ቢሆን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስንመለከት በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፵፩ ላይ በፈርዖናውያን ዘመነ መንግሥት በግብፅ የሰባት ዓመት ድርቅ እንደነበር እናነባለን። ግብፅ የምታርሰውና ሰብሏን የምታመርተው በዐባይ ወንዝ መለከተኛነት ከኢትዮጵያ በሚሄድለት ዓፈርና የዝናም ውሀ መሆኑ የታወቀ ነው። በውሀ እጥረት ምክንያት እግብፅ የሰባት ዓመት ረኀብ ከገባ በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ ላይ ሰባት ዓመት በማከታተል አልዘነበም ነበር ማለት ነው። ድርቅ የሕዝብ እልቂትና ፍልሰትን ስልሚያስከትል አሁን ለይተን ባናውቀውም በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ የጠፉም የወረሩም ነገዶች መኖራቸውን ለመገመት ይቻላል። የጥንት ግብፃውያን ዐባይ እየደረቀ ሲያስቸግራቸው ወንዙ ወይም አምላኩ የተቆጣቸው እየመሰላቸው ምሱን በመት በመት እንዲት ቆንጆ ልጅአገረድ እየሠውለት ይለማመጡት ነበር። እንግዲህ የዐባይ ወንዝ በዚያን ጊዜ ሁሉ ውሀው መቀነሱ የሚያሳየው በኢትዮጵያ የዝናም እጥረት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እንደያውም ከዚያ በፊት ሁሉ የነበረ መሆኑን ነው። የአክሱም አወዳደቅ እንዴት እንደሆነ አንዳንድ አሳቦች ተሰንዝረዋል። ከነሱም ውስጥ የመሬት መንቀጥቀጥ፤ የሌለ ሃይማኖት መነሣት ይገኙበታል። በኔ አስተያየት ድርቅና ተስቦም ሊታከሉ ይገባቸዋል።

የጥንት ግብፃውያንን ዘመን አልፈን ወደክርስቲያኑና ወደእስላሙ ዘመን ስንመጣ በተለይ ከዓሥራ ሁለተኛው እስከ ዓሥራ አራተኛው መቶ ዓመት እግብፅ የተጻፉትን የማርያም ታምር በግዕዝ ተተርጉመው ስናነብ በየጊዜው

የዓባይ ወንዝ ውሀ መቀነስ ይህም በሀገሬቱ ላይ የእህል እጥረትን ማስከተሉ በግልጽ ይታያል። በየጊዜው የተነሡ የኢትዮጵያ ቅዱሳን ታሪክም (ገድላቸው) በየዘመናቸው ተስቦ (ሕማመ ብድብድ) እና ረኀብ (አበረ እክል) ተደጋግሞ መነሣቱን ይናገራል።

ረኀብና ተስቦ አብዛኛውን ጊዜ አብረው ይሄዳሉ። ተስቦ በሚል አጠቃላይ ስም የምጠራው ማንኛውም ተላላፊ በሽታ ነው። ግዕዙም እንደዚሁ በጠቃላይ «ብድብድ» ይለዋል። እሱም በሕሊችን እንደሚያምንበት ኃጢአታችን ሲበዛ እግዚአብሔር ለመቀጮ የሚያመጣብን መቅሠፍት ነው። ተስቦ አርፈን ባለመቀመጣችን ራሳችን በራሳችን ላይ የምናመጣው መዐት መሆኑ ነው። ድርሳነ ሚከኤሉ እንደሚያስተምረን ማንኛውም በሽታ (ብድብድም ሆነ ወይም ሌላ ዓይነት) የሚመጣው ከአጋንንት ነው። በዚህ እነጋገር የታመመ ሰው ከፈለገ ጋኔን ይዘኛል ማለት ይችላል። በሽተኛን ወደ ጠበል የምንወስደው ስለዚህ ነው። አጋንንት ሰይጣናት አይደሉም። ሰይጣናት እምሰክን በመደፈር የወደቁ መላእክት እንደመሆናቸው አይጋቡም አይበዙም አይሞቱምም። ሥራቸውም ሰውን ኃጢአት ማስገባት <u>ብቻ</u> ነው። አጋንንት ግን፦

> ሥጋ የሌላቸው በውሀና በየብስ (በደረቅ መሬት) የሚኖሩ ናቸው። እነሱ እንደሰው ይጋባሉ ይረባሉ፤ በመጨረሻም ይሞታሉ። መልካቸው እንደ ሰው ነው፤ እውሬ እባብ ወይም ሌላ ነገር የሚመስሉም አሉ። ሰውን ኃጢአት ማሠራት የነሱ ጉዳይ አይደለም። ግን በሽታ ይሆናሉ፤ ለሞትም ያደርሳሉ። ከነሱ ማሀል ብድብድ የሚሆኑ አሉ፤ ንዳድ የሚሆኑም አሉ፤ ሌላ ሌላ በሽታ የሚሆኑም አሉ። በዓለም ላይ ያሉነሱ እንዳችም በሽታ የለም። ሆኖም ያለልዑል (እግዚአብሔር) ፈቃድ መግደል አይችሉም። ቢፈልጉ (የማንንም) ነፍስ መያዝ ይችላሉ። የዚያች ነፍስ ውቃቢ መልአክ ካልተጨመረበት ግን ሊያወጧት አይችሉም።

## መካከለኛው ዘመን

የግብፅ ድርቅ ከኢትዮጵያ አየር ሁኔታ ጋር የተያያዘ መሆኑን ከተቀበልን ከዚህ በታች ያለውን ካልታተመው <u>ከመጽሐፈ ሐዊ</u> ያገኘሁትን ልጠቅስ እወዳለሁ፦

ከነ በመዋዕለ ቅዱስ ጳኩሚስ ረኀብ ወኃጥአ እኃው ሥርናየ ወተኃጥአ እክል ውስተ ኩሉ ምድረ ግብጽ።

በቅዱስ ጳኩሚስ ዘመን ረኀብ ሆነ። መነኮሳቱም ስንዴ ተቸገሩ፤ በግብፅ ምድር ሁሉ እህል ጠፋ።

የመነኵሴዎች አብር መኖርን ያመጡ ቅዱስ ጳኵሚስ የኖሩት ከ290 እስከ 346 ዓ/ም ገድም ሲሆንና በሰቸውም ዘመን ግብፅ ረኀብ ከገባ በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያም ሳትራብ አትቀርም። ወደኋላው ዘመን በግብፅ ረኀብ እንደገባ የሚያስረዱ የግዕዝ መጻሕፍት ብዙ ናቸው።

በኢትዮጵያ ላይ በየጊዜው የደረሰውን ችግር በቀጥታ ወደሚመስከሩት ማስረጃዎች እናተኩር። ከነዚህም አንዱ ስንክሳር ነው። ስንክሳር ጻድቃን በዕለተ ሞታቸው በየዓመቱ የሚነበብላቸው መታሰቢያቸው ነው። እስንክሳሩ ውስጥ ያለው ከግብፅ በትርጉም የመጣልን የሦስት የግብፅና የኢትዮጵያ ሊቃነ ጳጳሳት ታሪክ ኢትዮጵያ በረኀብና በተስቦ እንደተቀጣች ያመለክታል። ሦስት ጊዜም መቀጮው ከግብፅ የሚመጡልንን ጳጳሳት ስለበደልን ነው።

የመጀመሪያው በያመቱ በጥቅምት 23 ቀን ከሚነበበው ከሊቀ ጳጳሱ ከአቡነ ዮሳብ (831-850 A.D.) ታሪክ ውስጥ ይገኛል፦

በዚህ አባት ዘመን የኢትዮጵያው ንጉሥ (ለሊቀ ጳጳሱ) እንደህ ሲል መልክት ላከባቸው፤ «ሊቀመጡበት የተገባዎንና መንግሥቱም በጸጋው የጸናበትን የወንጌላዊውን የማርቆስን መንበር እጅ እነሣለሁ። ራርተውልኝ ጳጳሳችንን አባ ዮሐንስን (መልሰው) እንዲልኩልን እለምንዎታለሁ። ከሀገራችን ሰዎች ከቅዱሱ ወንጌላዊ ማርቆስ ወንበር ብርሀን ተሰስተው እግራቸውን እሸህ ከተሞላበት መንገድ ላይ ያሰረፉ አሉ። እነዚህ ጳጳሳችንን አባ ዮሐንስን አባረሯቸው። ስለዚህም በላያችን በሀገራችን ላይ ከፍ ያለ ስቃይ ደረሰብን።

ሰዎቻችንም ሁሉ በተስቦ ሞቱ፤ ከብቶቻችንም አለቁ። በሀገራችን ላይ እንዳይዘንም እግዚአብሔር ሰማይን ከለከለው። ጠላቶቻችንም ተነሡብን፤ አሸነፉንም። (ይህ ሁሉ የደረሰብን) የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለማስን ነው።

ሁለተኛው በኅዳር 12 ቀን ከሚነበበው ከሊቀ ጳጳሳቱ አቡነ ፊለታዎስ (979-1003 A.D.) መታሰቢያ ውስጥ ተጽፏል፦

በዚች ዕለት ደግሞ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ አባት ፊላታዎስ አረፉ።... በሳቸው የሹመት ዘመን የኢትዮጵያው ንጉሥ ለኖባው (ለሱዳኑ) ንጉሥ ለጊዮርጊስ ላከበት። (እንዲህም) አለው፤ «ከእኛ አስቀድመው የነበሩ ንጉሦች በሠሩት (ክፉ) ሥራ እግዚአብሔር በኛ ላይ ተቆጥቷል። ይኸውም በጳጳሱ በአባ ጴጥሮስ ጉዳይ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመጣሳቸው ነው። በሊቀ ጳጳሳቱ በአባ ቆዝሞስ (933 A.D. ያረፉት) ዘመን ጳጳሱን ከሹመታቸው አባረው በሳቸው ምትክ ሚናስ የሚባል ውሸተኛ ሾመው ነበር። እነሆ (ከሳቸው ጀምሮ የተሾሙት) ስድስቱ ሊቃነ ጳጳሳት አንድም ጳጳስ አልሾሙልንም። ስለዚህ አገራችን ጠፋ። ሰውም ከብቱም ሁሉ በረኀብና በተስቦ አለቀ። ጠላቶቻችንም ተነሡብን ከሀገራችን ሰዎች ብዙዎችን ማረኩ። ከተሞቻችንን ዘረፏዋቸው። ዝናም እንዳይጥል ተከለከለ መሬትም ፍሬዋን ነፈገች ጠላቶቻችንም ከተሞቻችንን አቃጠሉ፤ ቤተክርስቲያኖቻችንንም ዘረፏቸው። እኛንም ከሀገር ወደሀገር ያባርሩናል። ስለእግዚአብሔርና ስለእርቶዶክስ ሃይማኖት (ብለህ) የጭንቄ ተካፋይ እንድትሆን እለምንሃለሁ። ወደ አባታችን ወደ ግብፁ ሊቀ ጳጳሳት ወደ አባ ፊላታዎስ ደብዳቤ ጽፈህ እኛንና አገራችንን ስለእግዚአብሔር (ብለው ከግዝቱ) እንዲፈቱን ይኸንንም የወደቀብንንም ጭንቀትና መከራ እግዚአብሔር ከኛና ከአገራችን ላይ ያስወግድልን ዘንድ እንዲጸልዩልን፣ ምሕረትም አድርገው ጳጳስ እንዲልኩልን _(እማልደን)።»

እነዚህ ሁለት ጥቅሶች የጉዳትን መነሻት ሳያመለክቱ አይቀሩም። ከዓሥረኛው መቶ ዓመት ወዲህ ስለ አክሱም ዘመነ መንግሥት የሚናገሩ መጻሕፍት አልተገኙም። ቀጥሎ የሚጠቀሰው ማስረጃ የሚያመለክተው በዛጔ ዘመነ መንግሥት በተለይም በዓሥራ ሁለተኛው መቶ ዓመት ላይ ኢትዮጵያ በመላዋ በረኀብና በተላላፊ በሽታ እንደተሰቃየች ነው። ጊዜው አሁንም በትክክል አይታወቅም ግን ዳግማዊ አቡነ ገብርኤል የግብፅና የኢትዮጵያ በትሪያሪክ በነበሩበት ጊዜ ስለሆነ በዘመናቸው በ 1131-1145 (A.D.) ነው። በዚያን ጊዜ የነበረው የኢትዮጵያ ንጉሥ ለሰፊዋ ኢትዮጵያ አንድ ጳጳስ ብቻ የማይበቃት መሆኑን ተረድቶ፤ ግብፃችም ሌላ ተጨማሪ ጳጳስ ቢጠይቅ እንደማይልኩለት ስለሚያውቅ የዚያን ጊዜውን የኢትዮጵያ ጳጳስ አስጠርቶ

የሰቸው ብጤ ሌላ ጳጳስ እንዲሾሙ አስገደዷቸው። በትሪያርኩ አቡነ ገብርኤል ይኸንን በሰሙ ጊዜ የግዘት (ውግዘት) ቃል ከግብፅ ላኩ። ንጉሡ ግዝቱን ስለተሳለፈ በሱና በሀገሩ የደረሰውን ቅጣት ስንክሳሩ በሚያዚያ ፲ ቀን ንባቡ እስፍሮታል፦

ወሶበ በጽሐት ይእቲ መልእክተ ግዘት ውዕየ ጽርሑ በእሳት ወኮነ ውስተ ብሔሩ ረኃብ ወብድብድ ወተእኅዘ ዝናም ከመ ኢይዝንም ሰዕሌሆሙ ወበጽሖሙ ምንዳቤ ዓቢይ እስመ ንጉሥ ተአደወ ትእዛዘ እግዚአብሔር።

ያቺ የግዝት ደብዳቤ በደረሰች ጊዜ ቤተ መንግሥቱ በእሳት ተቃጠለ። በሀገሩም ረኃብና ተስቦ መጣ። ዝናምም እንዳይዘንምላቸው ታገደ። ታላቅ ጭንቅም ደረሰባቸው፤ ንጉሡ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጥሷልና።

ከዚህም ዘመን ጥቂት ቆየት ብሎ፤ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገና የዓመት ከሦስት ወር ሕፃን በነበሩበት ጊዜ (በ1208 ዓ/ም ገድም መሆኑ ነው።) በሸዋ ረኀብ ገብቶ ነበር። ገድላቸው «ኮነ ዐቢይ ረኀብ ውስተ ኵሉ ብሔረ ሸዋ» ይላል። በሽታውም ሆነ ረኀቡ በኢትዮጵያ የቱን ያህል እንደተስፋፋ አይታወቅም። ግን የሰቸው ተማሪ የነበሩት አቡነ ዜና ማርቆስ በተራቸው በሚያስተምሩበት ዘመን በሸዋ ረኀብ ገብቶ እንደነበረ ገድላቸው ይናገራል፦

ወእምድኅረ እምኑ ወተጠምቁ እሉ ሕዝበ ተንባለት ዘሀገረ ሞረት ወዘምድረ ወግዳ ወተጉለት ኮነ ብዙኅ ረኀብ በዓመት።

እነዚያ የሞረት፣ የወግዳ፣ የተጉለት የእስላም ወገኖች ከአመኑና ከተጠመቁ በኋላ በዓመቱ ብዙ ረኀብ መጣ።

እራሳቸው ትልቁ የኢትዮጵያ ጻድቅና የሃይማኖት መሪ አቡነ ተክለሃይማኖት በዘጠና ዘጠኝ ዓመታቸው የሞቱት በተስቦ ነው። በዚያን ጊዜ (1306 ዓ/ም ገደማ) እሳቸው በነበሩበት አካባቢ ተስቦ ገብቶ በመሠረቱት ገዳም በደብረ አስቦ (የዛሬው ደብረ ሊባኖስ) ከሚኖሩት ተከታዮቻቸው አብዛኞቹ አለቁ። ገድላቸው ጻድቁ የሞቱበትን ሁኔታ ሲገልጽ፦

ወበይእቲ ዕለት በእ ሕማመ ብድብድ ኀቤሆሙ ወተእኅዙ መነኮሳት ... ወሶበ ተእኅዘ አቡነ ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት በዝንቱ ደዌ ተጋብኡ ኀቤሁ ኵሎሙ ደቂቁ።

በዚያች ዕለት የተስቦ በሽታ መጣባቸው። መነኩሴዎቹም (በበሽታው) ተያዙ.... አባታችን ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት በዚሁ በሽታ በተያዙ ጊዜ (የመንፈስ ቅዱስ) ልጆቻቸው ሁሉም ወደሳቸው ተሰበሰቡ። ይላል።

የአቡነ ኤዎስጣቴዎስ ገድልም ወደ 1330 ዓ/ም ገደማ የእህል እጥረት እንደነበር ሲያመለክት «ወኮነ በውእቱ መዋዕል አበረ እክል ውስተ ኵሉ አህጉር ዘአውደሙ» በዚያ ጊዜ በአከባቢያቸው ባሉ አገሮች የእህል መታጣት ሆኖ ነበር ይላል። አቡነ ኤዎስጣቴዎስ የሰራዬ ሰው ስለነበሩ «በአከባቢያቸው» የሚለው በሰራዬ አከባቢ ያሉትን አገሮች ነው። ሆኖም ድርቁ በኤርትራ ብቻ ነበር ለማለት አይቻልም።

የደብረ ቢዘኑ (ኤርትራ) አቡነ ዮሐንስ (1362-1440 ዓ/ም ?) ታላቅ ጻድቅነታቸው የታወቀው፤ በልዑል እግዚአብሔር ዘንድ ተሰሚነት ባለው ጸሎታቸው ሰማይን ለጉመው ሦስት ዓመት ሙሉ ዝናም በማስቀረት የኢትዮጵያን ሕዝብ በመገሠጻቸው ነው። በዚህም ምክንያት እሳቸው ሰማይን እንደለጐመ እንደነቢዩ ኤልያስ ገዳማቸው ደግሞ እንደ ኤልያስ አገር እንደ ቴስቤን ተመስሎ እስከዛሬ ባመት ባመቱ በበዓላቸው እንዘምርላቸዋለን፦

ሰላም ለከ ገሣጼ ሕዝብ አብዳን፤
በከሊእ ዝናም ወጠል መጠነ ፫ ዘመን።
እንበይነ ዝንቱ ኃይልከ ኃይለ እጥናን፤
ተተርጐመ በኤልያስ ዮሐንስ ካህን።
ወቢቴስቤን ተመሰለት ቢዘን።

መጥፎን ሕዝብ ሦስት ዓመት ያህል ዝናምና ርጥበትን በመንሣት
የምትገሥጽ ሆይ፣ ሰላም ላንት ይሁን።
ስለዚህም ስለ እምላከዊ ኃይልህ፤
(ስምህ) ካህን ዮሐንስ ኤልያስ ተባለ።
(ደብረ) ቢዘንም በቴስቤን ተመሰለች።

በዚያን ዘመን ተከታታይ ድርቅ ብቻ ሳይሆን ተስቦም ተነሥቶ የደብረ ቢዘን መነኮሳት ሳይቀሩ አልቀዋል።

በአፄ ዳዊት ዘመን (1375-1406 ዓ/ም=1382-14 A.D.) በመላው ኢትዮጵያ የተዘረጋ ተስቦ የተነሣ ይመስላል። ሌሎቹን (በዐረብ ታሪክ ጸሐፊዎች የተጻፉትንም) ማስረጃዎች ልተውና በናታችን በቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ገድል የተጻፈውን ልጥቀስ። ተስቦው በዚያን ጊዜ አውሮፖን ያቃጠለት «ጥቁር

ሞት» የተባለው ሳይሆን አይቀርም።

ሁለተኛም እናታችን ክርስቶስ ሠምራ እንዲህ አሉ፤ ከዕለታት አንድ ቀን ተስቦ (ብድብድ) በዓለም ላይ ከዳር እስከ ዳር ተለቀቀበትና ብዙዎች ሰዎች አለቁ፤ ተጨረሱ። በቤታቸውም ለቅሶና እየየ ሆነ። በዚህ ሁኔታ ፫ ዓመት ቆየ። አንድ ቀን በዋሻየ ሳለሁ ለሰው ልጆች ሁሉ ከእግዚአብሔር ምሕረት እለምን ዘንድ በጎ አሳብ መጣልኝ። በዋሻየ ብቻየን (እየጸለይኩ) ሳለሁ፤ በሩም ዝግ ነበር፤ ከተስቦ ሠራዊት አንዱ ወደኔ መጣና በዋሻየ በራፍ ቆሞ አለ። በበራፉ ላይ ሲቀመጥ (በሯ) በግዛ እጇ ተከፈተችለት። ወዲያው እንዲህ ሲል መልስ ሰጠኝ፤ «የእግዚአብሔር ወዳጅ ክርስቶስ ሠምራ፤ እንደምን አለሽ?» እኔም ወዲያው «ሰላምታህን እቀበል ዘንድ አንተ ማነህ?» ስል መለስኩለት። እሱም እንዲህ አለኝ « ስሜ በድል አበፈር ነው። አመጣጤም ከሩቅ አገር ነው።» እኔም፤ «እኔ ወዳለሁበት ለምን መጣህ?» አልኩት። «ካንቺ ጋር እንድጫወት» አለኝ። «በላ እንጫወት» (አልሁት) በዚያን ጊዜ ቢለዋ ብድግ አደረገና የበሬ ስጋ ቆረጠ። ከበራፉ ላይ የተኙ ሁለት ውሾች አሉት፤ ያንን በቢለዋ የቆረጠውን ሥጋ ለነዚያ ውሾች ማለሳቸው። ወዲያው አንዱ ውሻ (ሥጋውን) እንሥቶ ይበላ ጀመር። ሁለተኛው ውሻ ግን አልበላም። እኔም (ለውሾቹ) ጌታ እንዲህ አልኩት፤ «አንዱ ሲበላ ሌላው ለምን አይበላም?» በዚያን ጊዜ ያ ዝም ብሎ ተኝቶ የነበረው ውሻ በሰው ቋንቋ አነጋገረኝ። እንዲህም አለኝ፤ «እንደሰው ልጅ ጓደኛየን እቀማለሁ እንዴ? እኛ የጌታችንን ትዛዝ እንጠብቃለን፤ እንፈራለን እንንቀጠቀጣለንም።» በዚያን ጊዜ «ይኸ ውሻ እንዴት በሰው ልጅ ቋንቋ ይናገራል!» እያልኩ አደንቅሁ ተገረምኩም። የነዚያ ውሾች ጌታም (እንዲህ ሲል) መለሰልኝ፤ «ውሾች እንዲህ በሰው ልጅ ቋንቋ ይናገራሉ። እኛ የፈጣሪያችንን ትእዛዝ እንጠብቃለን፤ እንደናንተ ከአምላካችን ትእዛዝ አንወጣም። ዝሙት አታድርጉ ይላችኋል፤ እናንተ ዝሙት ታደርጋላችሁ። አትስረቁ ይላችኋል፤ እናንተ ትሰርቃላችሁ። አትግደሉ ይላችኋል፤ እናንተ ትገድላላችሁ። እንደዚህ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከጣሳችሁ መዓቱን በምድር ሁሉ ይለቅባችኋል። የእግዚአብሔር ወዳጅ ክርስቶስ ሠምራ፤ ስሚ ልንገርሽ ከፈጣሪያችን አንዳች ትእዛዝ ሲወጣ የምንታዘዘው በሊቀ መላእክት ሚካኤል (አማካይነት) ነው፤ እንፈራለን እንንቀጠቀጣለን። እሱም እንዲህ ይለናል፤ «ሰውን ሁሉ ትገድሉ ዘንድ ከገራችሁ ውጡ» ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ይኸንን ሲለን እንፈራለን እንንቀጠቀጣለን። በዚያን ጊዜ (የኛ) መኳንንትና መሳፍንት ከንጉሣቸው ዘንድ ይሰበሰባሉ፤ ከንጉሡም ጋር ይማከራሉ። ንጉሡም ለመኳንንቱ፤ «ሂዱ ከሚስቶቻችሁ ጋር ተመካከሩ፤ ተመካከራችሁም እግዚአብሔር በመዓቱ እንዳይቀጣን ቶሎ እንውጣ» ይላቸዋል። በዚህ ጊዜ መኳንንቱ ቶሎ ይወጡና ከሚስቶቻቸው ጋር ይመካከራሉ። ወዲያውም ንጉሡና መኳንንቱ ፈጥነው ይወጣሉ። ከኛ ማህል ማንም ወደኋላ የሚቀር የለም፤ ወጣቶችም ሕፃናትም ቢሆኑ። ስሚ ልንገርሽ ክርስቶስ ሠምራ፤ እግዜር ካዘዘን በታ ስንደርስ ንጉሣችን (ከገሬው) ንጉሥ ቤት ይገባል፤ መኳንንቱም እንዲሁ ከመኳንንት ቤት። ከኛ ማህል ከሊቀ መላእክት ሚካኤል ትእዛዝ የሚወጣ የለም። በዚያን ጊዜ እንደታዘዝነው እናደርጋለን፤ እንደናንተ (ትእዛዝ) አናፈርስም። ንጉሥ ንጉሥን ይገድላል፤ መኳንንትም መኳንንትን ይገድላሉ፤ ወጣቶች ወጣቶችን

ይገድሏሉ፤ ሕፃናትም ሕፃናትን ይገድሏሉ፤ ሴቶችም ሴቶችን ይገድሏሉ፤ ወንዶች ባሮች ወንዶች ባሮችን ይገድሏሉ፤ ሴቶች ባሮችም ሴቶች ባሮችን ይገድሏሉ። እንደዚህ በሥርዓት የቆምን ነን። አለእኩያው የሚገድል የለም። ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል፤ «(በቃ) ቶሎ ውጡ፤ ወደአገራችሁ ተመለሱ» ሲለን ወዲያውኑ ስንፈራ ስንንቀጠቀጥ እንወጣለን። ወደቤታችንም በሰላም እንመለሳለን።

እስከ ዕለተ ሞታችን እንዲህ እንኖራለን። ክርስቶስ ሠምራ፤ ስሚ ሌላ ነገር ልንገርሽ፤ ሰዎች (ስለኛ) «ውሀ ይወስዳቸዋል፤ ወይንም ኸብ ይበላቸዋል።» (ቢሉሽ አትመኚ።) ይኸ ሁሉ አይደርስብንም።» ይኸንን ተናግር በጣና ባሕር ላይ በእግሩ ሄደና ደብረ ዳጋ ደረሰ። ወዲያው እኔ ወደለሁበት ተመለሰ። በዚያን ጊዜ እንዲህ ሲል መለሰልኝ «እንግዲህስ ወዳገሬ እሄዳለሁ፤ ግን የእግዚአብሔር ወዳጅ ክርስቶስ ሠምራ ሆይ፣ በቅድስት ጸሎትሽ አትርሺኝ።» እኔም «በሰላም ሂድ» አልኩት።

በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት (1427-1460 ዓ/ም=1434-1468A.D.) በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው የተስቦ መቅሠፍት ቀደም ካሉት መቅሠፍቶች በይበልጥ ይታወቃል። የንጉሡ ታሪክ፤ አንድ ቤቴርጊስ ማርያም ስለሚባል ልዑል የተጻፈው ተአምረ ማርያምና በዚያን ጊዜ የነበሩ ቅዱሳን (በተለይም የነአቡነ ፍሬ ሚካኤል፤ ዘርአ አብርሃም) ገድሎች እየደጋገሙ እንሥተውታል። ታሪኩ እንዲህ ይላል፦

ንጉሡ እዚያ በታ (ደብረ ብርሃን) መኖርን ባራዘመ ጊዜ የተስቦ በሽታ በጣም እየበረታ ሄደ። ብዙዎችም አለቁ። የሚቀብራቸውም አጡ።

ታሪክ ጸሐፊው ንጉሡ ዘርአ ያዕቆብ ያወጣቸውን ሕጎች ሲዘረዝር ተስቦ የፈጃቸው ሰዎች እንዴት መቀበር እንዳለባቸው ያወጣውን ሕግ ያነሣል፦

ሰዎችንም ተሰቦ በገደላቸው ጊዜ ያገሩ ሕዝብ ሁሉ ተሰብስቦ ብትርና ጅራፍ በመያዝ ተለይተው የተጸለየበት ጠበል እየረጩ እንዲቀብሯቸው አዘዘ። (የቀባሪዎቹን) ስማቸውንም ማኀበረ ወንጌል ብሎ ጠራው። ብትራቸውንም በትረ ሙሴ (የሙሴ ብትር) አለው። እንደዚህ ያላደረገ፤ ሁሉም በየሀገሩ የሞተን ያልቀበረ ቤቱ እንዲዘረፍ ሀብቱ እንዲወሰድበት ለሹሞቻቸው ትእዛዝ አስተላለፈ።

ሕጉ የወጣው ከላይ እንዳየነው ሰው ቀባሪ እያጣ ሬሳው የትም ይወድቅ ስለነበር ነው።

በቴርጊሳ ማርያም ከንጉሡ ከዘርአ ያዕቆብ ልጆች አንዱ እንዲያውም አልጋውን የወረሰው በእደ ማርያም ሳይሆን አይቀርም። ስለዚህ ልዑል ከተጻፈው ተአምረ ማርያም ውስጥ እንዲህ የሚል ይገኝበታል፦

> በዚያን ዘመን ሊነገር የማይቻል የተሰቦ ሞት በሰው ሁሉ ላይ ሰፈነ… ከዚያም አንድ ቀን አንድ ሰይጣን የለከፈው ሰው ለአባቱ ያልሆነ ነገር አሳብቶበት መስፍኑ ይኸንን ልጅ (በተርጊሳ ማርያምን) ጠራው። በተርጊሳ ማርያምን እንዲጠራ መስፍኑ የላከው ይኸንኑ ያሳበቀበትን ሰው ነበር…። ልጅም እየተጣደፈ ተነሥቶ ተከተለው። ያ ሰው ግን በክፋት በጥድፊያ እያወቀ በወደመው፤ ተሰቦ ባለበት መንገድ ወሰደው… እመቤታችን ግን የመስፍኑን ልብ አራርታ ልጁን በደስታ ቃል አነጋገረው። ለበሽታውም (መከላከያ) መድኃኒት ሰጠው፤ «ጠጣ፤ እግዚያብሔር ለበሽታ እንዳይሰጥህ» አለው። …ንጉሡ (ልጁን) ከመጥራቱ በፊት አንዱ (የበቴርጊሳ ማርያም) ወንድም በተሰቦው ሞተ። ከመስፍኑ ዘንድ ከተመለሰ በኋላም ሌላው ወንድሙ በሆድ በሽታ (በተቅማጥ) ሞተ። በቴርጊሳ ማርያም ግን በመቤታችን በቅድስት ድንግል በ፪ ማርያም የጸሎት ኃይል ዳነ።… የተሰቦ በሽታ በመስፍኑ አደባባይ በየቦታው በጸና ጊዜ መስፍኑ ልጆቹን (ሌሎችንም) ወንዱንም ሴቱንም ጸሎተ ምህላ (እግዚእታ) ወደልዑል እግዚአብሔርና ወደ እመቤታችን ወደ ቅድስት ድንግል በ፪ ማርያም እንዲያቀርቡ አዘዘ። በቴርጌሳ ማርያም ግን በአባቱ በመስፍኑ አደባባይ ሁል ጊዜ ከወንድሞቹ ጋር ደጅ ይጠና ነበር። ከበቴርጌሳ ማርያም ወንድሞች አንዱ አብሮት እያለ ሞተ…

ጻድቁ ሕፃን ቅዱስ ቂርቆስ (የውጭ ሰው ነው) በሰማዕትነት ሲሞት እግዚያብሔር የሰጠው ቃል ኪዳን «ቤተ ክርስቲያንህን ከሠራ (ሰው) ዘንድ ተሰቦ አይምጣ፤ በ(ሀገሩም) ውስጥ የውሀ እጥረትና የእህል እጦት አይድረስ» የሚል ስለሆነ አፄ ዘርአ ያዕቆብ ይኸንን በመተማመን (ወይም የሚያደርገው ቢያጣ) የቅዱስ ቂርቆስን ቤተ ክርስቲያን አሠራ፤ ለጻድቁ መዝሙር ገጠመለት። ለቤተ ክርስቲያኑ ለማገልገያ የሚያስፈልገውን ሁሉ እሱም ልጆቹም እያዋጡ ሰጡ።

ከዚህ ቀጥሎ በኢትዮጵያ ታሪክ ጎልተው የሚታወሱት የግራኝ ጦርነት፤ የኦሮሞች ወረራና ታላቁ ድርቅ ናቸው። የግራኝ ጦርነት በ1521 ዓ/ም (1528

A.D.) ጀምሮ ያለቀው ከዓሥራ አምስት ዓመት በኋላ በ1536 ዓ/ም (1543 A.D.) ነው። ጦርነቱ መላውን አገር የሚነካ ስለነበረ በነዚያ ዘመናት እርሻ የቱን ያህል እንደታጐለ መገመት ይቻላል። የዘመኑ ታሪክም (የአፄ ገላውዴዎስ ታሪክ መቅድም) ሲያስታውሰው እላለፈም ፦

> በዚያን ዘመን ድል በሰዓደዲን በር (በዘይላ) እስላሞች እጅ ገባች። በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያኑም ባለሥልጣን ሆኑበት። በምሥራቅ በምዕራብ በደቡብ በሰሜን ያለውን ጦር ሁሉ አሸነፉ። በወርቅ በብር ከህንድ በመጡ የከበሩ ድንጋዮች የታነፁትን ቤተ ክርስቲያኖች ሁሉ እስከመዝረፍ ደረሱ። ከምእመናኑም አብዛኞቹን በሰይፍ ገደሏቸው። ወጣቶችን፤ ልጃገረዶችን፤ ሕፃናቱን ማርከው ለነውር ስራ እስከመሸጥ ደረሱ። በዚያን ጊዜ ብዙ ምእመናን የቤተ ክርስቲያንን ሃይማኖት እየተው ወደእስላም ሃይማኖት ገቡ። በሃይማኖታቸው የረጉ ከዓሥር አንድም አይሆኑም። በዚያ ዘመን አምሳያ የሌለው ታላቅ ረኀብ በኢትዮጵያ ተነሣ።

ጦርነቱ እንዳለቀ አሮሞዎች ኢትዮጵያን ሊወርሱ የቻሉት አገሪቷ በጦርነቱ ስለተዳከመች ወራሪን ለመቋቋምና ለመመለስ አቅም ስላነሳት ነው ይባላል። ድርቅ መኖሩን ባያመለክትም በዚያን ጊዜ ባገሪቱ የደረሰባትን ባይኑ ያየ ሰው የገጠመውን መዝሙር ልጠቅስ እወዳለሁ። ግዕዙ ወደ አማርኛ ሲመለስ ግጥምነቱ ይቀራል፤ ጣዕሙም ከእቃ ወደ እቃ ሲገለበጥ ነፋስ እንደመታው ጠጅ ይቀነሳል። (<u>መዝሙረ ክርስቶስ</u> መዝሙር 73)፦

ምነው ጌታ ለምን ለዘላለም ጣልከን፤
የተበታተኑትን የምትሰበስብ፤ የጠፉትንም የምትፈልግ።
ገሠጻህን የተቀበሉ ሕዝብህን አስታውስ፤
በመቅሠፍትህ የተገረፉትንም።
ከሁከት ያረፉበት ጊዜ የለቸውም።
ስለዚህ አረመኔዎች ይሰድቡናል።
ጠላት በቅዱሳንህ ላይ ምን ያህል እንደከፋ
ሁሉን ታውቃለህ፤ እንዲነግሩህም አትፈልግም።
አምላክ በሚያደርጉህ ላይ ውርደትን ያመጣል፤
ይልቁንም በቤተ ክርስቲያንህ ላይ።
እነሆ የበጎን መዝጊያ እንደዱር እንጨት አቃጠለው።
እንደ አረኛ ጎጆም ገድግዳዋን ገነጠለው።
ክብሯን አዋረደ፤ አረከሳትም።
የቅዳሴውንም ቤት የከብት ማቆሚያ አደረገው።
በልጅነቷ እንዴት ነበር ከፍ ከፍ ያደረግሃት፤
አሁንስ ክብሯን ለምን ታዋርዳዋለህ፤
ሞገሷንም ታጠፋዋለህ።
በጥፋት ብትወተውትህስ
አረኛ (ቢወርሳት) ይሻላልን?
ፈንሐስ ልብህን ያስደሰተው (አምላክ) ሆይ!
እስከመቸ ድረስ በቁጣ ዝም ትላለህ

(ችግራችንንም) ትታገሰለህ?
እንግዲህ ሕግህን ማን ይፈልጋታል?
ስምህንስ በምን እንቀድሰለን?
መጻሕፍቱ እንደሆኑ ተቃጥለዋል ተደምሰሰዋልም።
እናት ለሆዷ ልጆች እንደምትራራ ራራልን።
ሲቀጣ የማይገርፍ ጌታ የታለ?
ተማሪውን የማይገሥጽ አስተማሪም የለም።
ከቀጣ በኋላ የማይምርም አለየንም።
ብትርና አለንጋ ከጥንት ያለ ነው
ሥራውን ሳጓደለና ትእዛዝ ለዘነጋ።
ተጸጽቶ የተመለሰንም ይምሩታል።
እንደዚህ ያለው በመጻሕፍት ታውቋል፤
ከሰባ ዓመታት በኋላ
ጽዮንን (ኢየሩሳሌምን) እንደራራሀላትና
ሰዎቿን እንደማርካቸው።
ልጆቿ ከተበታተኑበት ተሰበሰቡ።
የማደን እራስ ክርስቶስ ሆይ፤
ሕዝብህን ማር፤ ጠላታቸውንም ንቀል።
ከተበታተኑበት ሰብስባቸው።
ጥፋተኛ ይማራልና፤ ለማኝም ይሰጠዋልና።
በነቢያት መጻሕፍት እንዲሉከው አትበለን፤
«የጥንት ዘመን ጻድቃን ኖኅ፤ ኢዮብ፤ ዳንኤል
እኔን ለመለመን በፊቴ ቢቆሙ እንኳ
ለዚህ ሕዝብ አልራራም።»
ከነዚህ የሕዝብ ታላላቆች (ሰዎች) በጎ ሥራ ይልቅ፤
የጥፋታችን ሚዛን ቢያይል እንኳን
ከሁሉ የሚበልጠውን የናትህን ንጽሕና አስታውስ።
የእግርና የእጅ(ህ)ን ችንካሮችም አስብ።
ትምረን ትራራልን ዘንድ፤ የእምሰክ ልጅ እንድዬ ሆይ።

ገላውዴዎስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመቱ ዝናም ጥሎ ሰዎች በእንጨት ስራ ስር ሽሚያ ከከብት ጋር መጣላታቸው ቀርቶላቸው «ዳቦ እንደድንጋይ በእግራቸው ረግጠው ነበረ።» ግን ብዙ ሳይቆይ፤ በሁለት ዓመት ውስጥ «ትልቅ ረኀብ ወደቀ፤ በዚህም የክቡርና የልዑል እግዚአብሔር ቁጣ በምድር ላይ ወረደ።»

ግራኝ አጦር ሜዳ እንደወደቀ ጦርነቱ ለጊዜው አቁሞ ነበር። ሆኖም ጥቂት እንደቆየ እንደገና ግጭት ተነሣ። መጀመሪያ አፄ ገላውዴዎስ አዳል ዘመተ (አዳል ዘይላን ይጨምር ነበረ) በኋላ ደግሞ የግራኝ ባለቤት ወይዘሮ ድል ወምበራ እኔን የሚያገባ ባሌን የገደለውን የአፄን አጥናፍ ሰገድን (የገላውዴዎስ) ራስ ያመጣልኝ ነው ብላ ኖሮ አሚር ኑር ገላውዴዎስ እስከለበት ዘምቶ የተመኙችውን እምጥቶ ጥሎሽ ማለሳት። ጭንቅላቱንም ከዛፍ ላይ ሰቀሉት። በዚያን ጊዜ በመላ ኢትዮጵያ በተለይም በምሥራቅ በኩል ታላቅ ድርቅ ሆኖ ሰውና ከብት እንደቅጠል ረገፈ። በዚያን ጊዜ ሰው እርስ

በርሱ ሳይበላ አልቀረም። ይህ በዓረብኛና በአማርኛ ተጽፎ በሐረር ታሪክ ውስጥ የተገኘው የዚያን ጊዜ ጭንቀት የሚገልጽ ሳይሆን አይቀርም ።

> በከብት ማለቅ የተነሣ (በሐረር ሕዝብ ላይ) ችጋር ጠናባቸው። ከዚህም በኋላ ገራድ አበሳም ተሾመ። ዋሊ ላይ ብዙ ሰው በችጋር አለቀበት። ውሀም ቀጅ አልቀረ ስለረኀቡ ጽናት ፩ ሴት ሰው እርዳ በላች። አንድ ሰው ነበር በሐረር፤ በየቀኑ ድሀ ይፈልግ ነበረ እያረደ ሊበላው ረኀብ ስለመጠናቱ በ፩ ቀን ከ፫ ሰዎች ጋር ተቀምጠን የሰው ሥጋ እያረደ የሚበላው ሰውዬ መጥቶ ከደጃፍ ላይ ሥጋውን በሸማው ቋጥሮ ቀመ። ሥጋ ግዙ የፍየል ሥጋ ነው አለ። (ከኛ ማህል) ፩ዱ ሰው ይህ ነገር የሰው ሥጋ መሰለኝ ብሎ ጠረጠረ፤ ጠየቀውም። ቢጠይቀው አዎን አለው። ከዚህ በኋላ ብዙህ አለቀሰ።

ድርቁም ያቆመው የጻድቅ ንጉሥ ራስ ስቅላችሁ እግዚአብሔር ሊቀጣችሁ ነው፤ አይሆንም አውርዱ ብሎ ደግ መከሬ ስለመከራቸውና ምክሩንም ስለሰሙ ነው ይባላል። ድርቁ ያመጣው ጉዳት የሚታወቀው በሕዝቡ አለማደግ እንዲያውም መቀነስ ነው። ለምሳሌ አንድ እንደ ኤ አ በ1902 ዓ/ክ (A.D.) የተጻፈ መጽሐፍ በመለከት የግራኝ ጦርነት የተነሣ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ከዛሬው (ከ1902 A.D.) ይበልጥ ነበር የሚል አገኘሁበት። ወደ አምስ መቶ ዓመት በሚጠጋ ዘመን ውስጥ ሕዝቡ በማደግ ፈንታ ካለውም ከጎደለ ተስበና ረኀብ ኢትዮጵያን ሰው እንደ አሸን እንደ ክረምት አግቢ እየፈላ ወደያው የሚጠፋበት አገር ያደርጓታል።

## የ ጐንደር ዘመነ መንግሥት።

በዚህ ዘመን የተጻፉትን የታሪክ መጻሕፍትና የቅዱሳን ገድሎች እየመረመሩና እየጠቀሱ መጻፍ ድርሰቱን ከመጠን በላይ ያራዝመዋል። ስለዚህ ታሪኩን ሳነብ በማስታወሻ የያዝኳቸውን እንዳሉ እዘረዝራለሁ ከዝርዝሩ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የመስቀል ምልክት (+) በተደረገበት ዓ/ም ያሉት ሲሆኑ ሌሎች አብዛኞቹ ጦርነት ያስከተላቸው እልቂቶች ናቸው። እነሱንም ያነሣሁት ለምሳሌ ያህል ነው እንጅ የነሱ ብጤዎች እልፍ እልፍ የተመዘገቡ ብዙ አሉ። ረኀብና በሽታውም ቢሆኑ ጸሐፊው ያያቸው ናቸው እንጂ በመላ ኢትዮጵያ የቱን ያህል እንደተስፋፉ የሚያውቅ የለም። ጸሐፊው ያላያቸው በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ ብዙ መቅሠፍቶች ይኖራሉ።

<u>ዓ/ም</u>

1583+ ረኀብ ሆነ፤ እህል እንኳ በቅሎ ነበር ግን <u>ከምንቸር</u> የሚባል በሽታ ሰብሉን አጠፋው።
1584+ ረኀብ ተነሥቶ እንዲት ሴት ታንቃ ሞተች፤ የቁርባን ኅብስት ተሰረቀ።
1606+ በዚህ ዘመን <u>ማነን ትታ</u> የሚባል ረኀብ መጣ።
1610+ በዚህ ዘመን <u>በጥቅምት</u> ወር ተስቦ ተነሣ።
1614 የዳሞት ሰዎች ጠፉ።

1615 በወግደ ሕዝብ ጠፋ።
1624 በረን ጠፋ።
1626+ በክረምት ፈንገል የሚሉት ተስቦ ተነሣ።
1630 በዚህ ዘመን አፄ ፋሲል ወደላስታ ዘመቱ፤ ብዙ ሰዎች
በረኀብና በብርድ አለቁ።
1632+ በዚህ ዘመን አንበጣ መጣና መሬት የምታፈራውን ፍሬ
ሁሉ በላው፤ በሰው ሁሉ ዘንድ ረኀብ ሆነ።
1636+ በዚህ ዘመን በሀገሩ ሁሉ ትኩሳት እንደሚያስነሣ በሽታ ያለ
ጉንፋን ተነሣ።
1639 በዚህ ዘመን (ንጉሡና ሠራዊቱ) ጉጃም ቆሬ ላይ ሰፍረው
ነበር ግን የሆድ በሽታ (ተቅማጥ) በተናቸው።
1645+ በዚህ ዘመን ከበብ የሚባል ተስቦ ተነሣ።
1660 በዚህ ዘመን (አፄ) ወደ ጉጃም ተሻገሩ፤ ብዙዎቹ በረኀብና
በጦር አለቁ።
1684 በዚህ ዘመን (አፄ) ዚገምን መቱት፤ ክርስቲያኖች አለቁ።
1685 በዚህ ዘመን (አፄ) ወደደበኔ ዘመቱ ክርስቲያኖች በረኀብና
በውሀ ጥም አለቁ።
1686+ በዚህ ዘመን በክረምት ተናንቂ የሚሉት ረኀብ ገባ።
1692 በዚህ ዘመን አፄ ወደ ጉድሩ ዘመቱ፤ ክርስቲያኖች አለቁ።
1693+ በዚህ ዘመን ወድር (?) የሚባል ረኀብ ገባ።
1696 በዚህ ዘመን ጠላት መጥቶ የጠርና የጉንደር ሕዝብ አለቀ።
1697+ በዚህ ዘመን ፈንጣጣ ተነሥቶ ሰው አለቀ።
1702+ በዚህ ዘመን ትል ፈልቶ ረኀብ ሆነ።
1703 በዚህ ዘመን በእምጋራ መሬት ተንሸራቶ ብዙ ሰው ሰጠመ።
1761+ በዚህ ዘመን ኩፍኝ (=ፈንጣጣ) ተነሣ።
1789 በዚህ ዘመን አመድ (በረዶ?) ዘነመ።
1803+
1804+
1805+ ሦስት ዓመት ሙሉ (ትግሬን) አንበጣ በላው ኩፍኝ
(=ፈንጣጣ ሰውን) ፈጀው።
1848+ በዚያ ዘመን ፈንግል የሚባል በሽታ ተከትሎዎ
(አፄ ቴዎድሮስ የተባሉትን ደጃዝማች ካሳን ነው)
የዘመተውንም ሠራዊት ፈጀው ከገርም ያለው
ባሳገር በበሽታ አለቀ። አልቃሽ እንደህ አለች፦

*በነጋሪትዎ ሞት ተሞርቦዎ፤*
*የወጣው አይገባ ያለው አይቆይዎ።*

# የአዲስ አበባ ዘመነ መንግሥት።

ንጉሥ ምኒልክ የኢትዮጵያን መንግሥት በጃቸው ለማግባት በሚያቅዱበት ጊዜ በሥርዓተ ንግሣቸውም ዘመን የኢትዮጵያን ከብት ያሟጠጠ የከብት በሽታ ገብቶ ነበር። በሽታውን ያመጣው ጣሊያኖች ሰሜን ኢትዮጵያን ሲይዙ ለሠራዊታቸው ስንቅ ከህንድ አገር ያመጡት የሥጋና እንዲሁም የጭነት ከብት ነው ይባላል። ይኸ አንዳንድ መጻሕፍት ከንትር የሚሉት በሽታ ያደረሰውን ጉዳት ገና ያልታተመው «የጉጃም ታሪክ» ከዚህ በታች በተጻፈው ሁኔታ ያስታውሰዋል፦

> ዳግማዊ ምኒልክ እንደነገሡ ወዲያው የከብት በሽታ መጥቶ በየሀገሩ ፈጀው የሚያርስ በሬ የሚታለብ አላም ታጣ። የሞተውን ከብት እንኳንና ሰው አውሬውና አሞራው ተጠይፎት እሚበላው አጥቶ አገር ምድሩ ጠነባ። ብቻ ቀርበቱን ለመገፈፍ እንኳን አታከተ፤ ዘመኑ ረኀብ ሆነ። ያን ጊዜ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት (የጎጃሙ) ሸንቅላ ዘመቱና ሠራዊቱን በከብትና በእህል አዳነው።... ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ኃላቤት ባጅቶ ቢመለስ በጎጃም ረኀብ ጠንቶ ብዙ ችጋረኛ ተጎድቶ በየመንገዱ ወድቆ የነፍስ ምጽዋት እያለ አሳዘነው። ንጉሡም አዘዥ ቢሰውርን አስጠርቶ የጅበላን ጉተራ አስከፍቶ ኢያስጫነ ኢያመጣ በደጀ ሰላም ለወደቀው ሁሉ ችጋረኛ ናኘው። ያን ጊዜ እናት ልጇዋን ጠላች ዘመድ ዘመዱን ጠላው። በአህያና በፈረስ ሥጋ እርስ በርሱ ተጣላ። በረኀብ የሞተውን የሚቀብረው አጥቶ አውሬና አሞራ ተጠየፈው አሳፈ አግዳሚው ዋይ ለልስ ኢያለ ቅጠል ኢየበጠቀ ሣር ኢያግበሰበሰ በሬሳው ላይ ኢየጣለበት ያልፍ ነበር። ያን ጊዜ ከቆላ ወደደጋ የተሰደደው እንጀሩን ቀጋውን አሞጩን ከደጋ ወደቆላ የተሰደደው እንኮዩን ከሺሙን ከኩን በመሀል ደረቢ የቀረው ሙረርጁን እክርማውን ሙጃውን ኢየበላ ወጣ። ለሞት የተቆጠረውም እህል እልመጥነው ብሎ ሰውነቱ ኢያበጠ ሞተ። ፯ ቁና እህል በ፩ ብር ተሸመተ። [አንድ ብር የዓመት ግቢ በሆነበት ዘመን] ደግሞ ወበሸማኔ የሚባል አውሬ በነብር ኢየተመሰለ ቤት ኢየቀደደ ብዙ ሰው በላ፤ ያን

ጊዜ ወቦ ሸማኔውና ጅቡ የቆመ ነው እንጅ የሞተ አይበላም ነበር። የዚህ ጊዜ እንዲት ደጋ በለቅሶ ዜማ ስታለቅስ እንዲህ አለች፦

ከአፋፉ ላይ ቆሜ ዘቅዝቄ ብየው
የሚከለከለው በላሞዋይ የለው።
ሰወ በላው እዩት አሳያችሁ።
ተወው አትሉመይ ምነው ኢያያችሁ።

አለች። ከዚህ በፊት በመልከመ ቀን አጼ ዮሐንስ ጎጃምን ሳይዘርፈው ክብቱ በጎጃም አረብቶ የሚነዉው ማር የሚመሰግበት ሜዳ ጠቦት ባለገሩ ሁሉ በማር ከልክል በመሬት ድምበር ኢየተጣላ ሲጋመስ ደኝነት ሲከፍል ይኖር ነበር። አጼ ዮሐንስ ከዘረፈው ከብቱን ፈራ (ጎደድ) ከፈጀው ወዲህ ግን አገሩ ምድሩ ደገለ ሰውና ፈረስ የሚውዋ የሚያጠልቅ ውድማ ሆነ። የበሬ እርሻ ቀርቶ የፍልፈል እርሻ በረከተ። የፍካሬ ኢየሱስ ትንቢት ወየሐርበዋ ለምድር እንጌዋ ወፍልፈል [ምድርን አይጥና ፍልፈል ያርሷታል] ያለው ደረሰ።ነገር ግን እግዚአብሔር ኢየጋድጋ ለሀገር ዘእንበለ ፭ ኄር [አገሪቱን ያለንድ ደግ ሰው አላስቀራትም] ያለው አልቀር ብሎ በጎጃም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በሸዋ አፄ ምኒልክ ለድጋውና ለሕዝቡ ሁል ጊዜ ይመጸውቱ ነበር።.... በዚያን ዘመን ደግሞ በሸዋ እንሳር ከሚባል አገር እንዲት ሴት ፯ ልጆች በልታ ተይዛ ከአፄ ምኒልክ አደባባይ መጣች ንጉሡም እንጦጦ ከእልፍኙ ደጃፍ ተቀምጦ መረመራት እርሱዋም አዎን ቢርበኝ በላኋቸው አለች። እርሱዋ ግን እንኳንና ፯ ሰው የበላች ቅናሽ ሥጋ የቀመሰች አትመስልም ነበር። እንጀቱዋ ከጀርባዋ ተለጥቶ እጇዋን እግሩዋን ማደት ወርቦት ትንሽ ደዘ ለጥባ ታሳዝን ነበር። ንጉሡም እንደት አገሬ ጠፉ ደጋየ ዘመዱ አለቀ ብሎ አዘነ። እንያም ይዘው ያመጡዋት ባላጋርቹዋ የርሱዋን ልጅ ትታ የኛን ልጅ ለይታ ከበላች ፍርድ በቃ ይሰጡን መሞት ይገባታል አሉ። አፄ ምኒልክም ለኔ ስትሉ ተውልኝ ቢጨንቃት ቢርባት ነው ደግሞ ሌላ ልጅ ካለማሁ ብላ ነው እንጂ ከባሰባት ልጆዋንም ቢሆን አትተውም ማሩልኝ ብሎ አስማራት። ወዲያው ልብሱዋን ቀለቡዋን ደርጎ እርሱዋን ማድቤት ልጆዋን ተማሪ ቤት አገባቸው።

ኢትዮጵያን ሦስት ዓመት ያህል ስለገረፉት መቅሠፍት ብዙ ተጽፏል። ያዩትም በሕይወት የደረሰንባቸው ሰዎች ነበሩ። ከነዚህም አንዱ (ልጃቸው መንግሥቱ ለማ ባሳተመው <u>መጽሐፈ ትዝታ</u> እንዳየነው) አለቃ ለማ ናቸው፦

ከብት አለቀና አደለም ረኀብ የሆነው? ከብቱ ያላለቀበት አገር የለ፤ ጭርስ ብሎ አገር አለቀ፤ በቶሎ ምን ምን አልተገኘም። የኔ አባት እስከ ሦስት መቶ ከብት ነበራቸው፤ አንዲት ጥጃ ተረፈቻቸው አሉ። ስሟን «ባለሁ ድረሽ» አሏት አሉ። ረኃቡን ያስነሣው የከብቱ ማለቅ ነው። በምን ይታረስ? መሬት ሳይታረስ እንደ ያው እንዳለ ቀረ። ረሀቡ ያን ጊዜውን ከብቱ እንዳለቀ ተከተለ፤ እስከ ሦስት ዓመት ድረስ ሰነበተ።

ጅብ ጭርስ አረገው ሰውን። አሁን (የአዲስ አበባ) ሥላሴ የተሠራበት ላይ የራስ ደስታ አባት የፊታውራሪ ዳምጠው ቤት ነበር የምኒልክ የፈረስ ቤት። እሳቸው ግሼን ተሹመው ሕደዋል ባለቃ ወልደ ያሬድ ተሰጠ ቤቱ፤ እኛም ኸዚያው ኸንድ ቤት ውስጥ ነን። ሊሊት «ወሰደኝ! ወሰደኝ! ወሰደኝ!» ሲል ያድራል። በበነጋው ማልዳ ጉባኤ ሲኼድ [ትምርት ስንጀምር ማለት ነው] አለቃ ወልደ ያሬድ፦ እንቅልፍ እንደሌለኝ ታውቋል «ለማ፤ ዛሬ ጅብ ስንት ሰው ወሰደ?» ይሉኛል።

«አምስት ስድት እስከ ሰባት ድረስ ወሰደ» እላለሁ፤ በድምጡ በጩኸቱ፤ «ይህን ያህሉ ወንድ ይህን ያህሉ ሴት» እላለሁ። ማ ይወጣል ጅብ ሊከለክል? ሁሉም ደከማ ነው —ረሀብ። ደሞ እሱን ቢወስደውስ ማን ያድነዋል?

አንዲት ልጅ ወዛ ብላለች —ጋይንቴ ደስታ እሚባል ነበርና እሱ እየረዳት ተነሥታ ፍሎሃ ወረደች። ብዙ ሰው የተቀመጠው እዚያ ነው ይኸ በደተኛው ሁሉ —ተቀበለና እዚያ አረደና በላት።

ልጆቻቸውን ጥቃቅኖቹን እያረዱ የበሉ ሴቶች ብዙ ናቸው። ሰው ቅጠል በላ፤ ያልተበላ ቅጠል የለም፤ ይኸ ቅጠል ቀረ እሚባለውን ነገር አላውቀውም።

አጤ ምኒልክ ለችግረኛው እርዳታ እንደመጠኑ ማድረጋቸው አልቀረም። ደጃች

ገርማሜ ነበሩ እደ በታች ብዙ እንዲያው ብዙ እሕል ተገኘ ኸሰቸው፤ ብዙ ጉድጓድ ነው ሰጡ። ለየመቅደሱ ሰጡ፤ ለየመምራኑ ተሰጠ። እኔም ለኛ ላስተማረዬ ላለቃ ተጠምቶ ወርጄ ጭኜ መጣሁ። እኛ ራስ ደርጌ ሦስት መቶ ነው አራት መቶ ደውለ? እሕል ሰጡ—ኸዚያ ኸገራቸው ኸደ [=ከእድእ] በታች ሙሉ እሚባለውን ይዞ ኸጉድጓድ ብዙ እሕል ተገኘ። ለስደተኛውም ብዙ ሰጡ። ጎጃሞችንም ሰደዷቸው እዚያ ታች። ጎጃምማ ባጤ ዮሐንስ ተዘርፎ የለም? መጀመሪያ ስደት የጀመረ ጎጃም ነው። ያልመጣ ማን አለ? ትግሬዎችም። እማሴን የመጣ አይመስለኝም።

ይኸ ከሀንድ የመጣ በሽታ ከብቱን ዘጠና በመቶ እንደፈጀውና ሕዝቡም በረኀብ አንድ ሦስተኛው እንዳለቀ ይተረካል።

ከዚህ ቀጥሎ ኢትዮጵያን ከዳር እስከዳር በመግረፍ በሰፊው የታወቀው የኅዳር በሽታ ነው። ዕድሜያቸውን በሉ የሚቆጥሩ አሁንም በሕይወት አሉ። የኅዳር በሽታ የተባለው ቸነፈሩ በኅዳር ወር ስለተስፋፋ ነው፤ ዘመኑም 1911 ዓ/ም ነበረ። አፄ ኃይለ ሥላሴም በሕይወት ታሪካቸው እስታውሰውታል፦

ከዚህም በኋላ ከኅዳር ወር ፩ ቀን ጀምሮ እስከ ኅዳር ፴ ቀን በአዲስ አበባና በሌላውም በኢትዮጵያ አውራጃ ሁሉ የቸነፈር (የግሪፕ) በሽታ ተስፋፍቶ ነበርና አዲስ አበባ ከተማ ብቻ ከ፴ሥር ሺ የሚበዙ ሰዎች ሞቱ። እኔ ግን በብርቱ ከታመምኩ በኋላ በእግዚአብሔር ቸርነት ተረፍኩ።

ያን ጊዜ አዲስ አበባ ገና የሠለሰ አንድ ዓመት ሕፃን ሆና ሰለ ከ፴ሥር ሺ የሚበዙ ሰዎች ከሞቱባት ከጃንሆይ ጋር በእግዚአብሔር ቸርነት ከሞት የተረፈው ስንት ይሆን። ጃንሆይ GRIPPE አሉት እንጅ INFLUENZA በመባል የታወቀው ከዓለም ላይ ወደ ሀያ እምስት ሚሊዮን ሰው የፈጀ ጉንፋን መሰል በሽታ ነው። ከላይ እንደተነገረው በሽታው በሞላ ኢትዮጵያ የዘመተ ስመሆኑ የልዑል ራስ እምሩ ማስታወሻም ተጨማሪ ማስረጃ ነው፦

በሺ፱፻፲፩ ዓመተ ምህረት በርፖና በእስያ አድርጎ የመጣው የነፋስ (የግሪፕ) በሽታ በኢትዮጵያም በመላው አገር ገብቶ ብዙ ሰው ሞተ። ያንጊዜ ሐረር ነበርኩ። እዚህም እሐረርጌ ከህዳር ወር ጀምሮ እስከ ጥር መጨረሻ ሰሞን ድረስ በጣም ከፍቶ በከተማው ውስጥ ብቻ እንኳን ከሰማንያ እስከ መቶ ሀያ በየቀኑ ይሞት ነበር። የታመመው ሰው ልክ አልነበረውም። በሽታውም ትኩሳቱ በጣም እየበዛ እራሱ እየዞረ አእምሮው እየጠፋ ደም እያስታወከ ነው። በቶሎም ካንዱ ወደአንዱ የሚተላለፍ በመሆኑ ብዙው ቤተሰብ እንዳለ እየተኛ አስታማሚው ብዙ ችግር ሆነ።

የጉጂም ታሪክ ጸሐፊም በአጭሩም ቢሆን «ነፋስ የሚባል በሽታ ፩ጊዜ መቱን የሚዘልስ [ተርታውን የሚፈጅ ማለት ነው] ከጀርመን የወደቀው መርዝ ከአዲስ አበባ ጀምሮ በ፩እፍታ ጉጂምና ዳሞት ደረሰ ለቀብሪ አታከተ።» ሲል እንሥቶታል። በሐረር ምናልባትም በአዲስ አበባ ሐኪም በሚገኝበት የባሕር ዛፍ ቅጠል እየቀቀሉ መታጠንን ተስፋ አገኙተውበት ነበር። በሌላው በታ ግን የሆነ ያልሆነውን «መድኃኒት» ይሞክሩ ነበረ። የጉጂሙ ታሪክ እንደሚለው፦

የሕግሙ ባሕል ደገሞ ባልና ነስር ተቅማጥና ውጋት ፬አይነት ነበረ። አመሉና ምግቡ (መደኒቱ ማለት ነው) ደገሞ እኩሉ ቋንጣ እኩሉ ጠጅ እኩሉ ኑግና ቶሎ ንፍሮ እኩሉ ቂጣና ቡን ይል ነበረ። ትረፍ ያለው ከርስቶስ ያልቶጠረው የቅቤ ቡና አዳነው። በወህኒ ቤት ታሥሮ የነበረው ሁሉ አስታማሚ ኢያጣ ከነሰንሰለቱ ተቀበረ። ያን ጊዜ አባ ኪዳኔ ማርያም ፪ኛው ስሙ አባ ውዛውዝ የሚባል ከሰው እስከ እንስሳ እርስዎ የሚል ደግ ባሕታዊ ነበረ። ቀራሽና ውኃ እንጨት የሚያስፈልገውን ሁሉ ኢየለመነ ኢየሰጠ ብዙ በሽተኛ ረዳ። ዘመድ የሌለውንም እያስታመመ ቀበረ። ብዙ ትሩፋት ሠራ። ያን ጊዜ ራስ ኃይሉ ደምበጫ ላይ ባለ በ፩ወገን ስለ በሽታው እግዚእታ እስይዞ ነበረ። በ፩ወገን የቤት ሥራ ናፋ አድርጎ ደንጋይ ሸክም ጭንቅ ድኃ ጨዋ ኪ ነገሩ አይሰማ(ለት)ም ነበር። ከበሽታው ይልቅ

ሰው በራስ ኃይሉ አዝኖ ነበረ።

ምን ጣጣ ነው!» ሲባል ሰምተናል። ጣጣ ሲያጋጥመው እንዲህ ያለም ይገኝ አይመስለኝም። «ጣጣ ፈንጣጣ» ሲባልም ሰምተናል። ታዲያ ጣጣ ምንድነው? የጉጂሙ ታሪክ እንደሚነግረን ከሆነ ይኸም ኢትዮጵያን ከገረፉት በሽታዎች አንዱ ነው፦

> በዚህም ወር [በጥር 1916?]ባ/ም ሞጌሴ [=ሞያሌ] የሰውነት ነቀዝ የቀበል ሕመም በሀገሩ ሁሉ ተዘርቶ የእጅና የእግር ጣት ኢያቆሰለ አስቸግሮ ነበረ። ገን እንደ እሸህ ነቅሶ ሲያፈርጡት የቀንጫጭት እንቁላል የመሰለ እየወጣ ይድን ነበረ። ፪ኛ ደግሞ ጣጣ የሚባል ሕማም ራስ ኢያዞረ የሚያም ነበረ። እርሱ ደግሞ በ[ጀን]ጥላ መገተሪያ በነጠለው ብረት አግሞ [=አግሎ] በእሳት ሲተኩሱት ይድን ነበረ። ስለዚህ ሕማሙን ጣጣ ብለው ስም አወጡለት። እገሌ ወይም እገሊት ጣጣ ታመዋል ይባል ነበረ።

የጣጣቴ መድኃኒት በሀገራችን የተለመደ ነው። በሽታና ረኀብ የሚመጡብን ስለኃጢአታችን መቀጮ ከሆነ ሞያሌና ጣጣ ሰው አስቸገሩ እንጅ ሕዝቡን «መቱን ስላልዘለሱት» ለትንሽ በደላችን ቀንጢጦች መሆናቸው ነዋ።

## የኢትዮጵያ ዮሴፍ።

ከላይ እንደተጠቀሰው በፈርዖናውያን ዘመን ሰባት ዓመት የቆየ ረኀብ በግብፅ ገብቶ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ግብፅ በዚያ በረኀቡ ዘመን እንኳን ልትራብ የጐረቤት አገር ሰዎች እህላቸውን የሚሸምቱት እዚያ ነበር። ይኸም የሆነበት ምክንያት ዮሴፍ የሚባል ብልህ ሰው ቀደም ብሎ አዝመራው በሠመረበት ዘመን ለክፉ ቀን የሚሆን እህል እንዲከተት ለንጉሡ ስለነገረውና

ንጉሡም የዮሴፍን ምክር ስለተቀበለው ነው። ይኸንን የመሰለ አገር የሚጠቅም ሕዝብን ከእልቂት የሚያድን ምክር ስለሰጠው ምክሩን ራሱ ከሥራ ላይ እንዲያውለው ዮሴፍን ከእስር ቤት አውጥቶ ከበታቹ በመላ ግብፅ ላይ እንደምክትል ንጉሥ እንደጠቅላይ ሚኒስቴር ሾመው። ታሪኩ የሚነግረን የዮሴፍን ብልህነትና ንጉሡ አስፈላጊነቱን በሚገባ ማወቁን ነው። የሕዝብ መሪ ሕዝቡን ከችግር ከማዳን ሌላ ዋና ጉዳይ የለውም። ፈርዖን ይህ ከባድ አስፈላጊነት ስለተሰማው እስከዚያን ቀን ድረስ እልባሌ ለነበረ (ያውም የውጪ አገር) ሰው የጣቱን ቀለበት አውልቆ ሰጠው። ቀለበቱ ጌጥ አይደለም የንጉሡ ማኅተም የተቀረጸበት ሥልጣንን በጅ ማድረጊያ ነው። ያንን ማኅተም የያዘ ጽሑፍ እንደ ንጉሡ ቃል ይከበራል። ኃላፊነቱን በሚያውቅ መሪ ዘንድ የሕዝብ ደኅንነት ከማንኛውም ጉዳይ ተቀዳሚነት እስከዚህ ድረስ ነው።

በኢትዮጵያ ታሪክ ድርቅ ረኃብ፣ ተስቦ የመንግሥት ጉዳይ ሲሆኑ አይታዩም። እርግጥ አንዳንድ መሪዎች እዚያው እቤተ መንግሥታቸው ድረስ የመጡባቸውን የረኃብ ስደተኞች ሲመጸውቱ ይታያሉ። በመሠረቱ ግን ይሰጉ የነበረው ረኃብ የጦር ሠራዊታቸውን እንዳይቀንስባቸውና ሥልጣናቸውን ሌላው ሠራዊቱ ያልተጉዳበት እንዳይቀናቀናቸው ስለሆነ ያንኑ የተራበውን ሕዝብ ለሠራዊታቸው እህል እንዲያመጣ መልሰው ይጠይቁታል። ለምሳሌ በጎደር በሽታ ጊዜ የጉጃም ሕዝብ መወዛወዝ እቅቶት ሳለ ለልዑል ራስ ኃይሉ «ፈጠበድኝና እናሞራ: … ዕለት ዕለት ሺህ ሺህ እንጀራ ራት ሁል ጊዜ ያገባ ነበረ።»

በሀገር ላይ የሚመጣ ረኃብ የመንግሥት ጉዳይ እንዲሆን ያለመስልቸት በብዙ ዘዴ ለረጅም ዘመናት የደከመና ውጤቱን በዓይኑ ለማየት የበቃ፤ በዚህም የኢትዮጵያን ታሪክ የለወጠ የኢትዮጵያ ዮሴፍ የምለው ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ነው። (መስፍን ጓደኛየ ስለሆነ እንቱ እያልኩ መጻፍ ያዳግተኛል።) መስፍንንና እንዳንዶችንም እንዳበ ኪዳነ ማርያም እንዳቅማቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሠሩትን ታላቅ ውለታ ታሪክና የሰማዩ አባታችን በቸርነታቸው ያስታውሷቸው እንደሆነ ነው እንጂ እንዲህ ያሉ የግል ጀግኖችን በይፋ

የሚያከብር መሪና አስተዳደር በኢትዮጵያ ገና አልተነሣም። ዮሴፍ ከእስር ቤት ወጥቶ ሲሸም መስፍን ከሥራው ላይ ተወስዶ ታሰረ። መስፍንን እንደማውቀው እስቸጋሪ ሰው ነው። እስቸጋሪነቱም ሊሆን የሚገባውን ነገር ምክንያት እያስቀረው በማለት ነው። መስፍን እድሜ ልኩን ሠርቶ አሁን በአዲሱ የጡረታ ሕግ ምክንያት የግል ሥራውን (ጥናት) ያኪያሂዳል። በዚህ ዘመን ሁሉ ቤት አልሠራም። እኔ እንደሚመስለኝ ኢትዮጵያን እንደቤቱ፤ ሕዝቧን እንደቤተ ሰቡ ቆጥሮ ነው። ከመስፍን ጋራ የብዙ ዘመን ጓደኝነት ሲኖረኝ፤ በየጊዜው እየተገናኘን በሐሳብ ስንጋጭና ስንስማማ፤ በየስብሰባውና በየግል ግብዣ ሰው ሁሉ ተበታትኖ ሁለታችን ብቻ ወደኋላ እየቀረን ስንጨቃጨቅ፤ አንዳንዴም እዚያው ስናነጋ ኖረን እስከ ዛሬ ድረስ የየት አገር ሰው እንደሆነ አልነገረኝም። ወንድም፤ እኅት፤ አጉት፤ አክስት፤ ወይም ሌላ የሥጋ ዘመድ ይኑረው አይኑረው አላውቅም። እናት አባቱ በልጅነቱ እንደሞቱ እንደጋጣሚ አንድ ቀን አውርቶልኛል። ያንንም ያነሣው እናቱ በሕይወቱ ላይ ያላቸውን ተጽእኖ ለማድነቅ ያሀል ነው። በኢትዮጵያ ጉዳይ መስፍን ፊት ለፊት ያለ ይሉኝታ ያለፍርሀት ስለሚናገርና ስለሚጽፍ የሚያደንቁት ብቻ ሳይሆኑ የሚቀየሙትም አይጠፉ። ለወቀው ሰው የመስፍን ቸርነትና ርኅሩኅነት ሞገደኛነቱን እንደሌለ ያደርጉታል።

በ1949 ዓ/ም ትግሬ ላይ ዝናም ሳይጥል ቀርቶ በ1952 ዓ/ም ላይ ረኀቡ ሰውን መቱን መዘለስ ደርሶ ነበር። ለጠቅላይ ግዛቱ ሕዝብ ለርዳታ በቅድሚያ የደረሰላቸው መስፍን ነው። ከሸዋ እህል ያላቸው ሀብታሞች እየፈለገ በነፃ እንዲሰጡ አስረድቶ የሰጡትን ወስዶ አከፋፈለ። አልበቃም፤ ብዙ ሰውም አለቀ። መስፍን ግን ስንቁን ሳይቀር ሰጥቶ አዲስ አበባ ተመልሶ የገባው ጠኔ እያግተረተረው በብዙ ማቃሰት ነው።

በ1965 ዓ/ም በወሎ ስለደረሰው ረኀብ የማናውቅ ብዙ አንሆንም። እንደ ያውም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ለመውደቅ ያበቁት ምክንያቶች ሲቆጠሩ እሱም እንዳንዱ ይገባል። በዚያን ጊዜ በወሎ ረኀብ

መግቢቱ በምስጢር ተይዞ ኖሮ ምስጢሩ የወጣው JONATHAN DIMBLEBY የሚባለው እንግሊዛዊ ጋዜጠኛ በፊልም አንሥቶ ስለሰየ ነው ይባላል። ይኸንን ጋዜጠኛ በኢትዮጵያ አዲስ የተቋቋመው ወታደራዊ መንግሥት ምስጋናውን ሊያቀርብለት ተጠርቷል ተብሎ አከተማችን ውስጥ አይተነዋል። ሚስተር ዲምብልቢ መመስገን ቢገባውም የወሎን ረኀብ ያወጣ የመስፍን ጥረት እንጂ እንግሊዛዊው አይደለም።

በዚያን ጊዜ እኔ የዩኒቨርስቲ መምህራን ማኅበር ፕሬዚዳንት ነበርኩ። መስፍን የማኅበራችን የሥራ ፕሮግራም ሹም ነበረ። የሥራ ፈጻሚዎች ስብሰባ ላይ ምን የሥራ ፕሮግራም የሱ ኮሚቴ እንዳወጣልን መስፍንን ብጠይቀው፤ «ረኀብ በወሎ ገብቷልና ዐቅማችንን ሁሉ እሱን መቋቋም ላይ እናውለው። ሕዝቡ ተርቦ የሞተውን በመንገድ እየቀበረ ከወሎ ድረስ በእግሩ እየተጓዘ አዲስ አበባ የመጣ አለ፤ ግን ማሀል ከተማ እንዳይገባ ከተቢ ላይ በፖሊስ ታግዷል። ከጥቂት ቀናት በፊት ከዶክተር አብርሃም ደሞዝ ጋራ አብረን ሄደን በዓይናችን አይተናል።» አለን። (ዘመኑ ስለራቀ ቃሉን በትክክል አልጠቀስኩት ይሆናል።) ስብሰባውን እንደጨረስን ከተቢ ወስዶ እመንገዱ ዳር የፈሰሰውን ሕዝብ አሳየን። የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በነገሩ እንዲገባበትና እርዳታም እንዲሰበስብ ብንጠይቅ (ያን ጊዜ እኔ ጀኔቭ የማእከላዊ ኮሚቴ አባል ነበርኩ።) መጀመሪያ ተጨባጭ ማስረጃ እንድናመጣ አስፈላጊውን ገንዘብ ብቻ ሰጠን። መጋቢት መጨረሻ ግድም ዓርብ ዕለት ዶክተር አብርሃም ደሞዝ፤ ዶክተር አሉላ አባተ፤ እኔ ሆነን ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ሴስና አይሮፕላን ተከራይተን ወደወሎ ሄድን። የደሴን አካባቢ፤ ወደሰሜንም እስከ ወልድያ ድረስ ወደታችም በቲ ድረስ የቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት ባዋሰኝ ላንድሮቨር መኪና እየተዘዋወርን በችጋር የሚያልቀውን ሕዝብ አነጋገርን። ድምጻቸውንም በቴፕ ሪከርደር ቀድተን ጣረሞት ከያዛቸውም አንዳንዶችን ፎቶግራፍ አንሥተን እሑድ ወደማታ ወደ አዲስ አበባ ተመለስን። ረኀብ የሚያንፈራፍረውንና አውሬ የሚገነጥለውን ሰው ከሚራ እያስተካከሉ ፎቶግራፍ ማንሣት ብዙ ልዩነት የለውም። የኒያ የሽማግሌ

ጥርስ በካሜራዩ ብቻ ሳይሆን በአእምሮየም ስለተቀረጸ አሁንም ወለል ብሎ ይታየኛል። እንደያውም እየዘገነነኝ ለብዙ ቀናት እበንን ነበረ። መስፍን አውሮፕላን ማረፊያ መጥቶ ሁላችንንም በየቤታችን አደረሰን።

ከቤት ስገባ ለካ የትልቋ ልጄ የልደት በዓል የሚከበርበት ቀን ኖሮ ከፈረንጅ አገር የመጣላትን አዲስ ልብሷን ለብሳ፤ አዲስ ጫማ ተጫምታ፤ የኢንሪኮ ኬክና ብስኩት የአገር ድፎ ዳቦም በጠረጴዛው ላይ ተንጣሎ፤ ጓደኞቿ ሁሉ ዓይን የሚማርክ ልብስ ለብሰው ስጠበቅ ደረስኩ። የመንገዳችንን ሪፖርት ለነገ ማድረስ አለብኝ የሚል አጥጋቢ ምክንያት ሰጥቼ የሥራ ጠረጴዛዬ ወዳለበት ክፍል ዘር አልኩ።

ያዘጋጀሁትን ሪፖርት በማግስቱ ለእሉሳና ለአብርሃም አሳይቼ በዋናው ላይ ፈረምንበት፤ እሱን ለኔ አስቀርቼ የተባዛውን ለመስፍን ሰጠሁት። መስፍን ሪፖርቱን፤ ፎቶግራፎችን፤ ቴፑን ሰብስቦ DROUGHT AND ITS CONSEQUENCES የሚል የጂዮግራፊ «ትርኢት» አሳየ። ተማሪዎቹ ያንን አይተው በማግስቱ ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ። ሕዝብ በረኀብ እያለቀ እንማርም አሉ። እኔም ከዚያ ወዲህ ወደ ማስተማሪያ ክፍል አልተመለስኩም። የዚያን ጊዜው ረኀብ ሁለት መቶ ሺህ ሰው ፈጀ የሚባለው የኛ ሪፖርት ያመለከተውን ቁጥር በመቀበል ነው። የወሎ ረኀብ ድብቅነቱ የወጣው ያን ዕለት ነው። መስፍን ከዚያ ቀደም ብሎ ፖርሳማ ውስጥ ያሉትን የወሎ ተወካዮች ሞክሯቸው ነበረ፤ እንደተማሪዎቹ ኃይል አልነበራቸውም። ሪፖርታችንን በውጪ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወደየውጪው አገር ቋንቋ ተርጉመው ጋዜጣ አወጡት። ሚስተር ዲምብልቢ ያንን አይቶ ነው ወደኢትዮጵያ የመጣው። አዲሱ መንግሥት ምስጋና ሲያቀርብለት ለማየት እንድንችል ያሀል በስነ ሥርዓቱ ላይ እንድንገኝ ተጋብዘን ቢሆን ዝርዝሩን ለመጻፍ ያመቸን ነበረ።

መስፍን አገሪቱ እንዴት የቱን ያሀል ለረኀብ እንደተጋለጠች መሠረታዊ ጥናቱን አሳትሟል:- Mesfin Wolde Mariam, Rural Vulnerability to Famine in Ethiopia. Vikas Publishing house Pvt. Ltd; New Delhi/ Addis Ababa, 1984. ጥናቱ ለሀገር

መድኅን የሚሆኑ ሐሳቦች ስላሉበት ስለድርቁ ለንግድ በጥድፊያ ከተጻፉት ከሌሎች መጻሕፍት ጋር በአንድ አይታይም። የሚያሳዝነው መስፍን በዚህ መጽሐፉ ውስጥ ስለራሱ ልናውቀው የሚገባውን ያህል አልጻፈም። ስለድርቅ ሁኔታ ጠለቅ አድርጎ ለማወቅ የሚፈልግ ይኸንን የመስፍን መጽሐፍና በታሪኩ በኩልም የሪቻርድ ፓንክረስትን ድርሰቶች ማንበብ ያስፈልገዋል፡- Richard Pankhurst, "The History of Famine and Pestilence in Ethiopia prior to the Founding of Gondär," Journal of Ethiopian Studies, Vol. X (1972); "The Earliest History of Famine and Pestilence in Ethiopia," Ethiopian Medical Journal, Vol. XI (1973); The History of Famine and Epidemics in Ethiopia Prior to the Twentieth Century, Addis Ababa 1985.

## መደምደሚያ

ከታሪካችን ታላላቅ ምዕራፎች አንዱ የሚመሰክረው የኢትዮጵያ መሬት የኢትዮጵያን የልጆቿን ደም ጠጥቶ፣ በልጆቿ ሥጋ ዳብሮ፣ የልጆቿ አጥንት የሚመረትበት መሆኑን ነው። ገበሬዎቹ ሠለስቱ አጋእዝት ወይም ሠልስቱ አጋንንት ረኀብ፤ በሽታ፣ ገዢዎቻችን ናቸው። በእናታችን በክርስቶስ ሠምራ አነጋገር እነዚህ ሁሉ ከልዑል እግዚአብሔር የሚለኩ ስለሆኑ የእናታችንን ቅዠት እርእያ በማድረግ ለሁሉም እንጸልይላቸው። ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ ተኀሢበ በደመ ውሉዳ፤ ወዚንም ወደ ግብፅ ሰዷ።

# ረሃብ ድርቅና መንስኤዎቻቸው

(ከገብርኤል ደንኤል)

ይህ ፅሑፍ በምንም ረገድ የተሟላ ነው በማለት የቀረበ ሳይሆን ለአንባብያን በርዕሱ ላይ ያለኝን ውሱን ግንዛቤ ለማካፈል ነው። አብዛኛውን ጊዜም በንባብ፣ በውይይትና በተመክሮ ላይ የተመሰረተ ነው።

የርዕሱ አንገብጋቢነት፣ ሁለገብነትና ሁለአቀፍነት አንባቢያን በርጋታ እንዲያስቡበት፣ በሰፊው እንዲተቹበትና መፍትሔ እንዲጠቁሙበት ያስገድዳል።

ይህ ሁኔታ ዓለም አቀፋዊነት ያለው ስለሆነ ከቁጥር ውጭ የሆኑ ተፅዕኖዎችም ሊኖሩ ስለሚችሉ የሚጠቁመው መፍትሔ መሰምታዊና መከራዊ የመሆን ዕድል ሊኖረው ይችላል። እንደአከባቢውም ተፈፃሚነቱ ይለያያል።

የፅሑፉ ጭብጥ ከሞላ ጐደል ረሃብና ድርቅ ሰው ሰራሽ ችግር ነው፣ ስለዚህም መፍትሔው ሰው ሰራሽ ነው ወደሚለው ያዘማል።

ይህ ማለት ግን የተፈጥሮን ተፅዕኖ በማኪሰስ ሳይሆን ሰው የሚችለውን ከልቡና በትክክል ከፈፀመ የቀረው ችግር እስከዚህም ላይሆን ይችላል በማለት ነው። ተፈጥሮን ማማረር መጀመሪያ የአቅምን ካደረሱ በኃላ ቢሆን ይመረጣል።

ፅሑፉ በሚከተሉት አርዕስተ ነገራት ተከፍሎ ቀርቧል ፦

፩ መንደርደሪያ
፪ ረሃብ በታሪክ
፫ ረሃብ በኢትዮጵያ
፬ የረሃብ መንስኤዎች

1 የተዛባ የአየር ጠባይ
 ሀ ዝናብና ድርቅ
 ለ የዝናብ መዛባት ምክንያቶች

2 የተዛባ የተፈጥሮ ሃብት አስተዳደር
 ሀ የውሃ ሃብት
 ለ የደን ሃብት
 ሐ ለም አፈር
 መ አሣ፣ የዱር አውሬና የቤት እንስሳት
3 ጦርነትና ረሃብ
4 የተዛባ ፖሊሲ
5 የተዛባ ቴክኖሎጂ

6 ድኅነት
7 ጤንነትና ረሃብ
8 እንበጣና ረሃብ
፭ መደምደሚያ

## ፩ መንደርደሪያ

የረሃብ መሠረቱ የዕለት ጉርስን ሊያስገኙ የሚችሉ ተፈላጊ ነገሮች ያለመሟላት ነው። ረሃብን ያለመከላከልና ያለማስወገድ ጉዳይ በአሁኑ ዘመን የድህነትና የአስተዳደር ጉድለት ነፀብራቅ መሆኑ ግሃድ ነው። የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቱን ለማርካት የተለያዩ ዘዴዎችን ሲጠቀም ቆይቷል። የምግብ ፍላጎትን እስመልከቶም ፍራፍሬ ለቅሞ አውሬ አድኖ ተከፍሎ በልቶ ኖራል። ከዚያም ኅብረተሰብ እየሰፋ፣ እየተከፋፈለ በመሄዱና ፍላጎትም እየጨመረ በለመጣ አምርቶና አርብቶ መብላት ተጀመረ። ብሎም አምራችና በላተኛ ክፍል በለተከሰተ ለገበያ ማምረትና ገዝቶ መብላት ተስፋፋ። የዚህ አዝማሚያ ባለገንዘቡ ሲበላ ገንዘብ አልባው ጾም ማደር ሆነ። የጾም ማደር ለገንዘብ አልባው ብቻ ሳይሆን በበሽታ ለተጠቃው፣ ተፈጥሮ ምርቱን ላደበየበት፣ የሠላም ማጣት ማምረት ለከለከለው ወዘተ ሁሉ ደረሰው።

ረሃብ ከፍተኛው የምግብ እጥረት ደረጃ ነው። አንድ ሰው ረሃብ ደረጃ የሚደርሰው ለረዢም ጊዜ መሠረታዊ ምግቦች ሳያገኝ ቀርቶ፣ ተዳክሞ የራሱን የውስጥ ሰውነት መብላት ጀምሮ፣ መንምኖ ሞት አፋፍ ላይ ሲደርስ ነው። በዚህ ደረጃ ሰውነት በሽታን ለመከላከል ስለማይችልና ለህዋሳት ተፈላጊ ንጥረ ምግቦች ስለማይኖሩ ረሃብተኛው በመጨረሻ በሞት ይገላገላል።

ረሃብ ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር አብሮ ያደገ፣ የተፈጥሮና የፍጡራን ውስጅ መልሰም የፍጡራንን ህልውና የሚፈታተን ክስተት ነው። ረሃብ መሰረቱ ምግብ አለማግኘት ሲሆን ከምርት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው። ለአብዛኛው በኢኮኖሚ ለተዳከመው አርሶአደር የረሃብ መንስኤ ተብለው ከሚጠቀሱት የሚከተሉት ይገኙበቸዋል፦


1) የዝናብ በጊዜው አለመዝነብ
2) የማምረት ጉልበት ማነስ፤ ለምሳሌ በበሽታ፣ ማረሻ ባለማግኘት፣ ዘር ባለማግኘት፣ መሬት ባለማግኘት፣ በሰው ሃይል ማነስ ወዘተ…
3) የእርሻ ጊዜ ማነስ ወይም የርሻ ወራት ማለፍ፤ ለምሳሌ በተለያዩ ምክንያቶች ጊዜ መባከን፦ በስብሰባዎች መብዛት፣ ፍርድ ቤት መመላለስ፣ በዘመቻ፣ በርቀት ወዘተ…
4) ለቤተሰብ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ዋጋ መናርና እነዚህን ለመግዛት ምርትን ያለዋጋው መሸጥ፤
5) የመዋጮ፣ የቀረጥ ወዘተ… መብዛት፤

6) ለምርት አስፈላጊ ሁኔታዎች አለመሳካት፤ ለምሳሌ ድርቅ፣ ዶፍ፣ ውርጭ፣ አንበጣ፣ በረዶ፣ እሳት፣ ጦርነት ወዘተ።



ካርታ-ሀ


## አፍሪቃ - በድርቅ በመጠቃት ላይ ያሉ አገሮች



ካርታ-ክ



ካርታ ·ጠ



## ፪ ረሃብ በታሪክ

የተለያዩ አከባቢዎች በተለያየ ጊዜያት በመጠን የተለያዩ የረሃብ ዘመናት አሰልፈዋል። ዋንታዊ ተብለው ከሚነገሩለቸው ረሃቦች አንዱ ከስድስት ሺህ ዓመታት በፊት በድንጋይ ተቀርፃ የተገኘ ቢሆንም የረሃብ ስቃይ ፅሑፍ ከመጀመሩ በፊትም እንደነበር መገመት ይቻላል።[1]

በ100 ዓ.ም እና በ1921 ዓ.ም መካከል ቻይናን በ1828 ረሃቦች አጥቅተዋታል። ይህም ማለት በየአርባ ቀናቱ አንድ ረሃብ ይከሰት ነበር ማለት ነው።[2]

በአስራ አራተኛው መቶኛ ዘመን ከተላላፊ በሽታ ጋር በተያያዘ ረሃብ በአውሮጳ አርባ ስለት ሚሊዮን ሰዎች ሲሞቱ ሁለት ሰስተኛው የጣሊያን ተወላጅ ነበር።[3] በ1842 ገደማ የአየርላንድ የድንች በሽታ ባስከተለው ረሃብ አንድ ሚሊዮን ህዝብ ሲሞት የዚህ ኑ ያህሉ ተሰዷል።[4]

ዮሴፍ የሰባቱን ዓመታት የጥጋብና የሰባቱን ዓመታት ረሃብ ዘመን ሲተነብይ የምስሩ ፈርኦን አገሩ በረሃብ እንዳያልቅ እህል በጉተራ እንዲከዝን አዟል።[5]

በ1951-53 ዓ/ም በቻይና በሚስጢር የተያዘው ረሃብ እስከ 64 ሚሊዮን ህዝብ በመጨረስ በሃያኛው ክፍለ ዘመን ከፍተኛው ነው ይባላል።[6]

በአፍሪቃም ተመሳሳይ የረሃብ ክስተቶች በተለያዩ ጊዜያት ነበሩ፤ አብዛኛዎቹ በፅሑፍ ማህደር ስለአልሰፈሩ ያደረሱት ጉዳት ምን ያህል እንደሆነ መገመት ያስቸግራል።

በ1960-61 በናይጀሪያ አገር በባያፍራ እርስበርስ ጦርነት ያስከተለው ረሃብ እስከ አንድ ሚሊዮን ተኩል ህዝብ ጨርሷል።[7]

ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት ከሃያ የማያንሱ የአፍሪቃ አገሮች በረሃብ ተጠቅተዋል። ለረሃብ የተጋለጠውም ህዝብ ብዛት እስከ መቶ ሃምሳ ሚሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል። በጣም የተጠቃው የአፍሪቃ ምዕራብ ክፍል የሳሄል (SAHEL) ተብሎ የሚታወቀው የሞርታኒያ፣ ሴኔጋል፣ ቡርኪና ፋሶ፣ ቻድ፣ ኒዠርና ማሊ አከባቢ ሲሆን የዚሁ ወሳፈን ሱዳንን ኢትዮጵያንና ሶማሌን አደርሷል።

የሚቀጥለው የአፍሪቃ ካርታ በድርቅ በሃይል የተጠቁትን፣ በመጠኑ የተጠቁትንና እስከሁን ደህና የሆኑትን ያሳያል። እንደሚታየው ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በድርቅ ተጉድተዋል (ካርታ ሀ)

ከላይ ከተጠቀሱት የረሃብ ሁኔታዎች መነሻ ናቸው ተብለው ከሚነገርላቸው አስባቦች መካከል ድርቅ፣ ጦርነት፣ብዝበዛ፣ በሽታ፣ የአግዜር ቁጣ ወዘተ… ይገኙባቸዋል።

የአፍሪቃ አገሮች (አብዛኛውንም ከሰሃራ ምድረ በዳ ደቡብ የሚገኙት)

ከፍተኛ የውሃ ሃብት አላቸው። አብዛኛዎቹም የውሃ አካላት ዓመቱን በሙሉ ሳያቋርጡ የሚፈሱ ሆነው ስለሚገኙ የዘመኑ ረሃብ ሊበባስ የቻለበት ዋንኛ ምክንያት እነዚህን ወንዞች በሚገባ ባለመጠቀም የተነሳ መሆኑ ግልፅ ነው።

ሁለተኛው የአፍሪቃ ካርታ (ካርታ ለ) የሚያሳየው ታላላቆቹን የአፍሪቃ ወንዞች ነው። ካርታው እንደሚያሳየው አብዛኛዎቹ በድርቅና በረሃብ የተጠቁት አካባቢዎች በቂ የውሃ ሃብት ያላቸው መሆናቸውን ነው። ይህ የሚያመለክተው የረሃቡ ዋና ምክንያት ድርቅ ወይም የተፈጥሮ ሃብት መጓደል ሳይሆን የተፈጥሮሃብት በሚገባ ባለመጠቀም መሆኑ ነው።

በእንፃሩ እንደሚታየው የሰሜን አፍሪቃ በረሃማ አገሮች ወንዞችም ባይኖራቸው የረሃብና የድርቅን ስጋት የተለያዩ የተፈጥሮ ሃብቶችን በመጠቀም እንዳስወገዱ ነው።

## ፫ ረሃብ በኢትዮጵያ

በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ መጠን ያላቸው ረሃቦች ሳይታወቁ መኖራቸው ቢገመትም መዝገብ የያዘው ረሀብ በመጽሐፈ ስንክሳር(8) የተጠቀሰው የዘጠነኛው መቶ ዓመት ሲሆን እሱም በህዝብ ሐጢዓት የተነሳ እግዜር ተቆጥቶ ዝናብ ስለከለከለ ድርቅ ያስከተለው ነው። በ፲፮ኛው መቶ ዓመት እርግማን ያስከተለው ረሃብ ህዝብ እንደፈጀ ይኸው መፅሐፍ ይናገራል።

በዘመነ አምደፅዮንም (1306–1336) አሰቃቂ ረሃብ እንደነበር ይታወቃል።

በ1512–18 ፖርቱጋላዊው ተጓዥ ፍራንሲኮ አልቫሬዝ በትግራይ አንበጣ እህልና ቅጠሉን እንዳደበየውና ህዝብ በረሃብ እንደተጠቃ ፅፏል።

በ1500–32 በልብነድንግል ዘመን፣ በ1532–61 በገላውዴዎስ ዘመን እንዲሁ ረሃብ ነበር። በ1624–59፣ በ1739፣ በ1814 የአንበጣ ረሃብ ገብቷል። በ1264–65 ረሃብና ተላላፊ በሽታ በሃረር በርካታ ህዝብን ማጥፋቱ ይነገራል። በ1336–64 በሰይፈ ያሬድ ጊዜ በሽታና ረሃብ ገብቶ መላ ኢትዮጵያን አደብይቷል። በ1427–28 በሽታውና ረሃቡ በስፋት ይዞ የአብሲኒያን ህዝብ ከንቱሠ ጭምር ገድሏል።

ከ1600–1700 ዘጠኝ ታላላቅ ተላላፊ በሽታና ስድስት ከፍተኛ ረሃቦች በኢትዮጵያ ነበሩ።

ከሁሉም አልቆ በስፋትና በጥልቀት የተፃፈለትና የኢትዮጵያ ታላቁ ረሃብ ተብሎ የሚታወቀው በዳግማዊ ምኒሊክ ዘመን 1881–84 በድርቅ፣ በበሽታ፣ በአንበጣና በጦርነት ቁጥሩ ያልታወቀ ህዝብ የጨረሰው ነው። ይህንኑ ሲተርኩ የምኒሊኩ ፀሐፊ ትዕዛዝ ገብረስላሴ እንዲህ ሲሉ አስፍረውታል።(9) «በዚሁ ዘመን ከእግዜር መዓት ታዞ ላምና በሬ እየታመመ ያልቅ ጀመር፣ በዚያም ጊዜ አፄ ምኒሊክ በሬ ካለቀ እህል አይገኝም፣ እህል ከጠፋ ሰው አይቆይም፣ ይህ ዓመት በእንስሳ ብቻ አይቀርም ብለው የሸዋ ሰው በየአድባራቱ እየተሰበሰበ

እግዚአ በል ብለው እዋጅ አወጁ።»

«ከዚህ በኃላ በዘመኑ ማቴዎስ ሳሙ በሬው እልቶ እፄ ምኒሊክም በዚህ አዝነው ነበርና ሥርዓተ መንግሥት ለማድረግ እሳሰቡም፣ መዋረቢያና ደግ አስበጁ፣ ወታደሩም በሳገሩም እንዲቶፍር አደረጉ፣ በሬ ሰሳሰቀ ባህያና በበቅሎ በፈረስ ታረሰ፣»

«እናትና ልጅ የሚለያይ ብርቱ ረሃብ ሆነ፣ ፈረስ በቅሎ ተበላ፣ ከረሃቡ ከበሽታው የተረፈውን ጦር ፈጀው።»

በእፄ ኃይለሥላሴ ዘመን (የ1964ቱ) ረሃብ ከአስራ አራቱ አስሩን ክፍለተ አገራት ጉድቷል።{10} በወሎ ብቻ ከሁለት መቶ ሺህ ሰው በላይ በረሃብ አልቋል። ይህ ረሃብ ለ1966ቱ አብዮት ፍንዳታ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል። የወሎው ድርቅና ረሃብ ያስከተለው ዕልቂት በ1967 የመርማሪ ኮሚሺን እንዲቋቋም ረድቶ አንዳንድ ባለስልጣናት በሃላፊነት እስጠይቋል።

በኰሎኔል መንግስቱ ሃይለማሪያምም ዘመን በ1966 የቀጠለው ድርቅና ረሃብ በአሁኑ ጊዜ አብዛኛዎቹን ክፍለተ አገራት አዋቅቷል። በ1976/77 ስምንት ሚሊዮን የሚሆኑ ከመኖሪያቸው እንዲፈናቀሉ አድርጓል። ከዚህ ውስጥ ወደ ሚሊዮን የሚጠጉ ወደ ጎረቤት አገሮች ሲሰደዱ ሁለት መቶሺህ ህፃናት ያለወላጅ ቀርተዋል። ከሰባት መቶሺህ የማያንስ መሞቱ ይነገራል።{11}

በተከታታይ የታየው ረሃብ በ1976 ዓም ስድስት ሚሊዮን በ1977 ዓም አስር ሚሊዮን በ1978 ዓም ሰባት ሚሊዮን በ1979 ዓም ሰባት ሚሊዮን ህዝብ ዕርዳታ እንዲፈልጉ አድርጓል።{12} በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የተከሰተው የድርቅና የረሃብ ሁኔታ በዓለም ከታየው ሁሉ ታላቁና አስቃቂው ነው ይባላል።

## ፬ የረሃብ መንስኤዎች

ረሃብ የረዥም ጊዜና የተለያዩ ምክንያቶች ክስተት እንጅ በተናጠል የአንድ ነገር ውጤት ወይም በየተወሰነ ጊዜ ቀን ቆጥሮ የሚመጣ ነገር አይደለም።እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሃላ ቀር አካባቢዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የረሃብ ምክንያት ተብለው ከሚጠቀሱት የሚከተሉት ይገኛሉ።

1) የተዛባ የአየር ጠባይ (ዝናብ፣ ድርቅ፣ ሙቀት፣ በረዶ፣ ውርጭ…)
2) የተዛባ የተፈጥሮ ሃብት አስተዳደር (ውሃ፣ አፈር፣ ደን፣ ዱር አውሬ፣ ጉልበት…)
3) ጦርነት (የርስበርስ፣ የውጭ ጠለት፣ የወታደር ዘረፋ፣ የገበሬ ውትድርና…)
4) የተዛባ ፖሊሲ (የግብርና ድጋፍ፣ የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ መሬት ይዞታ፣ ሰፈራ…)
5) የተዛባ ቴክኖሎጂ (ማዳበሪያ፣ ድቀላ፣ ፀረ-በሽታ…)
6) ድህነት
7) በሽታ
8) እንበጣ፣ወዘተ

ከዚህ ቀጥሎ ከላይ የተዘረዘሩት በመጠኑ ይገለፃሉ።

## 1 የተዛባ የአየር ጠባይ

(ሀ) ዝናብና ድርቅ፦ በአሁኑ ጊዜ በብዙ አካባቢዎች አሳሳቢ ሆኖ የተገኘው ለረሃብ ዋና ምክንያት ተደርጎ የተወሰደው የዝናብ ሁኔታ ነው። የዝናብ ችግር ተብሎ የሚጠራው የዝናብ ጨርሶ መጥፋት ወይም ድርቅ፣ የዝናብ በተፈለገው ጊዜ በተፈለገው ቦታ በተፈለገው መጠን አለመምጣትና የዝናብ በብዛት መጣል ወይም ጐርፍ ናቸው።

ገበሬ ለእርሻው፣ ዘሩንና ከብት እርቢው ለስራ በዝናብ ላይ ይመካሉ። በኢትዮጵያ የተለያዩ የዝናብ ክፍለ አካባቢዎች ሲኖሩ ባአኪያቸው በዝናብ ላይ የተመሰረቱ የእርሻ ወራት አሉ። ዋናው የእርሻ ጊዜ ከሰኔ እስከ ነሐሴ የሚቆየው መኸር ተብሎ የሚታወቀው ገብስ፣ ስንዴ፣ ጤፍ ወዘተ የሚመረትበት ሲሆን መለስተኛ የእርሻ ጊዜ ከመጋቢት እስከ ግንቦት የሚቆየው በልግ ተብሎ የሚታወቀው ማሽላ፣ በቆሎ ወዘተ የሚመረትበት ነው።

ያለፉት ሃያ ዓመታት የዝናብ ሁኔታ በጣም ወላዋይ በመሆን ገበሬውን ችግር ውስጥ በመጣል ለልመና፣ ለስደት፣ ለስቃይ አብቅቶታል። በጣም የተጠቁ የሰሜኑና የምስራቁ አካባቢዎች ናቸው። የሰሜኑ አካባቢ ደግሞ አብዛኛው አምራች ገበሬ የሚገኝበት ነው።

በኢትዮጵያ ከ500 ሚሊሜትር ዝናብ መጠን በታች የሆኑ አካባቢዎች ደረቃማ በመሆን ለእርሻ አያመቹም። ለምሳሌ እንደ አዲስ አበባ ያሉ በታዎች በመካከለኛ ገምት በዓመት 1250 ሚሊሜትር መጠን ያገኙ ነበረ፣ እንደ አሥመራ ያሉ ደግሞ 450 ያገኛሉ። በጠቃላይ አብዛኛዎቹ አምራች አካባቢዎች ከ500 እስከ 1500 ሚሊሜትር ማግኘት ያስፈልጋቸዋል።

ከ1974 እስከ 1979 በሰኔና በሐምሌ ወራት በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ከተሞች የተመዘገበው የዝናብ መጠን እጅግ ዝቅተኛ ነበር። ይህም መጠን ለእርሻ ስለማይጠቅም ገበሬው በተከታታይ ችግር ውስጥ ወድቋል። እንደ ብሔራዊ አየር ምርመራ ድርጅት ዘገባ በሰኔና ሐምሌ 1979 የዝናብ ሁኔታ በግምት 80 ከመቶ የማያንሰው የአገሪቱ ምድር ለእርሻ ከሚፈለገው የዝናብ መጠን በታች እንደነበረው ያሳያል። {13}

በእንፃሩ ደግሞ የዝናብ መጥፋት እንዲህ ሁኖ ሳለ አልፎ አልፎ የሚመጣ ዝናብ ተጠራቅሞ ይጥል ይመስል ደፍ ይሆናል። የዚህ አይነት ዝናብም በንብረትና በሕይወት ላይ ከፍተኛ አደጋ ከማድረሱም በላይ ለም አፈር እየሸረሸረ በመውሰድ አካባቢውን የባሰ ምድረ በዳ ያደርገዋል። በተጨማሪም አንዳንድ በታዎች የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል የተገነባውን ልፍስፍስ መደቦችና ግድቦች ደዞ ይሄዳል። ይህ አይነቱ ሁኔታ ጉልቶ የታየበትም በነሐሴና መስከረም 1981 ዓም ሰሜን ክፍል የጣለው ዝናብ ሲሆን በአካባቢው ከፍተኛ ጉዳት አስከትሏል። የዓባይ ውሃ ሙላትም ሱዳንን በማጥለቅለቅ በሱዳን ታይቶ የማይታወቅ ከቁጥጥር

ውጭ የሆነ ሁኔታ ፈጥሯል።

(ለ) <u>የዝናብ መዛባት ምክንያቶች</u> ፡ ለዝናብ መዛባት የተለያዩ ምክንያቶች በብቸኝነትና ወይም በጋራ ሊጠቀሱ ይችላሉ።

እንደ ሃይማኖት መፃሕፍት ከሆነ የዝናብ መጥፋት በሰው ልጅ ጥፋተኝነት የተነሳ የሚከሰት የእግዚር ቁጣ ነው። በሳይንስ ደግሞ ከምድርና ከየብስ ወደ አየር የሚወጣው ውሃ አዘል ትነት ማነስ ወይም ጉም ሰርቶ ሳይቀዘቅዝ ሲቀር የሚከሰት ነው።

ለዝናብ መታወክ አንዱ ምክንያት የደን መጥፋት ነው። ደን ብዙ ውሃ አዘል ትነት ወደ አየር በማውጣት ተመልሶ ዝናብ ሆኖ እንዲወጣ ያደርጋል። የደን መጥፋት በዝናብ ላይ ቀፀበታዊ ተፅዕኖ ያደርጋል። በኢትዮጵያ በተከታታይ ከፍተኛ የደን መጥፋት ታይቷል። በአሁኑ ጊዜ ከኢትዮጵያ ምድር አራት ከመቶ ብቻ ነው በደን የተሸፈነው (ዘጠና ስድስት ከመቶው ዛፍ የሌለበት ነው ማለት ነው።) የዘመኑ ዝናብ መጥፋት ከዚሁ ምድረ በዳነት ጋር የተያያዘ መሆኑ ይነገራል።{14}

ሌላው የዝናብ መጥፋት ምክንያት «የካርቦንዳዮክሳይድ» ጋዝ በአየር ውስጥ ከመጠን በላይ መከማቸት ነው። «ካርቦንዳዮክሳይድ» ብዙ ነገሮች በተለያየ መንገዶች ሲቃጠሉ የሚፈጠር ጭስ ነው። ለምሳሌ እንጨት ሲነድ፣ መኪና ሞተር ሲንቀሳቀስ፣ ፋብሪካዎች ሲሰሩ፣ ሰው ወደውጭ ሲተነፍስ ወዘተ ካርቦንዳዮክሳይድ ይወጣል። አብዛኛውን «ካርቦንዳዮክሳይድ» አዝዕርቶች ለእድገታቸው ስለሚያስፈልጋቸው ይጠቀሙበታል። ነገር ግን የደን መጥፋትና የጋዙ መጠን መጨመር ከሞተሮች የሚወጣው ካርቦንዳዮክሳይድ በዓየር ላይ በብዛት እንዲከማች ስለሚሆን ውጤቱ ጋዙ በመሬት ዙሪያ ማንዣበብ ይሆናል። ይህም እንደጉም በምድር ዙሪያ የሚንዣበብ ጋዝ በተለምዶ ከመሬት የሚንፀባረቀን የፀሐይ ጮራ አፍኖ በመሬት ላይ ያስቀረዋል። በዚህ የተነሳ የመሬት ሙቀት እየጨመረ በመሄድ ጉም እንዳይቀዘቅዝ በማድረግና ጉምን በመበተን ዝናብ እንዳይኖር ያደርጋል። ይህም የታፈነ ሙቀት ክስተት «የአረንጓዴ ቤት ውጤት» «ግሪን ሃውስ ኢፌክት» ተብሎ የሚጠራው ነው።{15}

ለመሬት ሙቀት ብሎም ለዝናብ መዛባት ተጨማሪ አስተዋፅዖ የሚያደርገ የ«ኦዞን»(OZONE) ጋዝ ነው። ኦዞን የሚባለው «ኦክስጂን» መሰል ጋዝ በምድር ዙሪያ በመንሰፈፍ መሬትን ከፀሐይ ከሚመጣው መርዘኛ «አልትራ ቫዮሌት» (ULTRA VIOLET RAY) ጮራ በብዛት ከመጋለጥ ይከላከላል።

የ«ኦዞን» ከለላ ክሌለ የመሬት ሙቀት ከመጨመሩም በስተቀር ከፀሐይ የሚመጣው ጮራ ሲበዛ የቆዳ ካንሰርና ሌሎች ጉዳቶችን በአዝዕርት ላይ ያደርሳል። ለ«ኦዞን» ጋዝ መቀነስ ወይም መሳሳት አስተዋፅዖ ያደርጋሉ ተብለው የሚጠቀሱት ልዩ ልዩ ፋብሪካዎች የሚጠቀሙባቸው ኬሚካሎች ውጤቶች ናቸው። ከነዚህም ኬሚካሎች መካከል «ክሎሮፍሎሮካርበን»፣ «ሚቲልክሎሮፎርም» እና «ካርበንቴትራክሎራይድ» ይገኙባቸዋል።{16} በቴክኖሎጂ የቀደሙ አገሮች እነዚህን መሰል ኬሚካሎች

በመጠቀም በሰማይ ላይ የእዘን ከለሳን በማሰሳት ወይም በመቅደድ ዓለም ለመርዘኛው ሙራ እንዲጋለጥ ያደርጋሉ።

ሌሎች የተለያዩ የፋብሪካ ውጤቶች ወደአየር በመትነንና በመንሰፈፍ ከዝናብ ጋር በመቀላቀል አሲድ ዝናብ በመፍጠር መርዘኛ ሆነው በሕይወት ላይ ጉዳትን ያስከትላሉ፤ አዝዕርቶችም በቀላሉ ይጠፋሉ። በባህር ያሉ እንደ አሣ ያሉትንም ለምግብ የሚጠቀሙ ነገሮችም ይጉዳሉ። «አሲድ ዝናብ» በጊዜ ብዛት ደንን በመቀነስ፣ እርሻን በመመረዝ፣ የውሃ ነፍሳትን በመጉዳት ረሃብን የማስከተል ችሎታው በቀላሉ የሚታይ አይሆንም።(17) በዚህ የተነሳ በጀርመን፣ በካናዳና በሰሜን አሜሪካ በቁማቸው በመሞት ላይ ያሉ የዛፍ ዓይነቶች እንዳሉ ታውቋል።

በአፍሪቃ አህጉር በርካታ ፋብሪካዎች ስለሌሉ የነዚህ አይነት ጥሶች ችግር አነስተኛ ነው እንዳይባል በነፋስ እየታዘለ ያልተበከለው አካባቢ ሁሉ የመበከል ዕድሉ ትንሽ አይሆንም።

በመሰረቱ የዝናብ መታወክ ሰው አመጣሽ ክፍል ቢኖረውም የመሬት አቀማመጥ፣ የፀሐይ ሁኔታ የተሳልቀ እሰተ ጉመራዎች ክስተት በአጠቃላይም ከሰው ቁጥጥር ውጭም የሆኑ የተፈጥሮ ሁኔታዎች እንዳሉ መገንዘብ ያስፈልጋል። ይህም ሲባል እጅ አጣጥፎ በመቀመጥ የተፈጥሮና የስልጣኔ እስረኛ ሆኖ መቅረት ያስፈልጋል ማለት አይደለም። የሰው ልጅ ታሪክ ከአካባቢውና ከተፈጥሮ ሂደት ጋር በመታገልና ሀልውናውን ከማረጋገጥ ጋር የተሳሰረ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

## 2 <u>የተዛባ የተፈጥሮ ሃብት አስተዳደር</u>

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሃብት ከታደሉ ጥቂት አገሮች አንዷ ነበረች። በመሬት ስፋት፣ በህዝብ ብዛት፣ በዓየር ጠባይ፣ በመሬት አቀማመጥ፣በውሃ ሃብት፣ በዱር እረፅዋት፣ በከብት ሃብት፣ በአሣ፣ በባህር በሮች፣ ወዘተ የሚወደደራት ጥቂቶች ነበሩ።

(ሀ) <u>የውሃ ሃብት፦</u> ኢትዮጵያ በርካታ ወንዞችና ሃይቆች አሏት። ዓመቱን ሙሉ ሳያቋርጡ የሚፈሱ ብዙ ናቸው።

የሚቀጥለው የኢትዮጵያ ካርታ (ካርታ ሐ) የሚያሳየው የታወቁትን ትላልቅና ዓመቱን ሙሉ ሳያቋርጡ የሚፈሱትን ነው። እዚህ ካርታ ላይ ያልተጠቀሱ በአካባቢያቸው የታወቁና እንዲሁም ሳያቋርጡ የሚፈሱትን ለአንባቢያን ትቸዋለሁ።

አስር ከመቶ የሆነው የአገሪቱ ምድር ማለትም መቶ ሃያ ሺህ ካሬ ኪሎሜትር የሚሆነው የውሃ ሽፋን ያለው ነው። የወንዞችም አቀማመጥ የክፍለተ አገራቱ ድንበር እንዲሆኑ በመደረግ ለሁሉም አካባቢዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ይገኛሉ። ዋንኛ ተብለው ከሚታወቁት ወንዞች ጥቁር

ዓባይ፣ ተከዜ፣ ባሮና አካቦ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌ፣ አዋሽ፣ አሞና ባርከ ይገኙበቸዋል። በተጨማሪም አስራ አራት ሃይቆች አሉ።

ኢትዮጵያ በዓመት ከአንድ መቶ ቢሊዮን ኩብ የማያንስ ውሃ ወደ ውጭ አገሮች ታፈሳለች። የአሞ ወንዝ በዓመት አስራ አምስት ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ ወደ ቱርከና (ሩዶልፍ ተብሎ ይታወቅ የነበረው) ሃይቅ ይዞ ይሄዳል። ጥቁር አባይ ደግሞ አርባ ስድስት ቢሊዮን ኩብ አፈር አዘል ውሃ ይዞ ወደ ሱዳንና ግብፅ ይሄዳል።{18}

የግብፅ ህልውና፣ ስልጣኔና ታሪክ የተመሠረተው አብዛኛውን በጥቁር አባይ ውሃ ነው። የውሃን ጥቅም በመገንዘብም ውሃ እንዳይባክን፣ ለክፉ ቀን እንዲውል በማሰብ ግብፃውያን አባይን በመገደብ ታላቁን ሰው ሰራሽ ሃይቅ (ናስር ሃይቅ ተብሎ የሚታወቀውን) ከአንድ ቢሊዮን ዶላር ያላነሰ ገንዘብ በማውጣት ጥቅም ላይ አውለውታል። በዚህም የተነሳ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመስኖ ለእርሻ ውሏል። ከዚህም በስተቀር ግድቡ ለኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ አገልግሏል። ይህም ሲሆን ግድቡ የፈጠራቸው ችግሮች አሉ። ህዝብን ማፈናቀሉ፣ እንደ ቢላርዚያና አንኮሴርኪያሲስ ዓይነት አባዋራ በሽታ ማስፋፋቱ፣ የጨው መጠንን በአካባቢው መሬት ላይ መጨመሩ፣ ወዘተ… በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም።{19}

እንደሊብያ ያሉ በረሃ ውስጥ የሚገኙ አካባቢዎችም ተፈጥሮን ለመቋቋም ልዩ ጥረት በማድረግ አንዳንድ ቆራጥ እርምጃዎችን ወስደዋል። ሊብያ በ1976 ዓም የከርሰምድር ውሃን በመጠቀም ውሃው በመስኖ አካባቢውን እንዲያገለግል ሺህ ዘጠኝ መቶ ኪሎ ሜትር ቧንቧ በመዘርጋት ብዙ መሬት ለእርሻ እንዲውል ተደርጓል። ይህ ሰው ሰራሽ ወንዝ በስራ ለማዋል አስራ አንድ ቢሊዮን ዶላር ወጭ ተደርጓል ይባላል።{20}

በኢትዮጵያም በቅርቡ የአዋሽ መስኖ እቅድ ዘጠኝ መቶ የአፋር ዘላን ቤተሰቦችን በሁለት ሺህ አምስት መቶ ሄክታር መሬት ላይ በማስፈር አስር ሺህ ሄክታር ደግሞ ለግጦሽ እንዲውል አድርጓል። በኦጋዴንም በዋቢ ሸበሌ ወንዝ በመጠቀም 30,000 የሚሆኑ አስፍራል። 5000 ሄክታር የሚሆን ለእርሻ ውሏል።{21}

በኢትዮጵያ በመስኖ ሊለማ ከሚችለው መሬት ውስጥ አራት ከመቶ ብቻ ሲለማ ዘጠና ስድስት ከመቶው እንዲሁ ቁጭ ብሏል።

ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ በኢትዮጵያ ለመስኖ ሊውሉ የሚችሉትን የውሃ አካላትና ሊያለሙ የሚችሉትን መሬት መጠን ይዘረዝራል።{22}

## ለመስኖ ሊውል የሚችልና የዋለ መሬት መጠን (በሄክታር)

| የውሃ ምንጭ | በመስኖ ሊለማ የሚችል | በመስኖ የለማ | ጥቅም ላይ ያልዋለ |
|---|---|---|---|
| ባሮና አኮቦ | 1,000,000 | 0 | 100% |
| ጥቁር አባይ | 581,000 | 0 | 100% |
| ተከዜ፣ባርካ፣ጋሽ፣መረብ | 172,000 | 15,000 | 91% |
| አዋሽ | 162,000 | 0 | 100% |
| ዋቢ ሸበሌ | 153,000 | 65,000 | 48% |
| ሃይቆች | 83,000 | 2,000 | 98% |
| ገናሌ፣ዳዋ | 72,000 | 7,000 | 90% |
| ጠቅላላ | 25,000 | 0 | 100% |
| | 2,248,000 | 89,000 | 96% |

የኢትዮጵያ ሰሜናዊ መከከለኛ አካባቢዎች አቀማመጥ ከረብታማና ተራራማ ስለሆኑ ብዙዎችን ወንዞች በቀላሉ መጠቀም አስቸጋሪ ይሆናል። በአንፃሩ ደግሞ እንዲህ አይነቶች ወንዞች ግፊት ስለሚኖራቸው የኤሌክትሪክ ሃይል ለማመንጨት ይረዳል። መልሰ ይህን ሃይል በመጠቀም ውሃው ወደ ሌሎች ደረቃማ አከባቢዎች እንዲደርስ ማድረግም ይቻላል። ለዚህ ሁሉ በመጀመሪያ በጉ ፈቃድ፣ አማዳፊ ሁኔታዎችን ማወቅ፣ ገንዘብን በተገቢ በታ ማዋልን፣ ዕውቀትን ወዘተ ይጠይቃል።

(ለ) <u>የደን ሃብት</u>፦ የደን አይነት የተለያየና ሰፊ ጠቀሜታ ያለው ነው። በቤት ክልል የእንጨት ምንጭ በመሆን ለማገዶ፣ ለከሰል፣ ለቤት መስሪያ፣ ለቤት ዕቃዎች መስሪያ፣ ወዘተ ያገለግላል።

በእርሻ አከባቢ ደግሞ አፈር በጐርፍ እንዳይሸረሸር፣ የጐርፍ ፍጥነት በመግታት ውሃው በአለበት እንዲረጋ ለማድረግ፣ ለአንዳንድ ተክሎች ጥላና ከለላ ይሆናል። የኦክስጅን ጋዝና ትነትን በማውጣት የአየር ሚዛን እንዳይዛባ ይረዳል። ለዝናብ መፈጠርም ምክንያት ይሆናል። በልዩ ልዩ ሁኔታዎች የሚፈጠርን የካርቦንዳዮክሳይድ ጋዝ በመጠቀም በአየር ላይ የካርቦንዳዮክሳይድ መጠን እንዳይበዛ ይከላከላል። የዱር አውሬዎች መጠለያና መኖሪያም ነው።

አንዳንድ ዓይነት የደን ተክሎች የላስቲክ፣ የወረቀት፣ የዕጣን፣ የቅመማቅመም፣ የመድኃኒት ምንጭ በመሆንና የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት ይረዳሉ።

ከላይ የተጠቀሱት የደን ጥቅሞች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለአገር እድገት፣ ለረሃብ መኖርና አለመኖር ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ።

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ የደን መጠን የመነመነ ነው። አብዛኛው ደን በደቡብና በምዕራብ ክፍል ሲሆን የዚህ አከባቢ የዝናብ መጠን ከደኑ የተነሰ

የተሸለና ጊዜውን የጠበቀ ነው።

ሃያኛው መቶ ዓመት ሲጀምር (ከሰማኒያ ዓመት በፊት ገደማ) የኢትዮጵያ ምድር አርባ ከመቶው ደናማ ነበር። ከአርባ ዓመትም በፊት (ማለት በ1940 ገደማ) ይህ መጠን ወደ ሃያ ከመቶ ደርሶ አሁን ግን ከአራት ከመቶ የሚያንስ ነው በደን የተሸፈነው።{23} የደን ሽፋን በኢትዮጵያ በዓመት ከሁለት መቶ ሺህ ሄክታር እየቀነሰ ነው ያለው። በልዩ ልዩ ቦታዎች የዛፍ ተከላ ሥራዎችም ቢካሄዱም ቅሉ ተገቢው እንክብካቤ ባለመኖሩ ከተተከለው ሰባት ከመቶ ብቻ ነው የመፅደቅ አዝማሚያ ያሰየው።

ቀጥሎ ያለው የኢትዮጵያ ካርታ (ካርታ መ) የሚያሰየው ከዚህ በፊት የነበረውንና አሁን የቀረውን የደን ሽፋን ነው። በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ ለምልክት እንኳ የሚቀር የደን መጠን እንደማይኖር መገመት ይቻላል።

የደን አያያዝን፣አጠባበቅንና ልማትን በሚመለከት በተለያዩ አገሮች የተለያዩ ድንጋጌዎች ቢደረጉም አብዛኛዎቹ ከተግባራዊነታቸው ይልቅ ስማዊነታቸው ያይላል። በኢትዮጵያም የደን ልማት ቢሮ በተለያየ መልክ ተቋቁሞ እንደነበር ቢታወቅም አብዛኛው ትኩረት የደን ልማት ከቀጥተኛና ጠባብ የገቢ ምንጭነት አንፃር እንጅ ደን አስተዋፅዖ ሊያደርግ የሚችልባቸውን የተለያዩ ገፅታዎች በስፋትና በጥልቀት በማጤን አይመስልም። በቅርቡ ለሰፈራ፣ የግለሰብንም ሆነ የመንግሥት እርሻን ለመፍጠርና ለማስፋፋት ሲባል የሚወሰደው የደን ማጥፋት ዘመቻ ወደፊት ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት በመገምገም አይመስልም።

የደን ሁኔታ ጉዳይ እንዲህ ጉልቶ ባላሳሰበበትና ኢትዮጵያም ደናማ በነበረችበት ዘመን እንኳ ሳይቀር አፄ ሚኒሊክ በአገሩ የዛፍ መቀነስን ሲያዩ ይህንን ለመቆጣጠር አዋጅ አስነግረዋል። አዋጁም በዶ መሬት ይዞ የማይሰራበት ከፍተኛ ቀረጥ እንዲከፍል፣ ዛፍ የተከለ ግን ከቀረጥ ነፃ እንዲሆን የሚያደርግ ነበር። ሕዝቡም በዚህ ተገፋፍቶ ዛፍ መትከል እንደጀመረ ይታወቃል።

መፅሐፍ ቅዱስም የደንን ጠቀሜታ በመገንዘብ ዛፎች እንዳይቆረጡ፣ እንዳይጠፉ በመምከር ለሰው ህይወት ወሳኝና ምግብ ለጋሽ እንደሆኑ ይናገራል።

የደን ተከላ በብዙ አገሮች እየተካሄደ ቢሆንም፣ በስፋት የጠፋ ደንን መተካት አስቸጋሪ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ የሚተከለው የዘር ዓይነት አዲስ ከመሆኑ የተነሳ ዘላቂነቱ ያጠያይቃል። አብዛኛዎቹ ዘሮች የተሻሻሉ የሚባሉ፣ ለመብቀል ጊዜ የማይወስዱ ለደረቃማ አካባቢዎች የሚሆኑ ናቸው ይባላል። ይህ በመሠረቱ ጥሩ አስተዋፅዖ ቢሆንም ነባር ዘሮች በጊዜ ብዛት የአካባቢውን በሽታ፣ ድርቅ፣ ሙቀት፣ ቁር፣ ተባይ ወዘተ ሁኔታ የመቋቋም ችሎታ ስላዳበሩ ለነዚህም በተመክሮ ለበለፀጉ ዘሮች ተገቢ ቦታ መስጠት ያስፈልጋል።በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች በአሁኑ ጊዜ የደን ወደማ ለዘር እንኳ የሚተርፍ ፍሬ ያስቀረ አይመስልም። ብዙ ሌሎች አካባቢዎች የማይገኙ የዛፍ አይነቶች በጅምላ

መጥፋት የዘሮቹ አይነት ከምድር ገፅታ መጥፋት ማለት ነው። ይህም ማለት ብዙ ሚሊዮን ዓመት ያተረፈውን የዘር ዕድገት ውጤት ማደብየት ነው።(24) መልሰም መተከት አይቻልም። ለዚህ ነው ነባር ዘሮች ተመልሰው እንዲረቡ የሚባለው። አዲስ ዘሮች አዲስ ችግር ይኖራቸዋል።

የደን መውደምን ለመቆጣጠር ደንን የሚፈልጉና የሚያጠፉ ሁኔታዎች መርምሮ አመች መፍትሄ መፈለግ ተገቢ ነው። ለደን መጥፋት ወይም መቀነስ ምክንያቶች የተለያዩ ቢሆንም የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ይሆናሉ።

የከተማዎችና የመንደሮች መፈጠር/መስፋፋት ልዩ ልዩ የእንጨት አስተዋፅዖ ስለሚጠይቁ ይህ አንዱና ዋነኛው የደን ጠር ይሆናል።

መንግሥት ሆነ ግለሰቦችም የእርሻ መሬትን ለማስፋት ብዙ ደኖች አጥፍተዋል።

የተለያዩ ጦርነቶች ጠላት የተሸሸገበትን ቦታ ለማጥፋት፣ መሸሸጊያ ለማሳጣት፣ ያለፍርሃት ወደፊት ለመግፋት፣ የጠላትና የአከባቢውን ኢኮኖሚ/እርሻ ለማውደም በቦምብና በእሳት ብዙ ደኖች አጥፍተዋል። በዓየር መቀትና ድርቅ፣ በስህተት፣ በበረሃ የተፈጥሮ እሳት፣ ገበሬዎች ለእርሻ ዝግጅት በሚያደርጉት ቃጠሎ የተነሳ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ሰደድ እሳት ብዙ ደን ያጠፋል።

እንደነዚህ ዓይነት ሁኔታዎችን ለመግታት ተገቢውን ቁጥጥርና አገልግሎት ማበርከት የሕዝብ ተሳትፎ ማስተባበር ሠላም መገንባት የመንግሥት ሃላፊነት ነው።


(ሐ) <u>ለም አፈር</u> :- አፈር ለእርሻ ወሳኝ ነገር ነው፣ የለም አፈር አለመኖር ወይም ማነስ የእርሻውን ውጤትና ዓይነት ይወስናል። ዝናብ እንኳን እንደልብ ቢኖር ተገቢው አይነት አፈር ከልኖረ ውጤቱ ረሃብ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ከረብታማ አከባቢዎች በጣም ብዙ ለም አፈር በወንዝና በዝናብ እየተሸረሸረበቻው አብዛኛዎቹ በታዎች ምድረ በዳነት እያስፈራቸው ይገኛሉ። ይህ አይነቱ ሁኔታ ሊገታ ከሚችልበት ዘዴዎች ለምሳሌ አፈር ከሌላ ባታ አምጥቶ መጨመር፣ መሬትን በተከታታይ ከማረስ መቆጠብ ወይም ማሳደር፣ ዛፍን በመትከል ሽርሸራን መቀነስ፣ ለመሬት ለምነት አስተዋፅዖ የሚያደርጉ እፅዋት መዝራት ወይም እያቀላቀሉ መትከል ይገኙበቻዋል።

በኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በዓመት 1.6 ቢሊዮን ቶን ለም አፈር በውሃና በነፋስ ይሄዳል። ከአንድ ሄክታር መሃል አገር መሬት በዓመት አርባ ቶን ለም አፈር እየተሸረሸረ ይሄዳል።(25)

እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ዘጠና በመቶው ህዝብ በግብርና የሚተዳደርና ኢኮኖሚያቸው በእርሻ ላይ በመሠረቱ አገሮች የዚህ አይነቱ ያልተገታ የለም አፈር ወደ ውጭ መሄድ እጅግ በጣም አሳሳቢና መልሶ መተከት ወይም ማቋቋም የማይቻል ሁኔታ ይሆናል። ይህም መፍትሄ አልባ ወደ ሆነ ረሃብና

ካርታ-፴




( " The Challenges of Drought, Relief & Rehabilitation Commission, Addis Ababa, 1985, ገ.45 " ) ላይ የተመሠረተ

ጉዳት ያደርሳል። እንዲህ አድርጎ ያመለጠን ለም አፈር በሚገባ ተግባር ላይ ሰግኖአል የሕዝቦቻቸውን ህልውናና ኢኮኖሚያቸውን ከገነቡት መካከል ግብፅ እንደ ጥሩ ምሳሌ የምትጠቀስ ናት።

የአፈርን ጠቃሚነት ሊጎዱ የሚችሉ ልዩ ልዩ ነገሮች ቢኖሩም በአሁኑ ጊዜ አሳሳቢ እየሆነ የመጣው «የአሲድ ዝናብ» (ACID RAIN) ነው። «አሲድ ዝናብ» ልዩ ልዩ የፋብሪካ ጭሶች (ለምሳሌ «ሰልፈር ዳይኦክሳይድ» SULFURDIOXIDE፣ «ናይትሮጂን ዳይኦክሳይድ» NITROGEN DIOXIDE ወዘተ) ከአየር ጋር በመቀላቀልና መልካቸውን በመቀየር ወደ አሲድነት ሲቀየሩ የሚከሰት ነው። እነዚህም እንደ «ናይትሪክ አሲድ» (NITRIC ACID) «ሰልፍዩሪክ አሲድ» (SULFURIC ACID) ያሉት አሲዶች በዝናብ በመታጠብ ምድር ላይ በማረፍ አዝዕርትን፣ ነፍሳትን፣ ሰውን፣ ይጎዳሉ/ያቃጥላሉ። ከአፈር ጋርም በመቀላቀል ለም አፈርን ከመመረዝና ጥቅም አልባ ከማድረጋቸው በስተቀር ለምርት የሚያስፈልጉ ነፍሳትን ይገድላሉ።(26) እንደ ኢትዮጵያ ያሉት ብዙ ፋብሪካዎች የሌሉአቸው ከዚህ አደጋ ነፃ ሊሆኑ ይችላሉ ቢባልም፣ በተለያዩ ሁኔታዎች የተበከለ ዓየር በነፋስ ሃይል ከአንዱ ክፍለ ዓለም ወደ ሌላ በቀላሉ ስለሚዳረስ ችግሩ ዓለም አቀፍ በመሆን ሁሉንም አገሮች ሊጎዳ እንደሚችል መገመት ይቻላል። ይህ ቴክኖሎጂ የወለደው ከስተት ወደፊት ጉልተው የሚታዩና አሳሳቢ አደጋዎች ማስከተላቸው አይቀርም። የመሬትም እንደዚህ መመረዝ ለረሃብ አስተዋፅዖ በቀጥታ እንደሚያደርግ ግልፅ ነው። ይህ ችግር በአሁኑ ጊዜ በካናዳ፣ በአሜሪካና በአውሮጳ እንደዋና አሳሳቢ ጉዳይ ተወስዷል። ሌሎች የሶስተኛ ዓለም አበላት ግን ብዙም የመመርመሪያ መሳሪያ ስለማይኖራቸው ጥናቱም ብዙ ገንዝብና ዕውቀት ስለሚጠይቅ፣ አልፎም ከእፍንጫ አርቆ መመልከት እምብዛም ስለሆነ እንዲህ መሰሎችን ነገሮች አናስተናግድም።

(መ) አሣ፣ የዱር አውሬና የቤት እንስሳት ፦ ስለረሃብ ከተነገረ አሣና የዱር አውሬዎች የሚያደርጉት አስተዋፅዖ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም። እንደ ቻይና፣ ጃፓን፣ ኮርያ ወዘተ ያሉት በህዝብ ብዛታቸው የዓለም ሁለት ሶስተኛ ገደማ የያዙ ዋናና ተወዳጅ የምግብ ዓይነታቸው ከባሕር የሚገኙ እንደ አሣ፣ ሎብስተር፣ ሽሪምፕ ወዘተ ያሉ ናቸው። ስለዚህም የእርሻ ትኩረታቸው በዚህም ጭምር ነው። ስለሆነም በመሬት ላይ ብቻ ተስፋ አድርገው በዝናብና በድርቅ ተጎድተው ለረሃብ እጅ አልሰጡም።

ኢትዮጵያ ቀንደኛ የረሃብ እስረኛ ብትባልም ያላት የባሕር ምግብ ሃብት ከፍተኛ ነው።

በቀይ ባሕር ዘጠና ሺህ ካሬ ኪሎሜትር አሣና ተመሳሳይ ለምግብ ሊውሉ የሚችሉ አሣ መሰል ነገሮች ሊጠመዱበት የሚችሉ ክልል አላት። በዓመት ሊጠመድ የሚችለው የአሣ መጠን 66,000 ቶን ነው ይባላል። በሸምቅ ሸልቆ ሃይቆችም ሃያ ስድስት ሺህ ቶን አሣ ሊጠመድ ይችላል። ነገር ግን አብዛኛው ህዝብ አሣና ተመሳሳይ ምግቦች አዘውታሪ አይደለም ቢባልም፣ ተገቢው

ትምህርትና እርዳታ ቢሰጠው ተቀባይነት ያገኛል። በመሠረቱ አሣ በአልሚ ምግብነቱ የታወቀ ነው። ከዚህም አልፎ በዓለም ገበያ ከፍተኛ ተፈላጊነት ስለአለው ጥሩ የውጭ ምንዛሪ ማስገኛ ሊሆን ይችላል።

የዱር አውሬ ከደን መኖር ጋር የተዛመደ ነው። የደን መጥፋት ብዙ የዱር አውሬዎች እንዲያልቁ ወይም አገር ጥለው ወደ ጐረቤት አገሮች እንዲሰደዱ አድርጓል። የኬንያ የዱር አውሬ ፓርክ ኢትዮጵያን ለቀው በሄዱ እንስሳት እያደገ እንደሄደ ይነገራል። የዱር አውሬዎች ለቱሪስት መሳቢያ ከመሆኑም በስተቀር በተለያዩ አከባቢዎች እንደየአይነታቸው ለምግብነት እየታደኑ ይውላሉ። የቤት እንስሳትን ማለትም ላምን፣ በሬን፣ ፍየልን፣ በግን፣ ዶሮን ወዘተ አስመልክቶም ኢትዮጵያ በዓለም ታድለዋል ከሚባሉት ጥቂት አገሮች መካከል ነበረች። የከብትን ብዛት በሚመለከት በዓለም አስረኝነቱን ስትይዝ፣ በአፍሪቃ ተወዳዳሪ የላትም። ከላይ የተጠቀሱት እንስሳት ሥጋ ከመስገባቸው በስተቀር የወተት፣ የቅቤ፣ የእንቁላል፣ የቆዳ ወዘተ ምንጮች ናቸው። በአሁኑ ጊዜ የሚታየው ድርቅ ግን ትናንሽ ኩሬዎች በማድረቅና ሣርን በማጥፋት ከፍተኛ አደጋ እያደረሰ ነው። እንደሰው እንስሳውም ለረሃብና ለበታይ ተጋልጧል።

## 3— ጦርነትና ረሃብ

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ «ኋላቀርና ድሃ» አገሮች ጦርነትና ሠላም ማጣት ዋንኛ ሰው ሰራሽ የረሃብ፣ የድርቅና የድህነት ምክንያት ነው። ጦርነት የሰውንና የእንስሳትን ህይወት በማጥፋት፣ ገበሬውንና ሌላውን ጉበዛዝት ከሥራው በማፈናቀልና በእርስ በርስ መጪራረስ ጦርነት በመማገድ የተፈጥሮ ሃብትን (ጫካን፣ ሳርን፣ ውሃን፣ አፈርን ወዘተ) በእሳት በቦምብና በመርዝ በማጥፋት፣ ለዕድገት ሊውል የሚገባን ገንዘብ ለጦር መሳሪያና ለወታደር ያለመጠን በማባከን፣ ሠላማዊ ህዝብ ንብረቱን በትኖ ከመኖሪያው እንዲፈናቀል በማድረግ፣ ህዝቡን በልዩ ልዩ መዋጮ በማመንመን፣ ቁስለኛና አካለ ስንኩላንን በማብዛት፣ ትዳርን በማፍረስ፣ አባት አጥ ልጆችንና ባልአልባ ሴቶችን በመፍጠር በተለያዩ ቀጥተኛና

ተዘዋዋሪ መንገዶች ችግርን፣ ረሃብን ድርቅን ያስከትላል።

በአሁኑ ጊዜ በተጨባጭ እንደሚታየው ድርቅና ረሃብ ያጠቃቸው አብዛኛዎቹ የአፍሪቃ አገሮች ጦርነትና ተደጋጋሚ መፈንቅለ መንግሥት ያጠቃቸው ሁነው እናገኛለን።

በደቡብ ምስራቅ እስያ በካምፑቺያ በ1971 የታየው የምግብ መጥፋት ምክንያት ከዚያ ጊዜ አስር ዓመት በፊት ሳይቋረጥ የተካሄደው ጦርነት ያስከተለው መዘዝ ነበር። በ1975-77 በቻድ፣ በአንጎላ፣በኢትዮጵያ በሱዳን፣ በሞዛምቢክ የታየው የድርቅና የረሃብ ሁኔታ ከእርስ በርስ ጦርነት ጋር የገጠመ ነበር።

በተለይ በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምረው የተመዘገቡ ረሃቦች ከጦርነትና ከወታደር ዝርፊያ ጋር የተያያዙ ነበሩ። ህዝቡ በዘመቻና በጦር ዝግጅት ጊዜ ወታደሩን የመመገብ ግዴታ ይደረግበት ነበር። ዘመናዊ ውትድርና ከዚህ ዓይነት አስተዳደር የሚለየው የዘመኑ ወታደር ደሞዝ መከፈሉና ህዝቡ ይህን ደሞዝ በተዘዋዋሪ መንገድ ለመንግሥት በተለያዩ ቀረጦች ማስገባቱ ነው።

አፄ ምኒሊክ በ1881 በአፄ ዮሐንስ ላይ ባወጁት ክተት አዋጅ ሲናገሩ (29):- «ነገር ግን ከሠራዊት ብዛት የተነሣ አገር እንዳይበድልና እንዳይራብ እኩሌታውን ጦር ወደ ወሎ እኩሌታውን ቸሖ ሰደውት ተቀምጦ ነበር።» «ትግሮች ግን ከመተማ ወጥተው ያፄ ዮሐንስን ልጅ ራስ መንገሻን ይዘው ትግሬ ላይ እንደሸፍታ ሆነው ነበር። ስለዚህ አፄ ምኒሊክ ወደ ትግሬ ዘመቻ አሰቡ፣ ወዳጆቻቸውንም መኳንንቱን አስጠርተው ጊዜው ረሃብ ሆነ፣ እንዳልቀር እርስ በርሳቸው ትግሮች ጡዋት ማታ እየተዋጉ ሰውም መኳንንቱም አለቀ፤ እንዳልዘምት ሰው በሬው አልቋል ድሃው ይጉዳብኛል ብለው አማከሯቸው... መኳንንቱም ሰርዓተ መንግሥት አድርሰው ወደ ትግሬ ይዝመቱ ብለው መከሩ፣ ለዚህም መሰናደው እጅግ ብዙ ነበር።»

«በትግሬ አገሩ ሁሉ ገብር የሚዘረፍ ታጥቶ ሠራዊቱ ተርቦ ነበር።»

«ሠራዊቱ ከአምባው ከዋሻው እየገባ እየተታኰሰ እህሉን ዘረፈው»

«አፄ ዮሐንስ ጉጃምን ወግተውት ነበርና በዚህ ዘመን ይልቁንም ረሃብ

በ ጉጃም ፀና»

«በዚህ ዘመን የራስ መኰንን ሰዎች ከሐረርጌ ውጋዴን ከሚባለው አገር ዘምተው ብዙ ሰምና በሬ አስገብረው ከሐረርጌ ገቡ፤ ራስ መኰንንም በኢትዮጵያ ሰምና በሬ ታጥቶ አገሩ ውድማ እንደሆነ ያውቃልና ለጌታዬ ለንጉሠ ነገሥት ምኒሊክ ልርዳ ብሎ አምስ ሸህ በሬ አምስት ሸህ ሰም ወደ እንከበር ላከ»

ከዚህ ላይ የተጠቀሰው በአፄ ምኒሊክ ጊዜ ጦርነትና ዘመቻ ምን ያህል ለረሃብ መነሻና መጨረሻ እንደሆነ ለማሳየት ነው። መጨረሻውና ውጤቱም የኢትዮጵያ ታላቁ ረሃብ ተብሎ የታወቀው በ1881-84 የነበረውና የኢትዮጵያ አንድ ሶስተኛ ህዝብ ፈጅቷል የሚባለው ነው።

እንደ አለቃ ለማ አፃፃፍ በ1881-84 ጉጃምን ያወደመው ረሃብ በከፊል የ1879ኙ የአፄ ዮሐንስ ዘመቻ ባስከተለው የከብትና የሰው እልቂት ነበር።(30)

«የዮሐንስ ጦር ለሰውም ሆነ ለከብቱ በፍፁም ርህራሄ አላሳየም»

«የሱዳኑ መሐዲ ጦር በምዕራብ የጉንደርን አካባቢ አወደመው፣ አፄ ዮሐንስ የጉጃም ንጉሥ ተክለሃይማኖትና የሸዋው ምኒሊክ እያሴሩብኝ ናቸው ብለው በመጠርጠር ሊቀጧቸው በመፈለግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ጦር እንዲዘምት አደረጉ። ዘማቹም ያለፈበትን አገር ሁሉ በላው፣ ከዚህ ሁኔታ ለጥቆ ነበር ታላቁ ረሃብ የመጣው»

ፖንክረስት ወታደርንና አንበጣን ሲያወዳድር እንዲህ ብሏል፦ «አንበጣው በሜዳ ያለውን ነው የሚያጠፋ፣ ወታደር ግን የሜዳውን ያጠፋል ከቤት ያለውንም ይዘርፋል።»

ከላይ የተጠቀሱት የጦርነት፣ የዘረፋ፣ የረሃብ ሁኔታዎች በመጠንና በስፋት እየጨመሩ በአፄ ሃይለስላሴና በኰለኔል መንግስቱም ዘመነ አገዛዝ ቀጥለዋል። በኢትዮጵያ ድርቅ አጠቃቸው ከሚባሉት ዋና ዋና ስፍራዎች በአሁኑ ጊዜ ልዩ ልዩ የትግል እንቅስቃሴ የሚደረግባቸው ሆነው ይገኛሉ።

በኤርትራ፣ በትግራይ፣ በጉንደር፣ በወሎ፣ በአጋዴን የተለያዩ አካባቢዎች የሚታየው የድርቅና የረሃብ ሁኔታ የዘመቻ፣ የጦርነት፣ የሠላም መታወክ፣

የስደት ወዘተ ዋንኛ ውጤት ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት በተለያዩ አካባቢዎች በመታየት ላይ ያለው የጦርነት እንቅስቃሴ ከፍተኛ ነው። በ 1968 ዓም በሶማሌና በኢትዮጵያ መካከል የተካሄደው ጦርነት ከሁለቱ ወገን ያደረሰው የህይወት፣ የንብረትና የተፈጥሮ ሃብት ጥፋት ቀላል አልነበረም። በሃረርጌ ክፍለ ግዛት የደረሰው ጉዳት መጠን ከሃምሳ ሚሊዮን ብር በላይ ይገመታል። የብዙ ሽህ ዘለን ህይወትን ለማዳን ተብሎ የተሠራ የመስኖ ግድብ ከአገልግሎት ውጭ ከሆኑት ህይወት አልሚ ጥረቶች አንዱ ነበር።

በቅርቡ የዓለም መንግሥታት የዕርዳታ ድርጅት የምግብ ዕርዳታ ለማድረስ በኤርትራ ግዛት በሚጓዝበት ጊዜ በነፃአውጭ ድርጅት ተመትተው መኪናዎቹም ምግቡም በእሳት ተቃጥሎ ቀርቷል። ይህ የብዙ ሺህ ረሃብተኞችን ህይወት ማዳን የሚችለው ዕርዳታ እንዳይደርስ መደረጉ የረሃብን መስፋፋት መርዳቱ አይቀርም።

የኢትዮጵያ ወታደራዊ መንግሥት በሚያደርገው የማውደም ዘመቻ ይህ ነው የማይባል ጥፋት በየአካባቢው ማድረሱ የታወቀ ነው። ይህም መፍትሔ አልባ ሁኔታን በማስፋፋት የጦርነት ኢኮኖሚና አቋምን በማጠናከር ልንወጣ የማንችለው ችግር፣ ረሃብና ድርቅ ውስጥ ጥሎን የዓለም መሳለቂያ አድርጉን እንገኛለን።

## 4– የተዘበ ፖሊሲ

የስኮትላንዱ ተጓዥ ጄምስ ብሩስ ስለተዛበ አስተዳደር እንዲህ ሲል ፅፏል:- «ትላልቅ ጉንዳኖች፣ የአይጥ መንጋ… ብዙ እህል ፈጀ። ከዚህ ሁሉ መቅሰፈት የባሰው ግን መጥፎ መንግሥትና አስተዳደር ነው። መጥፎ መንግሥት ህዝቡ ከተፈጥሮ፣ ከተመክሮ ያገኘው ንብረቱን፣ ማንነቱን ከመቀፀበት ያወድምበታል። »[31]

የመንግሥት ፖሊሲ የረሃብና የድርቅን ሁኔታ ለመከላከል፣ ለማስወገድ፣ ወይም

ለማባበስ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

ብዙ በረሃብና ድርቅ የተ ጉዱ አገሮች መንግሥታት ስርነቀል፣ ቀራጥ፣ ከአካባቢያቸው ጋር የተጣጣመ እርምጃ መውሰድ ይሳናቸዋል። አብዛኛውን ህዝብ በገጠር የሚኖር እርሶ አደር መሆ ኑ እየታወቀና የአገሮቹ የኢኮኖሚ መሠረትም ባለቤት መሆ ኑ እየታወቀ ባሳገሩ በድርቅና በረሃብ ሲጠቃ ሁሉም ነገር ወደ እርሻና የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤና ልማት ግንባር አለመዋሉ በችግሩ መጠን፣ ዕድገትና ሂደት ላይ የሚገባው ትኩረት እንዳልትሰጠው ይጠቁማል። ብዙ መረባረብና ሁከታ የሚታየው ጊዜዊ በሆነ ምፅዋት ወይም ብድር ማግኘትና የተገኘውን መቀራመት ነው። አንዳንዶም ዘላቂ ተብለው በስራ የዋሉ ዕቅዶች በጥናት ያልተደገፉ፣ ባላዋቂ መክር የተዘጋጁ፣ ወጭያቸው ከጥቅማቸው ጋር ያልተመጣጠነ፣ ከአካባቢው ሁ ኔታ ያልተጣጣሙ፣ የይስሙላ ይመስላሉ። ዋና ከተማዎችን ማጋጌጥ፣ የተንዛዙ በዓሎችን ማክበር፣ ዓይን የሚስቡ «ሃውልቶችን» ለስም ማስጠሪያ ማቆም የብዙ አፍሪቃ መንግሥታት ተቀዳሚ ተግባራት የሆ ኑ ይመስላሉ።

ከአገር የተገኘውም ሆነ ከውጭ የመጣ ገንዘብ አዋዋል ኢሚዛናዊ በሆነ መንገድ በሥራ ማስኬጃ፣ በደሞዝና በውሎ አበል ያለበለዚያም ዘላቂ ውጤት በማያስገኝ ተግባር ላይ ይውላል።

ለምሳሌ የሳሄሉ ድርቅ የምዕራብ አፍሪቃን አገሮች ባጠቃበት ጊዜ ወደ ሁለት ቢሊዮን ዶላር በዕርዳታ ተገኝቶ ነበር። ከዚህ ውስጥ:-

35% ለጊዜያዊ ምግብ መግዣ

30% ለውጭ ምንዛሬ አስገኝ ምርትና የተያያዘ መስኖ

4% ለምግብ ጠቀስ ምርት

2% ለተፈጥሮ ሁኔታዎች ማሻሻያ ውሏል።

ይህ እንደሚያሳየው ድርቅን ለመከላከል፣ የአፈርን መሸርሸር ለማቆም፣ ደንን በመተከት ወዘተ ሊረዱ የሚችሉና ዘላቂ መፍትሔ ሊያስገኙ የሚችሉ እርምጃዎች ምን ያህል አነስተኛ ግምት እንደተሰጣቸው ነው።{32}

በኢትዮጵያም ተመሰሰይ ኢሚዛናዊ የበጀትና የመሬት አጠቃቀም ሁኔታ ይታያል።(33)

በ1973 ዓም ከታረሰው መሬት 3.5% የመንግሥት እርሻ ሲሆን ከመንግሥት የእርሻ በጀት እርባ ከመቶውን (40%) ተጠቅሟል። ይህ እርሻ ያመረተው ግን በአገሪቱ በጠቅላላ ከተመረተው አምስት ከመቶው (5%) የሚሆነው ብቻ ነው።

በአንፃሩ 98% የሚሆነው አራሽ ቤተሰብ 95% የሚሆነውን መሬት በማረስ 94% የሚሆነውን የአገሪቱን ምርት አምርቷል። ነገር ግን ከመንግሥት እርሻ በጀት ለተራው ገበሬ የተደረገለት እርዳታ ለመንግሥት እርሻ ከተደረገው እርዳታ ሲወዳደር ኢምንት ነበር። ለምሳሌ የመንግሥት እርሻ

80% የሚሆነውን የዱቤ አገልግሎት (CREDIT FACILITY)

95% የሚሆነውን የተሻሻለ ዘር (IMPROVED SEED)

76% የሚሆነውን ማዳበሪያና ፀረተባይ (FERTILIZER & PESTICIDES)

ሲጠቀም የእርሱ አደሩ እርሻ ግን ከ20% የሚያንሰውን አገኝቷል። አብዛኛውን ምርት ለሚያመርተው ተገቢ ድጋፍ በቀጥታ ጊዜውን ጠብቆና በብቃት ሲሰጠው ካልቻለ የረሃብና የድርቅ ሁኔታ በአሁኑ አያያዝ መገታት አይችልም።

ለአገር መከላከያና ለጦርነት የሚደረገው ትኩረት እንደዚሁ ለሌሎች የምርትና የዕድገት መስኮች ከሚደረገው ትኩረት ጋር ሲወዳደር ኢሚዛናዊነቱ ጉልቶ ይታያል። «የመከላከያ» በጀት ለ1975/76 የተያዘው አንድ ቢሊዮን ብር ሲሆን ከጠቅላላው የአገሪቱ በጀት 46% በመሆን ግማሹ ሊሆን ትንሽ ነው የቀረው። በዚሁ ዓመት ለእርሻና ለሰፈራ 10% ብቻ ነበር የተደለደለው። ከ1971 ዓም ጀምሮ «የመከላከያ» በጀት በመካከለኛ ግምት ከጠቅላላው የአገሪቱ በጀት ከሲሶ አንሶ አያውቅም።(34)

ኢትዮጵያ ከ1971 እስከ 1975 ዓም ሁለት ቢሊዮን ዶላር (አራት ሺህ ሚሊዮን ብር) ያወጣ የጦር መሳሪያ በመግዛት ከሰሃራ ምድረበዳ በታች ካሉት የአፍሪቃ አገሮች በጦር መሳሪያ ብዛት፣ ጥራትና እስከ ሦስት መቶ ሃያ አምስት ሺህ ጦር ለማሰለፍ በመቻል አንደኛነቱን ይዛለች (ደቡብ አፍሪቃን

አይመለከትም)።(35) ለዚህም ሳይሆን አይቀርም በረሃብ፣ በድህነት፣ በስደተኛ ብዛት በኋላ ቀርነትም እንደዚሁ አንደኝነትን የያዘች። ኢትዮጵያ ከ150 የማያንሱ ተዋጊ አይሮፕለኖች እንዳሏት ይነገራል።(36) የብራንት ኮሚሽን የአንድ ተዋጊ አይሮፕለን ዋጋ ከአርባ ሚሊዮን ብር በላይ እንደሚሆን የአንድ ተራ ታንክ ዋጋ ደግሞ ሁለት ሚሊዮን ብር እንደሚሆን ገልጿል፣ በአንፃሩ አንድ ታንክ ለመግዛት በሚወጣው ገንዘብ ለሰላሳ ሺህ ተማሪዎች የሚበቁ አንድ ሺህ የትምህርት ቤት ክፍሎች ሊሰራበት ይችል እንደነበር ይጠቁማል።(37)

በእርሻ መሬት ድልዳሊም ረገድ በብዙ አፍሪቃ አገሮች የተዛባ አሰራር ይታያል። ጥሩ ጥሩ ለምና ለመጓጓዥ ቅርበት ያላቸው መሬቶች ለምግብ እህሎች ማምረት ከመዋላቸው ይልቅ የውጭ ምንዛሪ ሊያስገኙ ለሚችሉ እንደ ቡና፣ ሻይ፣ ትምባሆ፣ ስኳር ጥጥ ወዘተ ላሉ የመንግሥትና የትርፍ ኩባንያዎች ለሚያስተዳድራቸው እርሻዎች ይውላሉ። መንግሥትም ለእንደነዚህ ዓይነቶች መስኮች ቅድሚያ ስለሚሰጥና የተራ ገበሬዎችን ጥረት ስለማይደገፍ ገበሬው በመንግሥትና ኩባንያ እርሻዎች ተቀጣሪ ሠራተኛ በመሆን ከአምራችነቱ ተገልሎ ጥገኛ ሆኖ ይቀራል። ይህም ዓይነተኛ የረሃብና የችግር ምክንያት ሆኗል።

ለምሳሌ የሳሄል አከባቢ አገሮች የቡና፣ የሻይ፣ የስኳር፣ የጥጥ፣ የኮኮና የትምባሆ ምርት በዓመት 12% ሲጨምር የምግብ ምርት ግን አቆልቁሏል።(38)

ስለዚህም እነዚህን በማምረት የተገኘ የውጭ ምንዛሪ ውድ የሆኑ መሣሪያዎችን፣ ምግቦችንና መንደላቀቂያ ዕቃዎችን በማስመጣት የባሰ ችግር ውስጥ እየወደቁ ያሉ አገሮች ብዙ ናቸው።

## 5– የተዛባ ቴክኖሎጂ

አንዳንድ ድርቅና ረሃብ ለማስወገድ ወይም ለመቆጣጠር የሚደረጉ ጥረቶች የሚያስከትሉት ጉዳት እልፎ እልፎ ከቁጥጥር ውጭ በመሆን ተጨማሪና አዲስ

ችግር ይፈጥሩ ይሆናል። ይህን በሚመለከት ሊጠቀሱ የሚገባቸው የማዳበሪያ ንጥረ ነገሮች፣ ተባይ የሚያጠፉ መድኃኒቶች፣ ትላልቅ ግድቦች፣ የውሃ ጉድጓዶች፣ የተሸሸሉ ወይም ድቅል ዘሮች ወዘተ ይገኙባቸዋል። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ነገሮች የሚፈጥሩዋቸው ችግሮች አብዛኛውን ጊዜ የጥናት መጉደል፣ መጠንን አለማወቅ፣ የሌሎችን ተመክሮ አለማጤን፣ አዲስ ነገሮችን ተስገብግቦ ማግበስበስ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህም ጥቅማቸውን ከችግራቸው ጋር አመዛዝኖ መጠቀም የተገባ ይሆናል።

ተባይ የሚያጠፉ መድኃኒቶች ብዙውን ጊዜ ተባይን ብቻ ሳይሆን የሚያጠፉት ለአዝዕርት የሚያስፈልጉ ፍጡራንን አብሮ በማጥፋት ለምርት ተፈላጊ የሆኑትንም ጨምረው ሊያጠፉ ይችላሉ።{39}

ግድቦች አብዛኛውን ጊዜ ትላልቆቹ ከፍተኛ ወጪ ከመጠየቃቸው በስተቀር ብዙ የተማረ የሰው ሃይል ይፈልጋሉ። በተጨማሪም የአካባቢውን የጨው መጠን በመጨመር የእርሻ መሬቶች ለምርት እንዳያመቹና ለእሣም ማራባት እንቅፋት ይሆናሉ። ግድቦችና መስኖዎች እንዳየአካባቢው ሁኔታ ለቀንድ አውጣና ለሌሎች ነፍሳት መራባት አመች ሁኔታን በመፍጠር ለቢላርዝያና (BILHARZIA) ለዓይን አሳዋሪው እንክሰርኪያሲስ (ONCHOCERCIACIS) በሽታዎች መስፋፋት ምክንያት ይሆናሉ። እነዚህ ድርብርብ ሁኔታዎች በምርትና በሰው ሃይል ተፅዕኖ በማድረግ ለረሃብና ተመሳሳይ ችግሮች አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።{40}

የተሸሸሉ ዘሮች ብዙውን ጊዜ ከውጭ የመጡ ስለሚሆኑ ለአካባቢው ዓየርና የመሬት ጠባይ እንግዳ በመሆን ዘላቂነታቸው አጠያያቂ ይሆናል። አዲስ ዘሮች በቀላሉ ለበሽታ የተጋለጡ ይሆናሉ። ድርቅን የመቋቋም ጉልበታቸው የተዳከመ ሊሆን ይችላል። ይህም አጠቃላዩ ምርት ላይ በመንፀባረቅ ረሃብን ሊያባብስ ይችላሉ። ስለዚህም በተቻለ መጠን የአካባቢውን ዘሮች በሚገባ በመንከባከብ፣ ተፈጥሮአዊ ማልሚያ ነገሮችን መጠቀም፣ የአፈር አያያዝና አጠቃቀም መቆጣጠር፣ የውሃ አጠቃቀም ማጤን ለዘላቂ መፍትሔ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ።

## 6– ድህነት

የምግብ አለማግኘት በመሰረቱ የረሃብ ዋነኛ ምክንያቱ ቢሆንም ስረ መሠረቱ ድህነት ነው። በአፍሪቃ ድርቅም እያጠቃቸው ረሃብ ግን ያላሸነፋቸው አገሮች አሉ። ይህ ጉልቶ የሚታየው በሰሜን አፍሪቃ ነው። ይህ ሊሆን የቻለበት ዋና ምክንያት የምግብ ፍላጐታቸውን በብዛት የሚያረኩት በግዢ ስለሆነና አገሮቹ የተፈጥሮ ሃብታቸውን በሚገባ በመጠቀም በቂ ገንዘብ ስለሚያመነጩ ነው። በኢትዮጵያ ረሃብ ያጠቃው ደሀውን ገበሬና ድሀውን ከተሜ ነው እንጂ ገንዘብ ያለውን አይደለም።

ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በዓለም በጣም ደሃ ተብለው ከሚታወቁት ዋንኛዋ ናት። ኢትዮጵያ በቂ የተፈጥሮ ሃብትና ይህንንም ለማዳበር የሚችል በቂ የሰው ሃይል ቢኖራትም ይህንን የተፈጥሮ ስጦታ በሚገባ ለማዳበርና ለኅብረተሰቡ ጥቅም ለማዋል ስለአልቻለች እንደብዙዎቹ የአፍሪቃ አገሮች በሰው ሰራሽ ድህነትና ረሃብ ሥር እየማቀቀች ትገኛለች።

የአፍሪቃ አገሮች ድህነት እንዲህ ተጋኖ የሚነገረው ለልመናና ለዘረፋ፣ ለማታለያና ከሃላፊነት ለመሸሽ እንዲያመች ሰበብ ከልሆነ በስተቀር በየአገሮቹ የሚመረተው ምርትና የሚዘዋወረው የገንዘብ መጠን በሚገባ ቢከፋፈልና የህዝብን መሠረታዊ ፍላጐት ለሚያሟሉ ዕቅዶች ቢውል ይህ ሁሉ ባልተወራ ነበር። አብዛኛዎቹ የአፍሪቃ አገሮች በብድር ዕዳ፣ በዱቤ ተይዘው ዋናውን ሳይሆን የዋናውን ወለድ እንኳ መክፈል አቅቶአቸው ሲገኙ፣ በንፃሩ የነዚህ አገሮች መሪዎች፣ ባለሟሎቻቸውና የውጭ አገር ባልደረቦቻቸው በተለያዩ መንገዶች በሚያሰፍር ሁኔታ የሕዝቡን ንብረት ሲንደላቀቁበት ይታያል።

ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ናቸው ድህነትን ሰው ሰራሽና የረሃብም ነፀብራቅ አድርገው የሚገልፁት። ይህ ዓይነቱ የአስተዳደር ጉድለት፣ ጭካኔ የተሞላው ብዝበዛና ግለሰብኝነት ለዚህ ዓይነቱ ረሃብና ችግር ዋና ምክንያት ሆኗል።

## 6– ድህነት

የምግብ አለማግኘት በመሰረቱ የረሃብ ዋነኛ ምክንያቱ ቢሆንም ስረ መሠረቱ ድህነት ነው። በአፍሪቃ ድርቅም እያጠቃቸው ረሃብ ግን ያላሸነፋቸው አገሮች አሉ። ይህ ጉልቶ የሚታየው በሰሜን አፍሪቃ ነው። ይህ ሊሆን የቻለበት ዋና ምክንያት የምግብ ፍላጉታቸውን በብዛት የሚያረኩት በግዢ ስለሆነና አገሮቹ የተፈጥሮ ሃብታቸውን በሚገባ በመጠቀም በቂ ገንዘብ ስለሚያመነጩ ነው። በኢትዮጵያ ረሃብ ያጠቃው ደሀውን ገበሬና ድሀውን ከተሜ ነው እንጂ ገንዘብ ያለውን አይደለም።

ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በዓለም በጣም ደሃ ተብለው ከሚታወቁት ዋንኛዋ ናት። ኢትዮጵያ በቂ የተፈጥሮ ሃብትና ይህንንም ለማዳበር የሚችል በቂ የሰው ሃይል ቢኖራትም ይህንን የተፈጥሮ ስጦታ በሚገባ ለማዳበርና ለኅብረተሰቡ ጥቅም ለማዋል ስለአልቻለች እንደብዙዎቹ የአፍሪቃ አገሮች በሰው ሰራሽ ድህነትና ረሃብ ሥር እየማቀቀች ትገኛለች።

የአፍሪቃ አገሮች ድህነት እንዲህ ተጋኖ የሚነገረው ለልመናና ለዘረፋ፣ ለማታለያና ከሃላፊነት ለመሸሽ እንዲያመች ሰበብ ከልሆነ በስተቀር በየአገሮቹ የሚመረተው ምርትና የሚዘዋወረው የገንዘብ መጠን በሚገባ ቢከፋፈልና የህዝብን መሠረታዊ ፍላጉት ለሚያሟሉ ዕቅዶች ቢውል ይህ ሁሉ ባልተወራ ነበር። አብዛኛዎቹ የአፍሪቃ አገሮች በብድር ዕዳ፣ በዱቤ ተይዘው ዋናውን ሳይሆን የዋናውን ወለድ እንኳ መክፈል አቅቶአቸው ሲገኙ፣ ባንፃሩ የነዚህ አገሮች መሪዎች፣ ባለሟሎቻቸውና የውጭ አገር ባልደረቦቻቸው በተለያዩ መንገዶች በሚያሰፍር ሁኔታ የሕዝቡን ንብረት ሲንደለቀቁበት ይታያል።

ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ናቸው ድህነትን ሰው ሰራሽና የረሃብም ነፀብራቅ አድርገው የሚገልፁት። ይህ ዓይነቱ የአስተዳደር ጉድለት፣ ሞክኑ የተሞላው ብዝበዛና ግለሰብኝነት ለዚህ ዓይነቱ ረሃብና ችግር ዋና ምክንያት ሆኗል።

## 7— ጤንነትና ረሃብ

በአስተዳደር ጉድለት፣ በኢኮኖሚ ድቀትና በኋላ ቀርነት በሚደከር ኅብረተሰብ ውስጥ ረሃብ በሽታን በሽታም ረሃብን ያስከትላል። አንድ ሀይወት ያለው ነገር ጤናማ ነው ተብሎ የሚነገረው ለኑሮ መሠረታዊ ፍላጐቶች ተሟልተው ሲገኙ ነው። በዝቅተኛው ደረጃ ሰው ለመኖር ውሃ፣ ዓየር፣ ምግብ፣ መጠለያ፣ መሸፈኛ ያስፈልገዋል። እነዚህ ከተሟሉ በኋላ ሌሎች የኅብረተሰብ፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ ፍላጐቶች እንደየበታውና ሁኔታው መሟላት ይጀምራሉ።
ለሰውነት ምግብ፣ ውሃና ዓየር ወሳኝ ፍላጐቶች ሲሆኑ የነዚህ ማነስ ሰውነትን በማድከም ለበሽታና ለሀመም ያጋልጣል። የደከመ ሰውነት በሽታ መከላከል፣ የሰውነትን ልዩ ልዩ ህዋሳትና አካላት ማጉልመስ፣ ተንቀሳቅሶ አምርቶና አዘጋጅቶ መብላት ይሰነዋል። የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ወይም አለማግኘት ለረዥም ጊዜ ሲደጋገም የመጨረሻ ደረጃ ረሃብ ወይም ጠኔ ይደርሳል።
ለረሃብ የተጋለጠ ሰው የሰውነት ክፍሉ እድገት የተቀጨ፣ የጫጫ ይሆናል። አብዛኛውንም ከሁለት ዓመት ዕድሜ በታች ባሉ ህፃናትና እርጉዞች ላይ ያልተሟላ ምግብ አለማግኘት በሚወልዱት የህፃናት አንጉል እድገት ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። አንጉል ወሳኝ እድገት የሚያደርገው በዚህ እድሜ ክልል ውስጥ ነው። ባልተሟላ ምግብ ያደጉ ህፃናት አስተሳሰብ ችሎታና የአንጉሉ ዕድገት ዝቅ ያለ ሊሆን እንደሚችል ይነገራል።
ድርቅና ልዩ ልዩ ሁኔታዎች የፈጠሩት የምግብ እጥረት ረሃብና በሽታን ያስከትላል። ረሃብ በጠቃው ህብረተሰብ ተላላፊ በሽታዎች የተስፋፉ ናቸው። በሽታዎቹ የሚያጠቁት ሰውን ብቻ ሳይሆን በሽታን መከላከል ያልቻሉ እንስሳትና አዝዕርትንም ጭምር ነው።
የኢትዮጵያ ታላቁ ረሃብ ተብሎ በሚጠራው በ1881–84 ረሃብ ጊዜ በሽታ ተስፋፍቶ ነበር። ፀሐፊ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ ሲፅፉ፦[41] «በዚህም ዘመን በሽታ ገብቶ ሰዎች ሞቱ .... በዚያን ጊዜ ይህንን በሽታ ታሞ የሚተርፍ የለም» ብለው

«.... ቢጊምድር በዚያ በክፉ ቀን በትልቁ ረሃብና በበሽታ ሰው ከብቱም አልቆ እንኳንስ ሰምና በሬ፣ ዶሮና ውሻ እንኳ በገሩ አይጮህም ነበር።» ሲሉ የረሃብንና የበሽታን አጥቂነት ገልፀዋል።

በኢትዮጵያ በልምድ፣ በሃይማኖትና በተለያዩ ምክንያቶች ለመበላት የማይፈቀዱ፣ ነገር ግን በሌሎች አገሮች ያለምንም ተፅዕኖ ዘወትር የሚበሉ የሥጋም ሆነ የአዝዕርት ምግብ ዓይነቶች በርካታ ናቸው።

የአመጋገብ ልምድን እስከተቻለ ደረጃ ለመቀየር መሞከር የረሃብን ስፋትና መጠን እንደሚቀንስ መገመት ይቻላል።

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ወግ አጥባቂ አካባቢዎች የሚዘወተር የምግብ ዓይነት መጥፋት ህዝቡን አማራጭ ያሳጣዋል። የዚህ ዓይነት ሁኔታ ነው አልፎ አልፎ ህዝቡ መርዘኛ የሆኑ ምግቦችን ያለጥንቃቄ እንዲበላ የሚያስገድደው። ለምሳሌ በወሎ በተከታታይ ድርቅና ረሃብ ህዝቡን ስለአጠቃው የምግብ መጥፋት ጊያ ተብሎ የሚታወቀውን መርዘኛ የሆነ አተር መሰል እህል (LATHYRUS SATIVA) እንዲበላ አድርጉታል። ይህ የጊያ ተክል ድርቅን የመቋቋም የተለየ ችሎታ ስለአለው ለምልሞ በመታየት ረሃብተኛን ያጓጓል። ይህን የተመገበ ሰው ላስሪዝም (LATHYRISM) የሚባል አን ጉልንና ነርቭን የሚያጠቃ ብሎም የሚያሽመደምድ በሽታ ይይዘዋል። ይህ በሽታ ድርቅና ረሃብ ባጠቃበት አካባቢ እንደተላላፊ በሽታ ሆኖ ተከስቷል።[42]

በተመሳሳይ አካባቢዎች የሚበቅሉ ገብስ ዓይነት እህሎችን የፈንገስ (FUNGUS) በሽታ ይይዛቸዋል። ይህ በፈንገስ የተለከፈ እህል በሚበላበት ጊዜ ኤርጉቲዝም (ERGOTISM) የሚባል የደም ስርን በማጥበብ የደምን መተላለፍ የሚከላከል እንደ ጋንግሪ ያለውን በሽታ ያስከትላል። በሰሜን ኢትዮጵያ አንዳንድ በእርዳታ የመጡና የተዘሩ ዘሮች በዚህ የእህል በሽታ በቀላሉ መጠቃታቸውና ከዚህም የተነሳ የተበከለውን እህል የበሉ ሰዎች የኤርጉቲዝም ቁራኛ እንደሆኑ ይወራል።

እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ነባሩን ችግር በማባባስ ህዝቡን ለተጨማሪ ረሃብና

አልቂት ያበቃዋል።።

## 8- እንበጣና ረሃብ

አፍሪቃ ለረጅም ጊዜ በእንበጣ መንጋ በመጠቃት የልዩ ልዩ አዝርዕት ጥፋት ደርሶበታል። የዚህ ዓይነቱ ችግር በኢትዮጵያ የሚታየው በሰሜን አከባቢዎች ሲሆን የታሪክ ፅሑፎች ስለዚህ ችግር ደጋግመው ይናገራሉ።

በ1512-18 በትግራይ ከፍተኛ ጥፋት ያደረሰው የእንበጣ መንጋ ነበር። ስለዚሁም ፖርቱጋሊዊው ተጓዝ ፍራንሲስኮ አልቫሬዝ ሲናገር «ምድር በማይታመን ሁኔታ በአነበጣ ተሸፍኖ፣ ዓየሩ ተሞልቶ የፀሐይ ብርሃን ከልክሎ ነበር» ይላል።

ለ1881-84 ታላቅ ረሃብ አስተዋፅዖ ካደረጉት ጦርነት፣ ድርቅ፣ ተስላፊ በሽታ በላይ እንበጣም ይገኝበታል። በቅርብ በታዩትም የኢትዮጵያ ረሃቦች እንበጣ ድርሻውን አድርጓል።

በተከታታይ በሰሜን ኢትዮጵያ እንደታየው ድርቅና ጦርነት ረሃብን ከስከተለ በኋላ መጠነኛ ዝናብ መጥቶ ህዝቡ ማምረት ሲጀምር እንበጣ መጥቶ ያመረተውን ያወድመዋል። በዚህም የተነሳ ከአንድ ረሃብ ወጥቶ ወደሌላው ይገባል። ይህም ብዙ ጊዜ መንግሥትንና ህዝብን ግራ አጋብቶ ተስፋ ማስቆረጥ ደረጃ የደረሰ ይመስላል። ይባስ ብሎ አንዳንዴ ከዚህ ችግር ጋር በረዶ በመጣል የተዘራውን ያጠፋዋል፣ ጉርፍም እንዲሁ ከፍተኛ አደጋ ያደርሳል። እነዚህ ክስተቶች እየተፈራረቁ ነው ሁኔታውን ተስፋ የለሽ ያስመሰሉት።

የእንበጣ መንጋ ከድርቅ በኃላ ከሚመጣ ዝናብ ጋር የተገናኘ ነው። የመሬቱ እርጥበት እንበጣ እዲፈለፈል አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል። የዘድሮው የእንበጣ መንጋ በ1920 ዎቹ ከታየውና አስር ዓመት ሙሉ አፍሪቃን ከጠቃው የከፋ ነው ይባላል።

እያንዳንዱ እንበጣ ሁለት ግራም ምግብ በቀን ይበላል፣ በቀን እስከ ዘጠና ኪሎሜትር ይጓዛል። ብዙ ቢሊዮን እንበጣ ያዘለ መንጋ ስማኒያ ሺህ ቶን ማሽላ

በአንድ ቀን የበላበት ሁኔታ እንደነበር ሲታወቅ ይህ መጠን አርባ ሺህ ሰዎች ለአንድ ዓመት ይመግብ የነበር ነው።(43)

አንበጣን ለማጥፋት ልዩ ልዩ ፀረ-ነፍሳት መድኃኒት መጠቀም ቢቻልም፣ ፀረ-ነፍሳት መድኃኒት አንበጣውን ከማጥፋቱም በላይ ሌላ ለእርሻ የሚያስፈልጉ ነፍሳትም ጨምሮ ስለሚያጠፋ ጠቀሜታው ከጉዳቱ መመዘዘን አለበት።

እልፎም ለፀረ አንበጣው መድኃኒት የተጋለጠው ምርት በሰው ወይም በእንስሳት በሚበላበት ጊዜ አደጋ የማስከተል ችሎታም ሊኖረው ይችላል። ፀረ-አንበጣ መድኃኒት ለጊዜው በራሪውን አንበጣ ቢገድልም በመሬት ውስጥ የተደበቀውን እንቁላል ስለማይገድል ትንሽ ዝናብ ሲመጣ ችግሩ ተመልሶ ይመጣል።

በውሃና በደን አያያዝ በአስተዳደር መስተካከል መሻሻል የድርቅና የረሃብን አደጋ መቆጣጠር ይቻላል ከተባለ ለአንበጣ አመች ሁኔታዎችን በመቆጣጠር የአንበጣንም አደጋ መቀነስ ይቻላል። የአንበጣ ችግር አህጉራዊ ስለሆነም ተገቢው ትብብር ከሚመለከታቸው ጋር ማድረግ ይረዳል።

## ፯ መደምደሚያ

የረሃብና ድርቅ መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው ከሚነገርላቸው ዋና ዋናዎቹ ተጠቅሰዋል። አብሮም ለችግሮቹ መፍትሄ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ የሚባሉት በመጠኑ ተጠቅሰዋል።

የተዛባ የዓየር ሁኔታ፣ ኋላቀር የርሻ ዘዴ፣ ከፍተኛ የአፈር መሸርሸርና ለምርት አመች አለመሆን፣ የገበሬው በቂ ድጋፍ አለማግኘት፣ ብዙ ሰውና እንስሳ በትንሽ መሬት ላይ መረባረብ፣ የገብያ ሁኔታ አለመሻሻል፣ የህዝብ ቁጥር እየጨመረ መሄድ፣ የትራንስፖርት አገልግሎት በባለገሩ አለመኖር፣ የሠላም መጥፋትና ሁሉም ነገር ጦርነት ላይ ማተከር፣ የውጭ መንግሥትና ድርጅቶች የተለያየ ተፅእኖች ማድረግ ወዘተ ችግሮቹን በማጠሳሰብ የኅብረተሰብን መሠረታዊ ህልውና አጠያያቂ ደረጃ ላይ አድርሶታል። በብዙ ዘመናትና ትውልድ

የተመሰረተን ባህል፣ልዕልና፣ ኩራት፣ ተመክሮ፣ግንኙነት፣ ተስፋ፣ ታሪክ በማመንመን ላይ ይገኛል።

አብዛኛዎቹ ችግሮች ሰው ሰራሽ ያለበለዚያም የሰው ተግባር ያባባሳቸው ሆነው ይታያሉ። የተፈጥሮ ችግር ተብለው የሚጠሩት በአሁኑ ጊዜ በሰው ቁጥጥር ስር ሊውሉ የሚችሉ ጥቂቶች አይደሉም። ነገር ግን እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ በመወሰድ ላይ ያሉት እርምጃዎች ቁንፅል፣ በጥናት ላይ ያልተመሰረቱ፣ ምልአተ ህዝቡንና ነገረ ተመክሮውን የማያሰትፍ በግል ጥቅም ዝናና በግን አህሎኝነት (በሽንገላ) ላይ የተመሰረተ ያለበለዚያም ባለማወቅ የሚደረጉ ስለሆኑ ብዙ ጊዜ ከሚሰጡት ጥቅም ጉዳታቸው ጉልቶ ይታያል።

በፅሑፍ ውስጥ ጊዜያዊ ዕርዳታዎች የሚያደርጉት አስተዋፅዖ አልተገለፁም። የነዚህ እርዳታዎች መጠንም ሆነ ዓይነት፣ ሊያደርሱ የሚችሉትን ውጤት ለማኮሰስ ሳይሆን ራሱን የቻለ ፅሑፍ ስለሚወጣው ላለመንካት ነው። በዚህ ረገድ መጠቀስ የሚገባው ብዙ ጊዜ የአገርም ሆነ የውጭ መንግሥታት ለአጭር ጊዜ ዕርዳታ ትኩረት በመስጠት ዘላቂ መፍትሔዎች ላይ የሚያደርጉት ዕርዳታ እስከዚህም ይሆናል። በሌላው ፅንፍ ደግሞ ችግሮቹን ለማስወገድ ቢርከራሲን ከመቀነስ ይልቅ ለአስተዳደርና ለአፈፃፀም የማያመቹ አውታሮችን በመዘርጋት እራሱን የቻለ ችግር ማብዛት የተለመደ ሆኗል።

በማጠቃለልም በአሁኑ ጊዜ በዓለምም ሆነ በየአካባቢው ለተፈጠሩትና መፈጠር ላይ ላሉት ተመሳሳይ ችግሮች እያንዳንዱ ግለሰብ አስተዋፅዖ በማድረግ ላይ ስለአለ፣ ለመፍትሔው እንደዚሁ ሊያበረክተው የሚችለውን መፈለግ፣ መወያየትና በተግባር መፈፀምም የግለሰብ ሃላፊነት ነው። አብዛኛውንም አዲሱና የተማረው ትውልድ ይህንን ሁኔታ የማስወገድ የወገን፣ የአገር፣ የትውልድ ሃላፊነት አለበት። ይህን ሁኔታ ለመቀየር የሁሉንም ኅብረተሰብ ክፍል አስተዋፅዖ ይጠይቃል።መፍትሔውም በፈቃደኝነት፣ በበጐ ፈቃድ፣ በመከባበር፣ በሁሉም ተሳትፎ፣ በመተባበር፣ በመቻቻል፣ በብልሃተኝነት፣ በእኩልነት፣ በትጋት፣ በመተማመን፣ በታማኝነት፣ በአርቆና አስፍቶ አስተዋይነት፣ ላይ

የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል። ሁሉም የእቅሙን የሚያበረክትበት ወቅት ነው። ከሁሉም በላይ ይልቅ የመንግሥት ህዝባዊነት፣ የህዝብ በሁሉም ደረጃ ትጋትና መሰረታዊ ተሳትፎ፣ የህዝብ መሠረታዊ ፍላጐት አርካታ ቅድምያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች መሆን አለባቸው።

## ፯– <u>የግርጌ ማስታወሻዎች</u> ( )

1–7 JOHN W MELLOR & SAHAR GAVIAN, <u>SCIENCE, FAMINE: CAUSES, PREVENTION AND RELIEF</u>. Vol. 235 Jan 1987,PP 539

8 <u>The Challenges of Drought</u>. The Relief and Rehabilitation Commission. Addis Ababa, 1985.

9 ፀሐፊ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ፣ ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ: 1959።

10 The Challenges of Drought,...

11 Special Report FAO/UN 1984.

12 <u>Ethiopia: Famine Fact Sheet</u>, UN Emergency prevention and Prepardness Group. Addis Ababa Mar. 1988.

13 <u>Early Warning System</u>, RRC, Special Report, Addis Ababa, Aug. 1987.

14 <u>Beyond the Famine, Food for the Hungry Int'l, An Examination of the Issues Behind Famine in Ethiopia</u>, Feb,1988.

15 GAIA, An Atlas of Planet Management, NY,1984. pp 116

16 <u>National Geographic, «Are We Poisoning Our Air,»</u> Vol.171 NO.4. Apr, 1987.

17 <u>Scientific American, «Acid Rain's Threat,»</u> Aug, 1988.

18 <u>National Geographic</u>,« <u>A Dam Against Famine,</u>» Vol. 167 No. 5, May 1985.

19 Ieuan Le, Griffiths, <u>An Atlas of African Affairs</u>.

20 Lloyd Timberlake, Africa in Crisis, 1986. pp198

21 The Challenges of Drought,...

22 Beyond the Famine,...pp97

23 Lloyd Timberlake,... pp129

24 Panoscope, No.6, May 1988. pp11

25 Beyond the Famine,...pp61

26 Scientific American,...

27 Beyond the Famine,...

28 Beyond the Famine,...

29 ፀሐፌ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ,...

30 The Challenges of Drought,...

31 James Bruce, Travels to Discover the Source of the Nile, 1790.

32 Lloyd Timberlake,...

33 World Bank, Recent Economic Development and Prospects for Recovery and Growth. 1987

34 Africa south of the Sahara, 1987, pp431.

35 New Africa Year Book, 1984/85.

36 Africa south of the Sahara,...

37 Brandt Commission, Program for Survival.

38 Lloyd Timberlake,...

39 Panoscope, pesticide: a Choice Between Health and Hunger. No2 Aug 1987.

40 A de Vos, Africa: the Devastated Continent?, Mans Impact on the Ecology of Africa. The Hague,1975

41 ፀሐፌ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ,...

42 Gabre-Ab etal, Ethiopian Medical Journal, «Neurolathyrism » a Review and Report of an Epidemic,» Addis Ababa, 1978

43 Africa Report, Special Report-Locust, Sept 1986.